በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት የፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነትን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ሚያዚያ 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ማውጫ

የክዋኔ ኦዲቱ ማጠቃለያ i

ክፍል አንድ 1

መግቢያ 1

የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት አመሰራረት 1

የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዓላማ እና ሥልጣንና ተግባር 2

ራዕይ 2

ተልዕኮ 2

ዓላማ 3

ሥልጣንና ተግባራት 3

የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት መዋቅር እና የሰው ኃይል 4

ድርጅታዊ መዋቅር 4

የሰው ኃይል 5

የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት የፋይናንስ ምንጭ 6

የሰነዶች ምዝገባና ሕትመት ስርጭት ዳይሬክቶሬት የፋይናንስ ምንጭ 6

የኦዲቱ ዓላማ 7

ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Audit area) 7

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) 7

የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች 7

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ 7

የፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ የስራ ፍሰት (Process Description) 8

የህትመትና ስርጭት ዳይሬክቶሬት ፓስፖርትን ሲያትምና ሲያሰራጭ የሚከተለው የስራ ሂደት /Process Description/ 9

ክፍል ሁለት 10

የኦዲቱ ግኝቶች 10

ሀ/ የመደበኛና አስቸኳይ ፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤ 10

የኢሚግሬሽን ፖሊሲ አጸድቆ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤ 10

ተቋሙ ለፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ የሚያገለግሉ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤ 10
ተቋማዊ መዋቅር በማጥናትና በሚመለከተው አካል በማጸደቅ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤ 13
ተቋሙ የቡክሌት ፓስፖርትን ወደ ኢ-ፓስፖርት መቀየር የሚያስችል አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤ 15
ተቋሙ አጠራጣሪ የሆኑ ተገልጋዮች ሲያጋጥሙ ዜግነታቸው የሚጣራበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤ 15
ተቋሙ የፓስፖርት አገልግሎት ፈላጊዎች በተቀመጠላቸው መመሪያ፣ ስታንዳርድ እና የጊዜ ሰሌዳ መሰረት አገልግሎቱን ማግኘታቸውን የሚከታተል መሆኑን በተመለከተ፤ 18
ተቋሙ የፓስፖርት ምዝገባ ቀን ቀጠሮ ያሳለፉ ግለሰቦች የሚስተናገዱበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤ 21
ተቋሙ የፓስፖርት ስርጭትን ለማካሄድ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤ 24
ተቋሙ የፓስፖርት የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት፣ ተደራሽነትና ሽፋን ደረጃን በመገምገም፣ ጥናት ማድረጉን በተመለከተ፤ 27
ተቋሙ የፓስፖርት አገልግሎትን ለመስጠት የቢሮው አቀማመጥ የስራ ፍሰትን ባማከለ መልኩ መደራጀቱን በተመለከተ፤ 29
ተቋሙ የሰራተኞች የስነ ምግባር መመሪያና የብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል የሚያስችል አሰራር በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤ 33
በተቋሙ የተገልጋይ ቅሬታ መፍቻ ስርዓት መኖሩና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤ 36
ለ/ የፓስፖርት ግብዓቶች ግዥ አፈጻጸም ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤ 37
በተቋሙ የፓስፖርት ግብዓቶች የግዥ ዕቅድ ስለመኖሩና ግዥው በውሉ መሰረት መከናወኑን በተመለከተ፤ 37
ተቋሙ ለፓስፖርት ግብዓቶች ግዥ የግዥ መስፈርት ማዘጋጀቱን በተመለከተ፤ 41
ሐ/ የፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ የክትትል እና የስልጠና ስርዓት መኖሩንና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፤ 42
ተቋሙ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ማደራጀቱን በተመለከተ 42
ተቋሙ ዕቅድ በማዘጋጀት አፈጻጸሙን በወጥነት መገምገሙን በተመለከተ፤ 43
ተቋሙ የፓስፖርት መረጃ ህትመት ጥራትና ቁጥጥር ስራን መስራቱን በተመለከተ፤ 45
ስልጠና የሚሰጥበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤ 46
ተቋሙ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤ 47
ተቋሙ ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን የህብረተሰብ አካላት ተጠቃሚ ማድረጉን በተመለከተ፤ 49

መ/ በቴክኖሎጂ የተደገፈ ውጤታማ የመረጃ አያያዝ፣ ጥገና እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር መኖሩንና ተግባራዊነቱን መገምገም፤ 52

ተቋሙ ዘመናዊ የመረጃ ማዕከላትን (data center)፣ ምትክ ቅጂ (Backup) እና የአደጋ ጊዜ መጠባበቂያ ማዕከላት (Disaster recovery sites) ማደራጀቱን በተመለከተ፤ 52

የፓስፖርት መረጃ ጥራት እና ደህንነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የአሰራር ስርአት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤ 53

የኢሚግሬሽን አገልግሎት ለማግኘት ተገልጋዮች የሚሞሏቸው ቅጾች ዲጂታላይዝድ መደረጉን በተመለከተ፤ 54

የፓስፖርት አገልግሎት መረጃዎች እና ማስረጃዎች በአግባቡ መያዛቸውንና መወገዳቸውን በተመለከተ፤ 55

ለህትመት ማሽኖችና ለፓስፖርት አገልግሎት ስርዓቱ (System) ጥገና መከናወኑን በተመለከተ፤ 57

የፓስፖርት አገልግሎትን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፤ 59

ክፍል ሦስት 60

መደምደሚያ 60

ክፍል አራት 63

የማሻሻያ ሃሣቦች 63

አባሪ አንድ:- የመመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria) i

አባሪ ሁለት:- የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት አደረጃጀት viii

አባሪ ሶስት:- በናሙና ተመርጠው የታዩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ዝርዝር ix

አባሪ አራት:- ተቋሙ ያሉት የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ብዛት እና ስራ ላይ ያለው የሰው ኃይል x

አባሪ አምስት:- ተቋሙ በገንዘብ ሚኒስቴር የተፈቀደለት አካውንት xi

አባሪ ስድስት:- በዋና መ/ቤትና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የፓስፖርት ስርጭትን የሚያሳይ ሰንጠረዥ xii

አባሪ ሰባት:- በህትመት ጥራት ጉድለት የወደቁ የፓስፖርት ቡክሌትና ላምኔት ብዛት xiv

አባሪ ስምንት፡- በዋናው መ/ቤት እና በቅርንጫፎች የሚሰሩ ሰራተኞች በዲሲፕሊን ጉድለት ምክንያት ለዲሲፕሊን ኮሚቴ ቀርበው ጉዳያቸው ተንጠልጥለው ያሉ xv

አባሪ ዘጠኝ፡- ከህዳር 2013 እስከ ሰኔ 2013 በህገወጥ መንገድ ፓስፖርት እንዲታተም ያደረጉ 23 ሰራተኞች እና ከዛ ውስጥ 11ዱ ክሳቸው ምን ላይ እንደደረሰ የማይታወቅ ሰራተኞች ዝርዝር xvi

አባሪ አስር፡- ከ 2013 ዓ.ም አስከ ጥር 2016 ዓ.ም ድረስ ገቢና ወጪ የተደረጉ ፓስፖርትና ላሚኔት xviii

የክዋኔ ኦዲቱ ማጠቃለያ

በዓለም የፓስፖርት አገልግሎት ፍላጎት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋ የሚሄድ እንደ ሀገራት የኢኮኖሚና ማህበራዊ እድገት፣ የዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት፣ ብሔራዊ ፍላጎትና ስጋት አንጻር አደረጃጀቱ የሚለያይ እና ከሰዎች ነፃ ዝውውር እና እንቅስቃሴ ጋር የሚያያዝ ነው።

ኢሚግሬሽን በኢትዮጵያ ረጅም ዓመታት ታሪክ አለው። በሀገራችን የሚሰጡት ዋና ዋና የጉዞ ሰነዶች መደበኛ ፓስፖርት፣ ዲፕሎማቲክ ፓስፖርት፣ ሰርቪስ ፓስፖርት እና የይለፍ ሰነድ (ሊሴ ፓሴ) ናቸው።

የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን በማረጋገጥ በሥራው ዙሪያ የሚታዩ የአሠራር ችግሮች ወይም ክፍተቶች ካሉ ችግሮቹን እና መንስኤያቸውን በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦችን ለማቅረብ ነው፡፡

ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጡት የትኩረት አቅጣጫዎች፤ የመደበኛና አስቸኳይ ፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤ የፓስፖርት ግብዓቶች ግዥ አፈጻጸም ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤ የፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ የክትትልና የስልጠና ስርዓት መኖሩንና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም እና በቴክኖሎጂ የተደገፈ ውጤታማ የመረጃ አያያዝ፣ የጥገና ስርዓት እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር መኖሩንና ተግባራዊነቱን መገምገም የሚሉ ናቸው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው በተቋሙ ዋና መ/ቤት እና በናሙና በተመረጡ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ማስረጃዎችን በመከለስ፣ የሚመለከታቸውን የስራ ኃላፊዎች ቃለ መጠይቅ በማድረግ፣ መረጃዎችን በመተንተንና በአካል ምልከታ በማድረግ ነው።

ኦዲቱ የተከናወነው በአለም አቀፍ የዋና ኦዲተር መ/ቤቶች የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (International Standards of Supreme Audit Institutions (ISSAI) እና በአዋጅ ቁጥር 982/2008 መሠረት ሲሆን በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ዋና ዋና ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

- ተቋሙ ለፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ የሚያገለግሉ የጸደቀ እና ወቅታዊ የሆነ መመሪያ፣ ስታንዳርና የዜጎች ቻርተር የሌለው መሆኑ፤
- ተቋሙ ከድንበርና ከጎረቤት ሃገራት መሆናቸው አጠራጣሪ የሆኑ ተገልጋዮች ሲያጋጥሙ ዜግነታቸው የሚጣራበት መመሪያ የሌለው መሆኑ፤ ዜግነት የማጣራት ስራው በልምድ የሚከናወን፣ ውሳኔው ዜግነትን በሚያጣራው ግለሰብ መልካም ፈቃድ ላይ የተመሰረተና ወጥ የሆነ አሰራር የማይከተል መሆኑ፤
- ተቋሙ የአዲስ መደበኛ ፓስፖርት እና የፓስፖርት እድሳት አገልግሎት ፈላጊዎች አገልግሎቱን በምን ያህል ጊዜ እንደሚያገኙ የተቀመጠ መመሪያ እና የጊዜ ሰሌዳ የሌለው መሆኑ፤ ፓስፖርት በቀነ ቀጠሮ የማይሰጥ፤ በቀጠሮ ያልደረሰላቸው ተገልጋዮች ማንን መጠየቅ እንዳለባቸው የሚገለጽበት አሰራር አለመኖሩ እና አገልግሎቱን በወቅቱ ማግኘታቸውን የማይከታተል መሆኑን፤
- የኢትዮጵያ ፌደራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 3 ላይ በህግ ካልተፈቀደ በስተቀር ማናቸውንም የመንግስት ገንዘብ መሰብሰብ እንደማይቻልና የመንግስት ገንዘብ እንዲቀበል ወይም እንዲሰበስብ ሥልጣን የተሰጠው ሰው ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የተቀበለውን ወይም የተሰበሰበውን የመንግስት ገንዘብ ወደተጠቃለለው ፈንድ ገቢ እንደሚያደርግ፣ ገንዘብ የተቀበለበትን እና ገቢ ያደረገበትን ደረሰኝ መዝግቦ እንደሚይዝ ቢገልጽም፤
    - ተቋሙ ገንዘብ ለመሰብሰብ መመሪያ የማውጣት ስልጣን ሳይኖረው በ21/12/2015 ዓ.ም የፓስፖርት ምዝገባ ቀን ቀጠሮ ያሳለፉ ግለሰቦችን በቅጣት ለማስተናገድ (የቅጣት ክፍያ ተመን) መመሪያ አዘጋጅቶ በዋና ዳይሬክተር ያጸደቀ መሆኑ፤
    - የመንግስት የባንክ ሂሳብ የመክፈትና የመዝጋት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ስልጣን ሆኖ ሳለ ተቋሙ የሂሳብ ቁጥር 1000569485782 በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በግለሰቦች ስም ከፍቶ ገቢ የሚሰበስብ መሆኑ፤
        - ✓ በአጠቃላይ አካውንቱ ከተከፈተበት እ.ኤ.አ ከ01/09/2023 እስከ 29/01/2024 ድረስ በአምስት ወራት ውስጥ ብር 17,940,165.91 (አስራ ሰባት ሚሊየን ዘጠኝ መቶ አርባ ሺህ አንድ መቶ ስልሳ አምስት ብር ከ91/100) ወደ አካውንቱ ገቢ የተደረገ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ የስራ

ኃላፊዎቹ በቃል እንደለጹት ለትርፍ ሰዓት ክፍያ እና ለበዓል ለሰራተኛው ስጠታ ብር 9,324,355.76 (ዘጠኝ ሚሊየን ሶስት መቶ ሀያ አራት ሺህ ሶስት መቶ ሀምሳ አምስት ብር ከ76/100) ለመንግስት ስራ የተሰበሰበን ገንዘብ ያለገንዘብ ሚኒስቴር ፈቃድ ወጪ የተደረገ መሆኑ እና እ.ኤ.አ በ29/01/2024 ብር 8,615,810.15 (ስምንት ሚሊየን ስድስት መቶ አስራ አምስት ሺህ ስምንት መቶ አስር ብር ከ15/100) በአካውንቱ ላይ ቀሪ የሚገኝ መሆኑን፤

- የኢትዮጵያ ፌደራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ ማናቸውም የመንግስት ገንዘብ የሚሰበሰበው ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያሳትመው ወይም እንዲታተም በሚፈቅደው ደረሰኝ ብቻ እንደሆነ የተገለጸ ቢሆንም ተቋሙ ፓስፖርት ለመውሰድ ከሚመጡ ተገልጋዮች ከመስከረም 2016 ዓ.ም ጀምሮ ብር 50 (ሀምሳ ብር) ያለደረሰኝ ሲቀበልና ሲሰበስብ የቆየ ሲሆን ከታህሳስ 2016 ዓ.ም ጀምሮ ብር 100 (አንድ መቶ ብር) የሚቀበል እና የሚሰበስብ ሲሆን፤ የሚሰበሰበውም ገንዘብ በገንዘብ ሚኒስቴር እውቅና ባለው የሂሳብ ቁጥር ሳይሆን በግለሰቦች ስም በተከፈተ በሂሳብ ቁጥር 1000569485782 ገቢ እንደሚደረግ የተገለጸ መሆኑን፤
    - ተቋሙ ከ20/01/2016 ዓ.ም እስከ 18/05/2016 ዓ.ም በዋናው መ/ቤት እና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በቁጥር 85,696 (ሰማንያ አምስት ሺህ ስድስት መቶ ዘጠና ስድስት) ፓስፖርት ከእያንዳንዱ ተገልጋይ ብር 50 (ሀምሳ ብር) ያለደረሰኝ በመቀበል ያደለ ሲሆን ለዚህም በድምሩ በብር 4,284,800.00 (አራት ሚሊየን ሁለት መቶ ሰማንያ አራት ሺህ ስምንት መቶ ብር) የሰበሰበ ቢሆንም፤ በገንዘብ ሚኒስቴር በተፈቀደለት በሂሳብ ቁጥር ገቢ ያላደረገ እና ከላይ በተጠቀሰው የግለሰብ አካውንትም ገቢ ስለመደረጉ ማስረጃው ያልቀረበ መሆኑ፤
    - ተቋሙ ከታህሳስ 2016 ዓ.ም ጀምሮ የፓስፖርት እደላውን በመ/ቤቱ ሰራተኞች በተቋቋመ ሸማቾች ማህበር እንዲያድልለት በተቋሙ ግቢ ውስጥ የማደያ ቦታ በማዘጋጀት ስራውን አሳልፎ የሰጠ እና ለዚህም ለአገልግሎት ብር 100 (አንድ መቶ ብር) ማህበሩ የሚቀበልና የሚሰበስብ መሆኑ፤

- ተቋሙ የፓስፖርት እደላ ሥራው በተቋሙ ሰራተኞች ማሰራት የሚችል በመሆኑ ለሌላ አካል አሳልፎ መስጠቱ ተገቢነት የሌለው መሆኑ፤ ይሁን እና የፓስፖርት እደላ ሥራውን ለሌላ አካል አሳልፎ መስጠት ቢኖርበት እንኳን የመንግስትን የግዥ ህግ መሰረት አድርጎ ያልሰጠ መሆኑ፤

➢ ተቋሙ ቪዲቸር (Viditure) ከተባለ የግል ድርጅት ጋር እ.ኤ.አ ከመስከረም 6/2021 እስከ መስከረም 30/2024 የሚቆይ በ28/12/2013 ዓ.ም በገባው የውል ስምምነት መሰረት ከሀገር ውጭ ያሉ ነዋሪዎች ለፓስፖርት አገልግሎት ኦንላይን ሲያመለክቱ ሰነዱን አጣርቶ ወደ ኢሚግሬሽን የሚያስተላልፍ እና ፓስፖርቱ ተዘጋጅቶ ሲያልቅ ከኢሚግሬሽን ተቀብሎ ወደ ደንበኛው ተቋሙ ካወጣው የአገልግሎት ክፍያ በተጨማሪ አንድ መቶ ዶላር (100$) በማስከፈል የሚያስተላልፍ ሲሆን ይህንን ስራ ለመስራት የተመረጠበትን መስፈርት፣ የግዥ ሂደት እና ፓስፖርትን ለማሰራጨት ፈቃድ (License) ያለው መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤

- ቪዲቸር ይህንን የፓስፖርት ስራ ለመስራት በሀገሪቱ የንግድ ህግ መሰረት ንግድ ፈቃድ ያላወጣ እና በታክስ ህጉ መሰረት ግብር የማይከፍል መሆኑ፤
- የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 እና በደንብ ቁጥር 449/2011 በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት ላይ የፓስፖርት አገልግሎትን በውክልና እንደሚሰጥ የተገለጸ ነገር ባይኖርም አገልግሎቱን ቪዲቸር ለተባለው የግል ድርጅት የሰጠ መሆኑ፤

➢ የሰራተኞች የስነ ምግባር መመሪያ የተዘጋጀ ሲሆን ጸድቆ ለሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በመላክ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑንና የተቋሙ ሰራተኞች ተገልጋዩን በአክብሮትና በትህትና የማያስተናግዱ መሆኑ፤ ለማሳያ፡-

- የስነምግባር ችግር ያለባቸው የተቋሙ ሰራተኞች መኖራቸው ከበር ጥበቃ ጀምሮ አስተባባሪዎችና አገልግሎት የሚሰጡ ኦፊሰሮች ተገልጋዩን የማመናጨቅ፣ አልባሌ ቃላት የመጠቀም አልፎም የመጎተት፣ የመገፍተርና የመማታት ሁኔታዎች መኖራቸውን በኦዲቱ ወቅት በተደረገ ምልከታ የታወቀ መሆኑ፤
- ተገልጋዮች ሊያሟሉት የሚገባቸውን ማስረጃዎች እንዲያሟሉ በትህትና የማይገልጹላቸው መሆኑ፤

- ተቋሙ የፓስፖርት ግብዓቶች የግዥ ዕቅድ በወጥነት የማያቅድ እና ግዥውም በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ ስለመደረጉ የማይከታተል መሆኑ፤ ለማሳያ፡-
  - በ19/12/2015 ዓ.ም ተቋሙ ከ2013-2015 ዓ.ም የግዥ እቅድና በዕቅዱ መሰረት ግዥው መከናወኑን የሚያሳይ ማስረጃ እንዲያቀርብ ቢጠየቅም የቀረበው መረጃ የ2013 እና በ2014 ዓ.ም የግዥ እቅድ ብቻ መሆኑና የ2015 ዓ.ም እቅድ ተጠይቆ ያልቀረበ መሆኑ፤
  - ከ2013-2015 ዓ.ም የግዥ እቅድ አፈፃፀም ያልቀረበ መሆኑ፤ ግዥው በእቅድ መሰረት ስለመከናወኑ የማይከታተልና የግዥ ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በማዘጋጀት የማይገመገም መሆኑ፤
  - በደብዳቤ ቁጥር ኢሚ6/492/8949 በቀን 21/12/2012 ዓ.ም የ2013 ዓ.ም የግዥ ዕቅድን ለማሳወቅ ለመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በተላከ ደብዳቤ መደበኛ ፓስፖርት 32 እና 64 ገጽ ብዛት 1,000,000 (አንድ ሚሊየን) እና ሆሎግራፊክ ፓስፖርት ላሚኔሽን ብዛት 1,154,000.00 (አንድ ሚሊየን አንድ መቶ ሀምሳ አራት ሺህ) በጨረታ ለመግዛት የታቀደ ቢሆንም ግዥው በእቅዱ መሰረት ስለመከናወኑ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የተጠቀሱትን የኦዲት ግኝቶች ለማሻሻል የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ተቋሙ ለፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ የሚያገለግሉ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት እና መመሪያና ስታንዳርድ አዘጋጅቶ በማጸደቅ ተግባራዊ ሊያደርግና ተጠያቂነትን በማስፈን ለተገልጋዩ ቀልጣፋ አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፡፡
- ተቋሙ ከድንበርና ከጎረቤት ሃገራት መሆናቸው አጠራጣሪ የሆኑ ተገልጋዮች ሲያጋጥሙ ዜግነታቸው የሚጣራበት ወጥ የሆነ የአሰራር መመሪያ አዘጋጅቶ በማጸደቅ በመመሪያው መሰረት ቀልጣፋ አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፡፡
- ተቋሙ የአዲስ መደበኛ ፓስፖርት፣ የፓስፖርት እድሳት፣ የጠፋ ፓስፖርት እና የፓስፖርት እርማት አገልግሎት ፈላጊዎች አገልግሎቱን በምን ያህል ጊዜ እንደሚያገኙ የሚገልጽ የአገልግሎት ስታንዳርድ ሊያዘጋጅና አገልግሎቱን በወቅቱ የሚሰጥበትና ተገልጋዩን እኩል ተጠቃሚ የሚያደርግበት እንዲሁም ፓስፖርት

ለመውሰድ የሚወስደውን የቀጠሮ ጊዜ የሚያሳጥርበት ቀልጣፋና ውጤታማ አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ተቋሙ ፓስፖርት ለመውሰድ ከሚመጡ ተገልጋዮች የሚሰበስበውን ገንዘብ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያሳትመው ወይም እንዲታተም በሚፈቅደው ደረሰኝ መሰረት የአገልግሎት ክፍያውን ሊሰበስ፤ እንዲሁም ለተቋሙ በገንዘብ ሚኒስቴር በተፈቀደ አካውንት ውስጥ ገቢ በማድረግ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ህጎች መሰረት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ተቋሙ የሰራተኞች የስነ ምግባር መመሪያ አዘጋጅቶ በሚመለከተው አካል በማጸደቅ መመሪያው ተግባራዊ ስለመደረጉና ሰራተኞች ከተገልጋዩ ጋር ባላቸው የስራ ግንኙነት ተገልጋዩን በአክብሮትና በትህትና የሚያስተናግዱ ስለመሆኑ ውጤታማ የክትትልና የቁጥጥር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ተቋሙ የፓስፖርት ግብዓቶች የግዥ ዕቅድ በየአመቱ በማዘጋጀት ግዥውን በዕቅዱ መሰረት ሊያከናውንና ተግባራዊነቱን ለመገምገም የአፈጻጸም ሪፖርት አዘጋጅቶ ቀልጣፋ እና ውጤታማ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ክፍል አንድ

መግቢያ

1. በዓለም የፓስፖርት አገልግሎት ፍላጎት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋ የሚሄድ እንደ ሀገራት የኢኮኖሚና ማህበራዊ እድገት፣ የዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት፣ ብሔራዊ ፍላጎትና ስጋት አንጻር አደረጃጀቱ የሚለያይ እና ከሰዎች ነፃ ዝውውር እና እንቅስቃሴ ጋር የሚያያዝ ነው።
2. ኢሚግሬሽን በወደቦች፣ በአየርና የብስ ኬላዎች ወደ አገራት ለመግባት ወይም ለመውጣት ለሚፈልጉ ሰዎች ሕጋዊ የጉዞ ሰነዶችና የይለፍ ፈቃድ የሚሰጥ፣ ሕጋዊ እንቅስቃሴ እንዲኖር የሚቆጣጠርና ሕግ የሚያስከብር ተቋም ነው።
3. ኢሚግሬሽን በኢትዮጵያ ረጅም ዓመታት ታሪክ አለው። በሀገራችን የሚሰጡት ዋና ዋና የጉዞ ሰነዶች መደበኛ ፓስፖርት፣ ዲፕሎማቲክ ፓስፖርት፣ ሰርቪስ ፓስፖርት እና የይለፍ ሰነድ (ሊሴ ፓሴ) ናቸው።

የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት አመሰራረት

4. በ1900 ዓ.ም ከአድዋ ጦርነት በኋላ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በአዋጅ ሲቋቋሙ የኢሚግሬሽን ቢሮ በአገር ግዛት ሚኒስቴር “የጸጥታ ዳይሬክሲዮን” ተብሎ በሚጠራው ክፍል ስር አንድ ንዑስ ክፍል ሆኖ ተዋቀረ። በአፄ ምኒሊክ የተጀመረው የኢሚግሬሽን አደረጃጀት እስከ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመን ቀጥሎ በወቅቱ የነበረው የኢሚግሬሽን ስልጣንና ተግባር በአገር ግዛት ሚኒስቴርና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ስር የተደራጀ ነበር።
5. በ1966 ዓ.ም ወደ ስልጣን የመጣው የደርግ ወታደራዊ አስተዳደር “የአገር ግዛት ሚኒስቴር” የሚባለው መስሪያ ቤት በ1967 ዓ.ም “በአገር አስተዳደር ሚኒስቴር” እንዲተካ አድርጓል። አገር አስተዳደር ሚኒስቴር ከ1967-1971 ዓ.ም የቆየ ሲሆን በዚህ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት በተቋቋመ “የመረጃ ማመዛዘኛ ማዕከል” ስር “የይለፍ መምሪያ” የሚባል ዘርፍ የኢሚግሬሽን ተግባራትን ያከናውን ነበር። በ1972 ዓ.ም መጨረሻ “የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችን ስልጣንና ኃላፊነት ለመወሰን በወጣ የማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 179/1972 ወደ ዋና መምሪያ በማደግ በአገርና ህዝብ ደህንነት ጥበቃ ሚኒስቴር “የኮንስላርና የይለፍ ዋና መምሪያ” የሚል መጠሪያ ተሰጠው።

6. በ1980 ዓ.ም የመንግስትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣ አዋጅ ቁጥር 6/1980 መሰረት ቀደም ብሎ ይጠራበት የነበረው ስም ተቀይሮ በአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር "የኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ዋና መምሪያ ተብሎ እንዲቋቋም ተደርጓል። የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት በአዋጅ ቁጥር 1/1987 ስራ ላይ ሲውል የመዘዋወር መብት ትኩረት ተሰጥቶት ነበር።
7. በሕገ-መንግስቱ መሰረት የደህንነት፣ ኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 6/1987፣ የብሄራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎትን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 804/2005፣ የኢሚግሬሽን አዋጅ ቁጥር 354/1995 እና ኢሚግሬሽን አለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ተቋም እንዲሆን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ያወጣው ደንብ ቁጥር114/1997 በተለይ የመውጫ ቪዛና ዋስን በማስቀረት የዜጎች የመንቀሳቀስ መብት እንዲረጋገጥ አስችሏል።
8. ከዚህም በመቀጠል በ2011 ዓ.ም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 449/2011 የኢሚግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ ሆኖ እንዲቋቋም ተደርጓል። በ2014 ዓ.ም የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የፌደራል አካል ሆኖ ተቋቁሟል። የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ተጠሪነቱ ለብሄራዊ መረጃ ደህንነት አገልግሎት ሲሆን የሩብ፣ የግማሽ፣ የዘጠኝ ወር እና ዓመታዊ ሪፖርት ለብሄራዊ መረጃ ደህንነት አገልግሎትና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር-ቤት ያቀርባል።

የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዓላማ እና ሥልጣንና ተግባር

ራዕይ

9. ሁሉም ሰው የሚታወቅባት ኢትዮጵያ

ተልዕኮ

10. ጥራት ያለውና ደህንነቱ የተጠበቀ የጉዞ፣ የኩነት እና የብሄራዊ መታወቂያ ሰነዶችን አገልግሎት ለተጠቃሚው ተደራሽ በማድረግ የሰዎችን ማንነትና ነጻ እንቅስቃሴ ማረጋገጥ፣ ደህንነቱ የተረጋገጠ ወቅታዊ መረጃና ማስረጃን በብቃትና በጥራት

በማመንጨት እና አደራጅቶ በመያዝ ለመልካም አስተዳደር ግንባታ እና ለአገራዊ ልማት እድገት በግብዓትነት እንዲውል ማድረግ፣

ዓላማ

11. ጥራትና ተአማኒነት ያለው የኢሚግሬሽን አገልግሎት በመስጠትና የብሄራዊ መታወቂያና ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ስርዓት በመዘርጋት የብሄራዊ ደህንነትን ፣ የህግ ማስከበርንና የማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ልማት ፖሊሲዎችን መደገፍ ነው።

ሥልጣንና ተግባራት

12. የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 ላይ አገልግሎቱ በደንብ ቁጥር 449/2011 ለኢሚግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነቶች ኤጀንሲ የተሰጡ ስልጣንና ተግባራትን በስራ ላይ እንደሚያውል ተገልጿል። በዚህም መሰረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ተሰጥቶታል፡-

- ለኢትዮጵያውያንና ለውጭ አገር ዜጎች የኢሚግሬሽን አገልግሎት መስጠትና ደህንነቱን የጠበቀ ቁጥጥር ያደርጋል፣
- ለውጭ አገር ዜጎች በህግ መሰረት የኢትዮጵያ ዜግነት ይሰጣል፣ ያነሳል፣
- የኢትዮጵያ ተወላጅ ለሆኑ ውጭ ዜጎች በትውልድ አገራቸው የተለያዩ መብቶችን ተጠቃሚ ለማድረግ በወጣው አዋጅ መሰረት አገልግሎት ይሰጣል፣
- የጉዞ ሰነዶችን ያትማል፣ ያሳትማል ወይም ይሰርዛል፣
- ለኢትዮጵያውያንና ለውጭ አገር ዜጎች የአገልግሎት ክፍያ ተመን አጥንቶ ገንዘብ ሚኒስቴር ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፣
- የአገልግሎቱን አሰራር ስርዓት፣ የድርጊት መርሀ-ግብር እና የመረጃ አጠቃቀምን ያዘጋጃል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣
- የብሔራዊ ደህንነትን ለመጠበቅ እና በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ ለዜጎች የሚሰጡ ተዛማጅ አገልግሎቶችን ቀልጣፋ በማድረግ ወንጀልን ለመከላከል የሚያስችል ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣
- የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ሥልጠናዎችን ይሰጣል፣ እንዲሰጥ ያደርጋል፣
- የአገልግሎት ጥራትና ሽፋን ደረጃን ለመገምገም ለመቆጣጠርና ለመደገፍ የሚያስችል ጥናት ያካሂዳል፣ በአሰራር ሂደት የታዩ ችግሮች ላይ የመፍትሄ ሀሳብ ያቀርባል፣

- የአገልግሎቱን የመረጃ ልውውጥ ስርዓት ተስማሚ በሆነ ቴክኖሎጂ እየታገዘ የሚሰራበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣
- የተሰበሰቡ መረጃዎችን ያጠናቅራል፣ ይተነትናል፣ ሪፖርት ያዘጋጃል፣ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣
- የአገልግሎቱን ማእከላዊ መረጃ ማእከል ያደራጃል፣ የሚዘረጋው ቴክኖሎጂና የሚሰበሰበው መረጃ ለአደጋ እንዳይጋለጥ ተገቢውን ደህንነትና ጥበቃ እንዲኖር ያደርጋል፣
- የአገልግሎቱ አሰራር ስርዓትን የሚመለከቱ የፖሊሲ ሀሳቦችን ያመነጫል ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣
- ከሚመለከታቸው የፌደራልና የክልል መንግስት አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፣
- መንግስታዊ ድርጅቶች፣ ማህበራት፣ የበጎ አድራጎት ድርጅት እና የሃይማኖት ተቋማት የኢምግሬሽን፣ ዜግነትና የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ብሄራዊ መታወቂያ ስርዓት የተሟላ እንዲሆን ተገቢውን ድጋፍ እንዲያደርጉ ያስተባብራል፣ ተቀናጅቶ ይሰራል፣
- አገልግሎቱ ወቅታዊና ከቴክኖሎጂ ጋር የሚሄድ ብሄራዊ መታወቂያ ያዘጋጃል፣ ያሳትማል፣ ይሰጣል፣
- የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል ይከሰሳል፣ እና
- አላማውን ለማስፈጸም የሚያግዙ ሌሎች ተዛማች ተግባራትን ያከናውናል።

የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት መዋቅር እና የሰው ኃይል

ድርጅታዊ መዋቅር

13. የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት በዋና ዳይሬክተር የሚመራ ሆኖ ለዋና ዳይሬክተር ቀጥታ ተጠሪ የሆኑ ስድስት የስራ ክፍሎች (አንድ የዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት፣ ሶስት ስራ አስፈጻሚዎች እና ሁለት ምክትል ዋና ዳይሬክቶሬቶች) ያሉት ሲሆን ለዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት ተጠሪ የሆኑ አምስት ስራ አስፈጻሚዎች፣ ለስራ አመራር ዋና ስራ አስፈጻሚ ዘርፍ ተጠሪ የሆኑ ሰባት ስራ አስፈጻሚዎች፣ ለሲቪል ምዝገባና የማዘመን ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ተጠሪ የሆኑ ሰባት ስራ አስፈጻሚዎች እና ለኢሚግሬሽን አገልግሎት ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ተጠሪ በሆኑ አምስት ስራ አስፈጻሚዎች ተደራጅቷል። (**ድርጅታዊ መዋቅሩ በአባሪ ሶስት ተያይዟል**)

የሰው ኃይል

14. ለኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት በመዋቅር የተፈቀደው የሰው ኃይል ብዛት 2600 መሆኑን የገለጹ ሲሆን፤ በሰው ኃይል የተሸፈነ 1252 ሲሆን ከዚህ ውስጥ 94 ሰራተኞች በተለያየ ምክንያት በስራ ላይ የሌሉ መሆኑንና በጥር ወር 2016 ዓ.ም 701 (62.7%) ወንድ፣ 417 (37.2%) ሴት፣ በድምሩ 1118 ማለትም 43% ቋሚ ሰራተኞች እንዲሁም 15(60%) ወንድ፣ 10(40%) ሴት በድምሩ 25 የኮንትራት ሰራተኞች አሉት፡፡ ከነዚህ ውስጥ የቋሚ ሠራተኞች የሰው ኃይል በትምህርት ደረጃ ሲተነተን የሁለተኛ ዲግሪ 68(6%) ፣ የመጀመሪያ ዲግሪ 466 (41.6%) ፣ ኮሌጅ ዲፕሎማ 96 (8.5%) ፣ ቴክኒክና ሙያ ከደረጃ 1-4 174 (15.5%) ፣ ከ10+1 እስከ 10+3 6(0.5)፣ 10ኛ-12ኛ እና ከዚያ በታች 307 (27.4%) ሲሆን 1376 በሰው ኃይል ያልተሸፈነ ክፍት የስራ መደብ መኖሩን እንዲሁም ለጉዞ ሰነድ ምዝገባና አሰጣጥ ዳይሬክቶሬት የተፈቀደ የሰው ኃይል ብዛት 961 ሲሆን በሰው ኃይል የተሸፈነ 418 ሲሆን ከዚህ ውስጥ 38 ሰራተኞች በተለያየ ምክንያት በስራ ላይ የሌሉ መሆኑንና በጥር ወር 2016 ዓ.ም 216 (60.8%) ወንድ፣ 139 (39.1%) ሴት በድምሩ 355 ማለትም 36.9% ቋሚ ሰራተኞች እንዳሉትና 543 ማለትም 56.5% በሰው ኃይል ያልተሸፈነ የስራ መደብ መኖሩን ከሰው ኃይል መረጃ ለማወቅ ተችሏል።

የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት የፋይናንስ ምንጭ

15.የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን ከመንግሥት በጀት የሚመደብለት ሲሆን ከ2013-2015 ድረስ የተመደበለት በጀትና የወጣው ወጪ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል።

በጀት ዓመት	የተፈቀደ በጀት		ድምር	ስራ ላይ የዋለ በጀት		ድምር	ስራ ላይ የዋለ በጀት በመቶኛ	
	መደበኛ	ካፒታል		መደበኛ	ካፒታል		መደበኛ	ካፒታል
2013	527,160,207.00	64,632,248.00	591,792,455.00	433,955,923.94	29,903,777.98	463,859,701.92	82.3%	46%
2014	467,305,000.00	17,420,000.00	484,725,000.00	394,000,579.09	23,754,422.06	417,755,001.15	84.3%	136.3%
2015	803,615,480.00	19,160,000.00	822,775,480.00	483,186,989.05	11,484,554.20	422,126,697.03	60%	60%
ጠቅላላ ድምር	1,798,080,657.00	101,212,248.00	1,899,292,935.00	1,311,143,492.08	65,142,754.24	1,376,286,246.32		

በ2013 በጀት ዓመት የካፒታል በጀት ዝቅ ያለው የእቃ ግዥ ተጠይቆ በኮሮና ምክንያት አቅራቢዎቹ ባለማቅረባቸው መሆኑን እንዲሁም በ2014 ከፍ ያለው የ2013 ዓ.ም ተሰብሳቢ ሂሳብ በ2014 ዓ.ም እቃው ገቢ ሆኖ በመወራረዱ ምክንያት ፐርሰንቱ ከፍ ማለቱን በጽሁፍ አብራርተዋል፡፡

የሰነዶች ምዝገባና ሕትመት ስርጭት ዳይሬክቶሬት የፋይናንስ ምንጭ

በጀት ዓመት	የተፈቀደ በጀት		ስራ ላይ የዋለ በጀት		ስራ ላይ የዋለ በጀት በመቶኛ	
	መደበኛ	ካፒታል	መደበኛ	ካፒታል	መደበኛ	ካፒታል
2013	128,078,685.00	_	75,145,457.53	_	58.6%	_
2014	170,009,659.94	_	121,564,524.81	_	71.5%	_
2015	130,101,351.00	_	83,005,157.52	_	64%	_
ጠቅላላ ድምር	428,189,695.94		255,223,812.19			

የኦዲቱ ዓላማ

16.የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን በማረጋገጥ በሥራው ዙሪያ የሚታዩ የአሠራር ችግሮች ወይም ክፍተቶች ካሉ ችግሮቹን እና መንስኤያቸውን በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦችን ለማቅረብ ነው፡፡

ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Audit area)

17.ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ **"የፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤"** የሚል ነው፡፡

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues)

18.ከላይ በተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Audit area) ስር አራት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ተለይተዋል። እነርሱም፡-

1. የመደበኛና አስቸኳይ ፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤
2. የፓስፖርት ግብዓቶች ግዥ አፈጻጸም ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤
3. የፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ የክትትል እና የስልጠና ስርዓት መኖሩንና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፤
4. በቴክኖሎጂ የተደገፈ ውጤታማ የመረጃ አያያዝ፣ የጥገና ስርዓት እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር መኖሩንና ተግባራዊነቱን መገምገም፤

የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች

19.የኦዲት ቡድኑ የተመረጡትን አራት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችን ለመገምገም የሚያስችሉ ሰላሳ አንድ (31) የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተው ተቋሙ አስተያየት እንዲሰጥበት ተልኮ አስተያየት ተሰጥቶበታል፡፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቱ (**በአባሪ አንድ**) ተያይዟል፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

20.የክዋኔ ኦዲቱ የተከናወነው በመንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ላይ የክዋኔ ኦዲትን ለማካሄድ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአለም አቀፍ የዋና ኦዲተር መ/ቤቶች

የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (International Standards of Supreme Audit Institutions (ISSAI) መሠረት እና በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ሥልጣን ነው፡፡ኦዲቱ የተከናወነው በኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ሲሆን የሸፈነው ከ2013 ዓ.ም እስከ ጥር 2016 ዓ.ም ድረስ ያለውን በጀት ዓመት አፈፃፀም ነው፡፡

21. የኦዲት ቡድኑ የተቋሙን አሰራር የሚመለከቱ የተለያዩ አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ከ2013-2015 በጀት ዓመት ዕቅድ እና ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶች፣ የኢሚግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ የአምስት ዓመት (2014-2018 ዓ.ም) ስትራቴጂያዊ እቅድ፣ በኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት የአሰቸኳይ ፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥን ወደ መደበኛ ስርዓት ለማስገባት የተዘጋጀ የጥናት ሰነድ ነሀሴ 2014 ዓ.ም፣ ኢሚግሬሽን ከየት ወዴት ነሀሴ 2010 ዓ.ም፣ መ/ቤቱን በሚመለከት የወጡ የተለያዩ ብሮሸሮች መጽሄቶች እና የተለያዩ አግባብነት ያላቸው መረጃዎችን የከለሰ ሲሆን፣

22. ኦዲቱ የተከናወነው በተቋሙ ዋና መ/ቤት እና በናሙና በተመረጡ ስድስት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ማስረጃዎችን በመከለስ፣ የሚመለከታቸውን የስራ ኃላፊዎች ቃለ መጠይቅ በማድረግ፣ መረጃዎችን በመተንተንና በአካል ምልከታ በማድረግ ነው።

የፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ የስራ ፍሰት (Process Description)

ባለጉዳዮች በአካል ቀርበው ሲያመለክቱ

- ✓ ሰነድ ማጥራት
- ✓ ባዮ ዳታ ምዝገባ ማካሄድ
- ✓ ክፍያ ማስከፈል
- ✓ እግድና አሻራ ማጣራት
- ✓ የህትመት ፈቃድ መስጠት
- ✓ ጉድለት እርማት መስጠት

ባለጉዳዮች በኦንላይን ሲያመለክቱ

- ✓ ለእድሳት፡- በአካል መቅረብ ሳያስፈልጋቸው ሰነዳቸው በሲስተም ላይ ተጣርቶ ክፍያ በባንክ ከፍለው በቀነ ቀጠሮ ቀን ፓስፖርት ከፖስታ ቤት እንዲረከቡ ይደረጋል፣

- ✓ አዲስ ፓስፖርት እና የፓስፖርት እርማት በኦንላይን ሲያመለክቱ፡- በኦንላይን ቀጠሮ ይዘው በአካል ኢሚግሬሽን ቢሮ ቀርበው በኦንላይን የያዙት ሰነድ ትክክለኛ ስለመሆኑ ኦርጅናል አቅርበው ከተመሳከረ እና ከተጣራ በኋላ አሻራ ፊርማ እና ፎቶ ይሰጣሉ የሚስተካከል የሚታረም ፊደል ካለ እንዲታረም ይደረጋል፤

የህትመትና ስርጭት ዳይሬክቶሬት ፓስፖርትን ሲያትምና ሲያሰራጭ የሚከተለው የስራ ሂደት /Process Description/

- ✓ የፓስፖርት መረጃዎችን ምዝገባ እና ህትመትን ሲስተም የሚያገናኝ /Fetcher/ አማካኝነት መረጃዎችን ማየት፤
- ✓ ፓስፖርት ከመታተሙ በፊት ፊርማ፣ ፎቶ፣ ጾታ እና የመሳሰሉት መኖሩን የማጣራት /Validation/ ስራ ማከናወን፤ ችግር ከተገኘበት ወደ የፓስፖርት ምዝገባ መመለስ
- ✓ ፓስፖርት ላሚኔሽን ላይ ማተም /Printing/፡- ህትመት ስራ የላሚኔት ወረቀት /ላስቲክ ላይ ተገልብጠ እንዲታተም ማድረግ
- ✓ ፓስፖርት የመሰግሰግ፡- ፓስፖርት ቁጥር ከላሚኔሽን ቁጥር ጋር ተመሳሳይ ማድረግ ስራ መስራት /Bindig/
- ✓ የጠበሳ /lamination/፡- የተሰገሰገው ፓስፖርት እና ላሚኔት በ250°C ሙቀት ባለው ማሽን ይጠበሳል ከላሚኔት ላስቲክ ወደ ፓስፖርት ቡክሌት የታተመው ይጣበቃል
- ✓ ፓስፖርት በትክክል ስለመታተሙ በጥራትና ቁጥጥር (Quality Assurance/ Quality Control) በሲስተምና በአካል የፓስፖርት ቁጥር፣ የተሰጠበት ቀን እና የሚያበቃበት ቀን ይረጋገጣል
- ✓ ፓስፖርት ወደ ምዝገባ ሲስተም መመለስ /checkout/
- ✓ ፓስፖርትን በፊደል፣ በመዳረሻ ቦታ እና በጾታ መለየት /sort/
- ✓ ፓስፖርቶችን ወደ ፖስታ ቤት እና ከሀገር ውጭ ላሉ ኢትዮጵያውያን ፓስፖርት የሚሰጥ ድርጅት (Venditure / Digital INVEA) ማሰራጨት /Dispatch/
- ✓ አስቸኳይ እና በኃላፊዎች ውሳኔ የተሰጠባቸውን ፓስፖርቶች በማዕከል ለተገልጋዮች ማደል /Deliver/
- ✓ በማዕከል የሚታደሉ ከሆነ በሲስተም Delivery ይደረጋሉ፡፡

ክፍል ሁለት

የኦዲቱ ግኝቶች

ሀ/ የመደበኛና አስቸኳይ ፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤

የኢሚግሬሽን ፖሊሲ አጸድቆ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤

23. ተቋሙ የኢሚግሬሽን አሰራር ስርዓትን የሚመለከት ፖሊሲ ሊያመነጭና ለሚመለከተው አካል በማቅረብ አጸድቆ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል።

24. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች እና ከተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ ተቋሙ የኢሚግሬሽን አሰራር ስርዓት የሚመለከት ፖሊሲ አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል በማቅረብ አጸድቆ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል።

25. ስለጉዳዩ የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ተቋሙ የሚሰጠው አገልግሎት በአብዛኛው ከውጭ ዜጎች ጋር የተያያዘ በመሆኑ እስካሁን የሚጠቀመው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ፖሊሲን መሆኑን ገልጸዋል።

26. የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ይህንን ይበሉ እንጂ የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 እና በደንብ ቁጥር 449/2011 በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት የተቋሙን አሰራር ስርዓትን የሚመለከቱ የፖሊሲ ሀሳቦችን በማመንጨት ለሚመለከተው አካል እንደሚያቀርብ፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ እንደሚያደርግ የተመላከተ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል።

27. የኢሚግሬሽን አሰራር ስርዓት የሚመለከት ፖሊሲ ተዘጋጅቶ ስራ ላይ ባለመዋሉ በተቋሙ የሚከናወኑ ስራዎችን በተመለከተ በብቃት ውሳኔ እንዳይሰጥ ከማድረጉም በላይ ተቋሙ የተሰጠውን ተልዕኮ ከሀገራዊ ስትራቴጂክ ጉዳዮች ጋር አስተሳስሮ እንዳይሰራ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

ተቋሙ ለፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ የሚያገለግሉ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤

28. ተቋሙ ለፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ የሚያገለግሉ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት እና መመሪያና ስታንዳርድ አዘጋጅቶ በማጸደቅ ተግባራዊ ሊያደርግና አፈፃፀሙን ሊከታተል ይገባል።

29. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች፣ ከተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና በተደረገ የአካል ምልከታ፡-

- ተቋሙ ለፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ የሚያገለግሉ የጸደቀ እና ወቅታዊ የሆነ መመሪያና ስታንዳርድ የሌለው መሆኑ፤
- የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 እና በደንብ ቁጥር 449/2011 በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት የተቋሙን አሰራር ስርዓትና የድርጊት መርሀ-ግብር እንደሚያዘጋጅና አፈጻጸሙን እንደሚከታል የተገለጸ ቢሆንም መመሪያዎችን የማዘጋጀት እንጂ የማጽደቅ ኃላፊነት ያልተሰጠው ሆኖ ሳለ ተቋሙ ሰኔ 2015 ዓ.ም የተሻሻለ የአስቸኳይ ፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ አዘጋጅቶ በዋና ዳይሬክተር አጸድቆ (በሚመለከተው አካል ያልጸደቀ) ስራ ላይ ያዋለ መሆኑ፤ ለፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ በመላክ እንዲመዘገብ ያላደረገ መሆኑ፤
- እንዲሁም መመሪያው በግልጽ ያላስቀመጣቸው ጉዳዮች ያሉ መሆኑ ለማሳያ፡-
    - በሶስት ሀኪሞች የተፈረመ ታማሚው ግለሰብ ውጭ አገር ሄዶ እንዲታከም የታዘዘ ከህክምና ቦርድ ከመንግስትም ይሁን ከግል ሆስፒታል የተጻፈ ማስረጃ እንዲሁም ከታማሚው ጋር አብሮ የሚጓዝ አንድ ቤተሰብ አስታማሚ፣ የሚል ሲሆን ምንም እንኳን የአስታማሚው ስም በደብዳቤው ላይ ይጠቀስ የሚል በመመሪያው ባልተገለፀበት ሁኔታ ታማሚዎች ይዘው የሚመጡትን አስታማሚ ስሙ በደብዳቤ ላይ አልተጠቀሰም በማለት አገልግሎቱን የማይሰጡ መሆኑ፤
    - የውጭ የትምህርት እድል የተሰጣቸውና የትምህርት እድሉን ካመቻቸላቸው የትምህርት ተቋም የተጻፈ ደብዳቤና ሌሎች ከዚህ ጋር የተያያዙ **ደጋፊ ማስረጃዎች** የሚል ሲሆን ደጋፊ ማስረጃዎቹ ምን ምን እንደሆኑ በግልጽ ያልተቀመጠ መሆኑ፤
    - ውጭ ሀገር እቃ በማስመጣት እና በመላክ ንግድ ላይ የተሰማሩ ተቋማት ወይም በውጭ ሀገር ከሚገኙ ድርጅቶች ጋር የስራ ግንኙነት ያላቸው ከፍተኛ ግብር ከፋዮች፣ የባንክ ኤል ሲ ባለቤትና ስራ አስኪያጅ አስቸኳይ ፓስፖርት ማውጣት እንደሚችሉ የተገለጸ ቢሆንም ምን አይነት ማስረጃዎች አሟልተው መምጣት እንዳለባቸው በግልጽ ያልተቀመጠ መሆኑ፤

- በቀን 6/5/2015 የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት ባቀረበው የቅሬታ አቤቱታ ሰሚ ሁለተኛ ሩብ ዓመት ሪፖርት ላይ የሪፈራል ሆስፒታል ወረቀቶች ከጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ብቻ ካልሆነ አንቀበልም የሚሉ ባለሙያዎች መኖራቸው የተገለጸ መሆኑ፤
- የዜጎች ቻርተር አዘጋጅቶ ወደ ተግባር ለማስገባት በ2013 ዓ.ም ያቀደ ቢሆንም እስከ አሁን ድረስ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑን፤
- የፓስፖርት አገልግሎትን በተመለከተ እያንዳንዱ ተግባር የአፈጻጸም ስታንዳርድ ወጥቶለት በምን ያህል ጊዜ፣ ጥራትና መጠን መከናወን እንዳለበት ተለይቶ የማይታወቅ መሆኑን፤

ለመረዳት ተችሏል።

30.እንዲሁም ዝርዝራቸው በአባሪ 3 በተያያዘ በናሙና ተመርጠው በታዩት ቅ/ጽ/ቤቶች የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ፡-

- መመሪያና ስታንዳርድ አለመኖሩን፤ ከዋናው መ/ቤት መመሪያዎች የሚተላለፉት በቃል እንጂ በጽሁፍ የተሰጣቸው መመሪያ የሌለ መሆኑን፣ ስራዎችን እየተሰሩ ያሉት በልምድ መሆኑን፤
- የተሰጣቸው የዜጎች ቻርተር አለመኖሩን፤

ገልጸዋል።

31.ስለጉዳዩ የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ካለው የስራ ባህሪ አንፃር መመሪያ ሊኖረው ያልቻለው የኢሚግሬሽን አሰራር በተለያዩ ጊዜ የሚሰጡት አገልግሎቶች የተለያዩ በመሆናቸው መሆኑን ገልጸዋል።

32.በተጨማሪም የተቋሙ ኃላፊዎች በረቂቅ ሪፖርቱ ላይ በሰጡት አስተያየት እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና የአሰራር ስርዓቶችን በማሻሻል ጥቅም ላይ ለማዋል እንዲፀድቅ ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት የተላከ እና በሂደት ላይ ያለ መሆኑን፤ የዜጎች ቻርተር ግን አለመዘጋጀቱንና ወደፊት እንደሚሰሩበት ገልጸዋል።

33.የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች መመሪያ ሊኖረው ያልቻለው በተለያዩ ጊዜ የሚሰጡት አገልግሎቶች የተለያዩ በመሆናቸው መሆኑን ቢገልጹም መመሪያዎችን በየጊዜው

ማሻሻል የሚቻል በመሆኑ እና ተቋሙ ዋና ዋና መስፈርቶችን በመመሪያው ማካተት ስለሚቻል እንዲሁም የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት የተቋሙን አሰራር ስርዓትና የድርጊት መርሀ-ግብር እንደሚያዘጋጅና አፈፃፀሙን እንደሚከታተል የተመላከተ በመሆኑ፤ እንዲሁም ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት እንዲጸድቅ የተላከው አዋጅና ደንብ እንጂ መመሪያዎችና የአሰራር ስርዓቶች ያልተካተተ በመሆኑ፣ የተሰጠውን ምላሽ እንደ ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

34. ለፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ የሚያገለግሉ መመሪያ፣ ስታንዳርድና የዜጎች ቻርተር ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ባለመደረጉ በአሰራር ላይ የአተገባበር ችግር እንዲፈጠር፣ በጊዜ ተመጥኖ ግልጽነት ያለው ስራ እንዳይሰራና በዘፈቀደ በመስራት ተገልጋዩን ለእንግልትና ለምሬት እንዲጋለጥ ከማድረጉም በላይ ብልሹ አሰራር እንዲስፋፋ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

ተቋማዊ መዋቅር በማጥናትና በሚመለከተው አካል በማጸደቅ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤

35. የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ተቋማዊ መዋቅር በማጥናትና ለሚመለከተው አካል በማጸደቅ የተፈቀደው የስራ መደብ በሰው ኃይል ሊሟላ እና የስራ መዘርዝር (Job Description) ለሰራተኛው ሊሰጠው ይገባል።

36. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች፣ ከተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና በተደረገ የአካል ምልከታ፡-

- የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት መዋቅራዊ አደረጃጀት፣ የስራ መደቦች ምደባና የደመወዝ ስኬል ጥናት የካቲት 2011 ዓ.ም ተጠንቶ ተግባራዊ የተደረገ ቢሆንም በሚመለከተው አካል የጸደቀ ስለመሆኑ ማስረጃ አለመቅረቡ፤
- በተቋም ደረጃ በተጠናው መዋቅር 2,600 ክፍት መደቦች የተጠኑ ሲሆን 1,118 /43%/ የስራ መደቦች ብቻ በሰዉ ሃይል የተሟላ መሆኑ፤
- በደብዳቤ ቁጥር ኢሚ6/492/2834 በቀን 27/03/2016 ዓ.ም የተቋሙን መዋቅር እንዲያዘጋጁ አምስት ኮሚቴ ያዋቀሩ ቢሆንም ዝግጅቱ ምን ላይ እንደደረሰ የማይታወቅ መሆኑ፤
- ለሁሉም የስራ መደቦች የስራ መዘርዝር (Job Description) አዘጋጅቶ ያላጸደቀ እና ለሰራተኞችም ስራ ከመጀመራቸው በፊት እንዲደርሳቸው የማይደረግ መሆኑን፤

ለማወቅ ተችሏል፡፡

37.እንዲሁም በናሙና ተመርጠው በታዩት ቅ/ጽ/ቤቶች የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅና በተቋሙ ከተከለሱ ሰነዶች፡-

- ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ በሰው ኃይል ያልተሟሉ መሆኑ፤ ለማሳያ፡-
    - ሆሳዕና ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የተፈቀደለት የሰው ኃይል 23 ሲሆን አሁን ስራ ላይ ያለው የሰው ኃይል 12 ወይም 52%
    - ድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የተፈቀደለት የሰው ኃይል 24 ሲሆን አሁን ስራ ላይ ያለው የሰው ኃይል 10 ወይም 41%
    - ሰመራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የተፈቀደለት የሰው ኃይል 16 ሲሆን አሁን ስራ ላይ ያለው የሰው ኃይል 4 ወይም 25%
    - ጋምቤላ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የተፈቀደለት የሰው ኃይል 18 ሲሆን አሁን ስራ ላይ ያለው የሰው ኃይል 4 ወይም 22%

መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፤ (ለቅንጫፍ ጽ/ቤቶቹ የተፈቀደው የሰው ኃይል እና አሁን በስራ ላይ ያለው የሰው ኃይል ማስረጃ በአባሪ አራት/4 ተያይዟል)

38.ስለጉዳዩ የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ የካቲት 2011 ዓ/ም ተጠንቶ በሚመለከተው አካል የፀደቀ መዋቅራዊ አደረጃጀት፣ የስራ መደቦች ምደባና የደመወዝ ስኬል መረጃ በወቅቱ ፀድቆ መጥቶ ስራ ላይ የዋለ እንደሆነ፤ ቀድሞ የስራ ሂደቱ ሀላፊ የነበሩት ከቦታው ሲነሱ ህጋዊ ርክክብ ያልፈፀሙ በመሆኑ የተሟላ መረጃ ማግኘት አለመቻሉን፤ ሲቪል ሠርቪስ ኮሚሽን ከሚገኘው ቅጅ ላይ ኮፒ አድርገው እንዲሰጧቸው የጠየቁ መሆኑንና ምላሻቸውን በመጠባበቅ ላይ መሆናቸውን እንዲሁም በማጠቃለያ ጥያቄ ወቅት ከሲቪል ሰርቪስ ጸድቆ የመጣ የስራ መዘርዝር መኖሩን ነገር ግን በተቋሙ ስራ ልክ ባለመሆኑ ተግባራዊ አለመደረጉን ገልጸዋል።

39.ተቋማዊ መዋቅር በማጥናትና በሚመለከተው አካል በማጸደቅ የተፈቀደው የስራ መደብ በሰው ኃይል እንዲሟላ ባለማድረጉ እንዲሁም ሰራተኞች በተመደቡበት የስራ መደብ የስራ መዘርዝር እንዲሰጣቸው ባለመደረጉ ስራዎች በተወሰኑ ሰራተኞች ላይ ብቻ እንዲበዛ በማድረግ ለተገልጋዮች ቀልጣፋ አገልግሎት እንዳይሰጥ ያደረገ መሆኑ፤ እንዲሁም ማን ምን ይስራ የሚለውን ለመከታተልና ሰራተኛው ያለውን ግዴታ

እንዳያውቅና እስኪታዘዝ እንዲጠብቅ በማድረግ ስራዎች ላይ መመላለስና መገፋፋቶችን በመፍጠር ተገልጋዩን ለእንግልት ከመዳረጉም በላይ ከብልሹ አሰራር ጋር ተያይዞ ሰራተኞች ፍርድ ቤት ሲከሰሱ ምን ይሰሩ እንደነበር ለማስረዳት የስራ መዘርዝር የሌላቸው በመሆኑ ጥፋተኞች ሆነው ማስቀጣት እንዳይቻል በማድረግ ተጠያቂነትን ከማስፈን አንጻር ክፍተት ፈጥሯል።

ተቋሙ የቡክሌት ፓስፖርትን ወደ ኢ-ፓስፖርት መቀየር የሚያስችል አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤

40. ተቋሙ በዓለም አቀፉ የሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ስታንዳርድ (ICAO DOC 9303) መሰረት ጥናት በማድረግ የቡክሌት ፓስፖርትን ወደ ኢ-ፓስፖርት መቀየር የሚያስችል አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
41. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች እና ከተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ ተቋሙ በዓለም አቀፉ የሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ስታንዳርድ (ICAO DOC 9303) መሰረት ጥናት በማድረግ የቡክሌት ፓስፖርትን ወደ ኢ-ፓስፖርት መቀየር የሚያስችል አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።
42. ስለጉዳዩ የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ወደ ኢ-ፓስፖርት ለማስገባት ጥናት ተደርጎ ፕሮፖዛል ተዘጋጅቶ ወደ ሥራ ተገብቷል በማለት ገልጸዋል፡፡
43. የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ይህንን ይበሉ እንጂ የቡክሌት ፓስፖርትን ወደ ኢ-ፓስፖርት ለማስገባት የተጠናውን ጥናት እና ወደ ስራ መገባቱን የሚያሳይ ማስረጃ በተደጋጋሚ ተጠይቆ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል።
44. ተቋሙ የቡክሌት ፓስፖርትን ወደ ኢ-ፓስፖርት መቀየር የሚያስችል አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ባለማድረጉ የዶክመንቱ ደህንነት የተጠናከረ እንዳይሆን (ፎርጂድ እንዲሰራ) በማድረግ ተጽእኖ ያሳድራል።

ተቋሙ አጠራጣሪ የሆኑ ተገልጋዮች ሲያጋጥሙ ዜግነታቸው የሚጣራበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤

45. ተቋሙ ከድንበርና ከጎረቤት ሃገራት መሆናቸው አጠራጣሪ የሆኑ ተገልጋዮች ሲያጋጥሙ ዜግነታቸው የሚጣራበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- በተቋሙ ዋናው መ/ቤት ተገልጋዮች ከኢትዮጵያ ድንበር አካባቢ ከመጡ፣ በትውልድ ቦታቸው፣ በስማቸው (እስከ አያት ድረስ) እና በአነጋገር ዘይቤያቸው ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያላቸው ስለመሆኑ የሚጠረጠር ሲሆን ዜግነታቸውን ለማጣራት ትግርኛ እና ሶማሊኛ ቋንቋ ተናጋሪ ባለሙያዎች ቢሮ ቁጥር 141 እና 7 አስቀምጠ የተጠረጠረውን ተገልጋይ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ዜግነት የማጣራት ስራ ይሰራል።

46. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች፣ ከተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና በተደረገ የአካል ምልከታ፡-

- ተቋሙ ከድንበርና ከጎረቤት ሃገራት መሆናቸው አጠራጣሪ የሆኑ ተገልጋዮች ሲያጋጥሙ ዜግነታቸው የሚጣራበት መመሪያ የሌለው መሆኑ፤
- ዜግነት የማጣራት ስራው በልምድ የሚከናወን፣ ውሳኔው ዜግነትን በሚያጣራው ግለሰብ መልካም ፈቃድ ላይ የተመሰረተና ወጥ የሆነ አሰራር የማይከተል መሆኑ፤
- አንዳንድ ዜግነት የሚያጣሩ ሰራተኞች ባለጉዳዩን የሚቆጡ፣ የሚያመናጭቁ፣ የሰውን ክብር የሚነኩ፣ አግባብ ያለው ምላሽ የማይሰጡና አናስተናግድም እስከማለት የሚደርሱ መሆኑ፤
- በዋና መ/ቤት በሶማሌ ዜግነት የተጠረጠሩ ተገልጋዮችን የማጣራት ስራ የሚከናወነው ባልተሟላ የሰው ኃይል (በአንድ ባለሙያ ብቻ) መሆኑና ባለሙያው በተለያየ ምክንያት በስራ ገበታው ባይገኝ ስራው የሚቆም መሆኑ፤

ለማወቅ ተችሏል።

47. እንዲሁም በናሙና ተመርጠው በታዩት ቅ/ጽ/ቤቶች የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና የመስክ ምልከታ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ዜግነትን የሚያጣሩበት ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፤ ለማሳያ፡-

- በሆሳዕና፣ በሀዋሳ፣ በደሴ እና በጅማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ዜግነታቸው አጠራጣሪ የሆኑ ተገልጋዮች ሲያጋጥሙ ወደ ዋናው መ/ቤት በመላክ እንዲጣራ የሚያደርጉ ሲሆን በጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤት ደግሞ በክልሉ እና በወረዳ ጸጥታ ዘርፍ በኩል እንደሚጣራ የገለጹ መሆኑ፤

- በድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ዜግነት የሚያጣሩበት ስርዓት መኖሩን የገለጹ ቢሆንም በመስክ ምልከታ ወቅት ለተገልጋይ አገልግሎት እየሰጡ ስላልነበር ለማረጋገጥ አለመቻሉ፤

በኦዲቱ ወቅት ታውቋል።

48.ስለጉዳዩ የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ፤

- ከድንበርና ከጎረቤት ሃገራት ጋር የሚመጡ አጠራጣሪ የሆኑ ተገልጋዮች ሲያጋጥሙ መመሪያ ያለመኖሩ ካለው የስራ ባህሪ አንፃር ወጥ ከሆነ አሰራር እና መመሪያ ከተቀመጠ የተለያዩ ደላላዎች መመሪያውን አውቀው አለአግባብ ሊጠቀሙበት ስለሚችሉ እንደ ስራው ፀባይ እየታየ የሚወሰን መሆኑን፣ እንዲሁም ዜግነት የማጣራት ሥራ የሚከናወነው ከልምድ አንፃር ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ መሆኑን፤
- የሶማሌ ዜግነት ያላቸው ግለሰቦች ሲመጡ የሚጣራው በአንድ የሱማሊኛ ተናጋሪ የሆነበት ምክንያት አገልግሎት የሚሰጠው በዋና መስሪያ ቤት ብቻ ሲሆን ከክልሉ የሚመጡ አንዳንድ ባለጉዳዮች ብቻ በመሆኑና ሌሎች እዛው በክልላቸው አገልግሎት የሚሰጣቸው በመሆኑ እንደሆነ፤

ገልጸዋል።

49.የተቋሙ ኃላፊዎች በረቂቅ ሪፖርቱ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት አስተያየት ከፓስፖርት ጋር ተያይዞ ዜግነት የሚጣራው የትውልድ አካባቢውን ፣የትምህርት ዶክመንት እና የተለያዩ ማስረጃዎችን በመጠየቅ መሆኑንና የዜጎች መረጃ ዲጂታላይዝድ ባለመሆኑ ማመላለስ ያለ መሆኑ፤ የዜጎች መረጃ ዲጂታላይዝድ ሲደረግ አሁን ያለው እንግልት እንደሚቀንስ ገልጸዋል፡፡

50.የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ወጥ የሆነ አሰራር እና መመሪያ ከተቀመጠ የደላሎች መጠቀሚያ ስለሚሆን እንደ ስራው ፀባይ እየታየ የሚወሰን መሆኑን ቢገልጹም እንደተቋም ግልጽነት ያለውና ወጥ የሆነ አሰራር መዘርጋት ያለበት እና ሰራተኛውን በሥነምግባር በማነጽ ሚስጥራዊነቱን መጠበቅ የተቋሙ ኃላፊነት በመሆኑ ምላሻቸውን ለመቀበል ያዳግታል።

51.ተቋሙ ከድንበርና ከጎረቤት ሃገራት መሆናቸው አጠራጣሪ የሆኑ ተገልጋዮች ሲያጋጥሙ ዜግነታቸው የሚጣራበት ወጥ የሆነ አሰራር እና መመሪያ ባለመኖሩ

ተገልጋዩ እንዲንገላታ እና ውሳኔው በሚያጣራው ባለሙያ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ከማድረጉም በላይ ለብልሹ አሰራር የተጋለጠ እንዲሆን ያደርጋል።

ተቋሙ የፓስፖርት አገልግሎት ፈላጊዎች በተቀመጠላቸው መመሪያ፣ ስታንዳርድ እና የጊዜ ሰሌዳ መሰረት አገልግሎቱን ማግኘታቸውን የሚከታተል መሆኑን በተመለከተ፤

52. ተቋሙ የአዲስ መደበኛ ፓስፖርት፣ ለአስቸኳይ ፓስፖርት እና የፓስፖርት እድሳት አገልግሎት ፈላጊዎች በተቀመጠላቸው መመሪያ፣ ስታንዳርድ እና የጊዜ ሰሌዳ መሰረት አገልግሎቱን ማግኘታቸውን የሚከታተልበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

53. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች፣ ከተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና በተደረገ የአካል ምልከታ፡-

- የአዲስ መደበኛ ፓስፖርት እና የፓስፖርት እድሳት አገልግሎት ፈላጊዎች አገልግሎቱን በምን ያህል ጊዜ እንደሚያገኙ የተቀመጠ መመሪያ እና የጊዜ ሰሌዳ የሌለ መሆኑ፤
- ተቋሙ የተሻሻለ የአስቸኳይ ፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ሰኔ 2015 ዓ.ም ያዘጋጀ ቢሆንም ተገልጋዮች አገልግሎቱን በስንት ጊዜ እንደሚያገኙ የተቀመጠ የጊዜ ሰሌዳ አለመኖሩ፤

54. በተጨማሪም፤

- የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በኢሚግሬሽን፣ የዜግነትና የወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ የመደበኛ ፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ጥር 2012 ዓ.ም በተከናወነ የክዋኔ የክትትል ኦዲት ሪፖርት መደበኛ ፓስፖርት ለሚጠይቅ ባለጉዳይ በዋናዉ መምሪያ በ3 ቀናት እና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በ7 ቀናት ዉስጥ የጉዞ ሰነድ ተዘጋጅቶ እንደሚሰጥ የተገለጸ ቢሆንም አሁን ተቋሙ የአዲስ መደበኛ ፓስፖርት እና የፓስፖርት እድሳት አገልግሎት ፈላጊዎች አገልግሎቱን በምን ያህል ጊዜ እንደሚያገኙ የተቀመጠ መመሪያ እና የጊዜ ሰሌዳ የሌለው መሆኑ፤
- በኦዲቱ ወቅት የኦዲት ቡድኑ በ5/4/2016 ዓ.ም ከሰኔ 1/2015 ዓ.ም እስከ ህዳር 30/2016 ዓ.ም አስቸኳይ ፓስፖርት የተሰጣቸው ተገልጋዮች ዝርዝር ጠይቆ በዛ መሰረት በናሙና ተመርጠው ከተጠየቁ 60 የተገልጋይ ፋይሎች ውስጥ የቀረበው 46 ፋይል ብቻ መሆኑ፤

- ከታዩት 46 አስቸኳይ ፓስፖርት ከጠየቁ ፋይሎች ውስጥ 10ሩ አስቸኳይ ፓስፖርት መመሪያ ተራ ቁጥር 6 ላይ ከተገለፀው ቅድመ ሁኔታዎች ውጭ (ምንም ማስረጃ ላላመጡ፣ ቪዛ ላላቸው፣ ከግል መ/ቤት ለመጡ ሰራተኞች፣ የአውሮፕላን ቲኬት ላላቸው ወዘተ) በኃላፊዎች ፊርማ (እየተመራ) ፓስፖርት የተሰጣቸው መሆኑ፤

- የተቋሙ የኦንላይን መመዝገቢያ ድረ ገጽ ላይ ያሉ መረጃዎች ያልተሻሻሉና አብዛኛው ህብረተሰብ ሊረዳው በሚችል ቋንቋ ያልተዘጋጀ መሆኑ፤ ለማሳያ፡-
  - ድረ ገጹ በአንድ ቋንቋ (በእንግሊዝኛ) ብቻ መሆኑ፤ አብዛኛው ተገልጋይ ሊረዳው በሚችል (በሀገር ውስጥ) ቋንቋ ያልተዘጋጀ መሆኑ፤
  - ከአምስት ዓመት በታች ላሉ ህጻናት ፎቶ ማምጣት እንዳለባቸው የሚገልጽ መረጃ የሌለ ቢሆንም ልጆቻቸውን ይዘው የሚመጡ ቤተሰቦች ግን ፎቶ የሚጠየቁ መሆኑ፤
  - በድረ ገጹ ላይ የአስቸኳይ ፓስፖርት ለማውጣት መሟላት ስላለበት ቅድመ ሁኔታ ሰኔ 2015 ዓ.ም በወጣው የተሻሻለ የአስቸኳይ ፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ መሰረት ያልተሻሻለ መሆኑ፤
- የኦንላይን የፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጡ የአሰራር ስርዓት ሂደት (Standard operating procedure/SOP) የሌለ መሆኑ፤ ማን ምን እንደሚሰራ አለመታወቁና አንድ ባለሙያ በቀን ምን ያህል መመዝገብ እንዳለበት የተቀመጠ ስታንዳርድ አለመኖሩ፤
- አንድ ተገልጋይ አዲስ ፓስፖርት ለማውጣት ሲስተሙ እስከ ስድስት ወር የሚቀጥረው መሆኑ፤
- ተቋሙ ፓስፖርት በቀነ ቀጠሮ የማይሰጥ፤ በቀጠሮ ያልደረሰላቸው ተገልጋዮች ማንን መጠየቅ እንዳለባቸው የሚገለጽበት አሰራር አለመኖሩ እና አገልግሎቱን በወቅቱ ማግኘታቸውን የማይከታተል መሆኑን፤

ለማወቅ ተችሏል።

55.እንዲሁም በናሙና ተመርጠው በታዩት ቅ/ጽ/ቤቶች የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና የመስክ ምልከታ፡-

- ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አስቸኳይ ፓስፖርት በዋናው መ/ቤት ብቻ የሚሰጥ መሆኑ፤

- የፓስፖርት ህትመት እየዘገየ እና ፓስፖርት በቀጠሮ እየተሰጠ አለመሆኑን፣ ፓስፖርት ስርጭትን በተመለከተ ከፍተኛ ችግር ያለበትና እስከ አንድ ዓመት የሚቆይበት ሁኔታ መኖሩ፣
- የባለጉዳዩ የፓስፖርት ጥያቄ ከአቅም በላይ ሲሆንባቸው ወደ ዋናው መ/ቤት ቢሮ በአካል ሄደው እንዲጠይቁ እንደሚልኩና እነሱም በደብዳቤ ሲጠይቁ መልስ የማያገኙበት ሁኔታ መኖሩን፣

ገልጸዋል።

56.ስለጉዳዩ የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ የመደበኛው ፓስፖርት አገልግሎት የሚሰጠው በኦንላይን በመሆኑ የኦንላይን ሲስተሙ ራሱ የቀን ቀጠሮ የሚሰጥ መሆኑን፡፡ በቀጠሮ ቀን የማይደርስለት ተገልጋይ ቢሮ ቁጥር 3 በመሄድ ያለበትን ደረጃ ማየት የሚችል ከመሆኑም በላይ ግልጽ ላልሆኑ ጉዳዮች በተዘጋጀው የቅሬታ ክፍል ቅሬታዎችን ማቅረብ እንዲሁም በር ላይ ካለው መረጃ ክፍል መረጃ ማግኘት እንደሚችሉ ገልጸዋል፡፡

57.የተቋሙ ኃላፊዎች በመውጫ ስብሰባ ወቅት የአዲስ መደበኛ ፓስፖርት እና የፓስፖርት እድሳትን በተመለከተ አገልግሎት ፈላጊዎች አገልግሎቱን በምን ያህል ጊዜ እንደሚያገኙ የተቀመጠ መመሪያ እና የጊዜ ሰሌዳ የሌለ መሆኑንና የፓስፖርት ምዝገባ ሲስተሙ ቀጠሮ የሚሰጥ መሆኑን ፣ ሲስተሙ በሁለት ወርም ሆነ በስድስት ወር ሊቀጥራቸው እንደሚችል፣ በሌሎች ሀገራት ልምድም እስከ 2 ወር ተብሎ ይቀመጣል እንጂ በ ሁለት ወር ውስጥ ይሰጣል ተብሎ የማይቀመጥ መሆኑን፣ በዚህ ቀን ይደርሳል ብሎ ለማስቀመጥ ከመስሪያ ቤቱ ውጭ በሆኑ ምክንያቶች ሊዘገይ ስለሚችል መሆኑን መመሪያ ቢኖርም የውጭ ምንዛሪ እና የፓስፖርት ግብዓት በወቅቱ ካልቀረበ ፓስፖርት በወቅቱ መስጠት እንደማይቻልና መመሪያዉ መኖሩ ምንም እንደማይጠቅም፣ እንዲሁም አስቸኳይ ፓስፖርትን በተመለከተ በ2015 ዓ.ም የወጣ መመሪያ ቢኖርም በዛ መሰረት እየሰሩ አለመሆኑንና መመሪያዎቹን ለማሻሻል በሂደት ላይ መሆናቸውን፣ አሁን ላይ ግን ፓስፖርትና ግብዓቶችም ስላሉን አስቸኳይ ፓስፖርት ፈላጊዎች ክፍያውን እስከፈፀሙ ድረስ ፓስፖርት እንደሚሰጡ ገልጸዋል።

58.የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ይህንን ይበሉ እንጂ ፓስፖርት የሚሰጥበት የጊዜ ገደብ ስታንዳርድ መዘጋጀት ያለበት በመሆኑ፣ በቀጠሮ ቀን የማይደርስለት ተገልጋይን በተመለከተ የኦዲት ቡድኑ በ03/03/2016 ዓ.ም በክፍሉ ባደረገው ምልከታ ቢሮ ቁጥር

3 የፓስፖርት እድሳት፣ የጠፋ ፓስፖርት እና የፓስፖርት እርማት ሲኖር አገልግሎት የሚሰጥበት ክፍል መሆኑ በመታወቁ፤ ከመመሪያው ውጭ አስቸኳይ ፓስፖርት ለማግኘት በኃላፊዎች እየተመራ ካልሆነ የማይሰጥ በመሆኑ እና ኃላፊዎች ቢሮ መግባት ያልቻለ የሚመለስ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል።

59. በተቋሙ የአዲስ መደበኛ ፓስፖርት እና የፓስፖርት እድሳት አገልግሎት ፈላጊዎች አገልግሎቱን በምን ያህል ጊዜ እንደሚያገኙ የተቀመጠ መመሪያ እና የጊዜ ሰሌዳ ባለመኖሩ ግልጽ የሆነ አሰራር እንዳይኖር በማድረግ ተገልጋዮችን ለእንግልትና ላልተገባ ወጪ ከመዳረጉም በላይ ከመመሪያው ውጭ በኃላፊዎች እየተፈረመ የሚሰጠው አስቸኳይ ፓስፖርት ተገልጋዩን እኩል ተጠቃሚ የማያደርግ በመሆኑ ለብልሹ አሰራር በር ይከፍታል፡፡

ተቋሙ የፓስፖርት ምዝገባ ቀን ቀጠሮ ያሳለፉ ግለሰቦች የሚስተናገዱበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤

60. ተቋሙ የፓስፖርት ምዝገባ ቀን ቀጠሮ ያሳለፉ ግለሰቦች የሚስተናገዱበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል።

61. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች፣ ከተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና በተደረገ የአካል ምልከታ፡-

- በኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ለሚሰጡ አገልግሎቶች የአገልግሎት ክፍያ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 516/2022 የወጣ ቢሆንም የቅጣት ክፍያ ያልተካተተ መሆኑ፤
- የኢትዮጵያ ፌደራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 3 ላይ በህግ ካልተፈቀደ በስተቀር ማናቸውንም የመንግስት ገንዘብ መሰብሰብ እንደማይቻልና የመንግስት ገንዘብ እንዲቀበል ወይም እንዲሰበስብ ሥልጣን የተሰጠው ሰው ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የተቀበለውን ወይም የተሰበሰበውን የመንግስት ገንዘብ ወደተጠቃለለው ፈንድ ገቢ እንደሚያደርግ፣ ገንዘብ የተቀበለበትን እና ገቢ ያደረገበትን ደረሰኝ መዝግቦ እንደሚይዝ ቢገልጽም፤
    - ተቋሙ ገንዘብ ለመሰብሰብ መመሪያ የማውጣት ስልጣን ሳይኖረው በ21/12/2015 ዓ.ም የፓስፖርት ምዝገባ ቀን ቀጠሮ ያሳለፉ ግለሰቦችን

በቅጣት ለማስተናገድ (የቅጣት ክፍያ ተመን) መመሪያ አዘጋጅቶ በዋና ዳይሬክተር ያጸደቀ መሆኑ፤

- በመመሪያው የተተመነው ቅጣት ገንዘብ (ከ1-60 ቀናት ያሳለፉ በብር አንድ ሺህ / ብር 1000 እና ከ61-90 ቀናት ያሳለፉ ብር አንድ ሺህ አምስት መቶ/1500 ብር) የሚያስከፍል ሲሆን ገንዘቡ ለተቋሙ በገንዘብ ሚኒስቴር በተፈቀደ አካውንት ውስጥ የማይገባ መሆኑ፤
- የመንግስት የባንክ ሂሳብ የመክፈትና የመዝጋት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ስልጣን ሆኖ ሳለ ተቋሙ የሂሳብ ቁጥር 1000569485782 በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በግለሰቦች ስም ከፍቶ ገቢ የሚሰበስብ መሆኑ ዝርዝሩ እንደሚከተለው ተገልጿል፡-
  - ✓ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በደብዳቤ ቁጥር አአቅ/እአ/4575/23 በቀን 18/04/2016 ዓ.ም ለኢሚግሬሽንና ዜግነትና ወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ በላከው ደብዳቤ የሂሳብ ቁጥር 1000569485782 በቅድመአለም እና በቅድስት እና ጌትነት ስም እ.ኤ.አ በ01/09/23 አካውንት የተከፈተ ሲሆን እ.ኤ.አ በ15/09/23 ያለው የገንዘብ መጠን ብር 491,500.00 (አራት መቶ ዘጠና አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር) መሆኑን፤ እ.ኤ.አ በ01/09/23 በግለሰቦች ስም የተከፈተው አካውንት እ.ኤ.አ በ16/09/23 ወደ ኢሚግሬሽን ሰራተኞች መረዳጃ እድር የተቀየረ መሆኑ፤
  - ✓ በአጠቃላይ አካውንቱ ከተከፈተበት እ.ኤ.አ ከ01/09/2023 እስከ 29/01/2024 ድረስ በአምስት ወራት ውስጥ ብር 17,940,165.91 (አስራ ሰባት ሚሊየን ዘጠኝ መቶ አርባ ሺህ አንድ መቶ ስልሳ አምስት ብር ከ91/100) ወደ አካውንቱ ገቢ የተደረገ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ የስራ ኃላፊዎቹ በቃል እንደገለጹት ለትርፍ ሰዓት ክፍያ እና ለበዓል ለሰራተኛው ስጦታ ብር 9,324,355.76 (ዘጠኝ ሚሊየን ሶስት መቶ ሀያ አራት ሺህ ሶስት መቶ ሀምሳ አምስት ብር ከ76/100) ከመንግስት ስራ የተሰበሰበን ገንዘብ ላይ ያለገንዘብ ሚኒስቴር ፈቃድ ወጪ የተደረገ መሆኑ እና እ.ኤ.አ በ29/01/2024 ብር 8,615,810.15 (ስምንት ሚሊየን ስድስት መቶ አስራ አምስት ሺህ ስምንት መቶ አስር ብር ከ15/100) ቀሪ በአካውንቱ ላይ የሚገኝ መሆኑን፤

ለማወቅ ተችሏል።

62. እንዲሁም በናሙና ተመርጠው በታዩት ቅ/ጽ/ቤቶች የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና የመስክ ምልከታ የፓስፖርት ምዝገባ ቀን ቀጠሮ ያሳለፉ ግለሰቦች የሚስተናገዱበት የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

63. የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ ወቅት በቅጣት የሚስተናገዱት እስከ ሶስት ወር ያሳለፉ ተገልጋዮች መሆናቸውንና ክፍያው በትርፍ ሰዓት ገብተው ለሚያስተናግዱ ባለሙያዎች እንደሚውልና የበለጠ የተቋሙ ዋና ዳይሬክተሮች ምላሽ ቢሰጡበት በማለት የገለጹ ቢሆንም ስለጉዳዩ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ምላሽ አልሰጡም።

64. የተቋሙ ዋና ዳይሬክተሮች በረቂቅ ሪፖርቱ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት አስተያየት የተከፈተው የባንክ ሂሣብ ቁጥር በህግ የተቋቋመው የተቋሙ የሠራተኞች ማኅበር የባንክ ሂሣብ ቁጥር መሆኑን፣ ከደንበኞች በቅጣት መልክ የሚሰበሰበው ገንዘብ በማህበሩ አካውንት ገቢ እየተደረገ የሚገኝ እና ከሸማቾች ማኅበር ጋር ተገቢውን ትስስር በመፍጠር እየሰራ ያለ መሆኑ ማኅበሩም ህጋዊ እውቅና እና የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ያለው መሆኑን፣ ደንበኛውም የተወሰነውን ቅጣት ክፍሎ ለመስተናገድ ፈቃደኛ በመሆኑ፣ ለረዥም ጊዜ የተከማቸውን ፖስፖርት ወደ ደንበኛ ለማድረስ በመደበኛ ሰዓትና በመንግስት በጀት ብቻ ለማስተናገድ ስለማይቻል ሠራተኞችን በቅዳሜና እሁድ እንዲሁም በበዓላት ቀን በማስገባት የትርፍ ሰዓት ሂሣብ እየከፈለ የታተሙ ፓስፖርቶችን ለደንበኞች እያሰራጨ የሚገኝ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

65. የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ይህንን ይበሉ እንጂ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በቀን 15 ሐምሌ 2014 ዓ.ም በቁጥር ሲሰከ30/ጠ13/882/14 የትርፍ ሰዓት ስራ ክፍያ መመሪያን በተመለከተ ለተቋሙ በደብዳቤ የላከና በዛም መሰረት የትርፍ ሰዓት ክፍያ መክፈል የሚችሉ በመሆኑ ፤ የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 እና በደንብ ቁጥር 449/2011 በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት ለኢትዮጵያውያንና ለውጭ አገር ዜጎች የአገልግሎት ክፍያ ተመን አጥንቶ ገንዘብ ሚኒስቴር ሲፈቀድ ተግባራዊ እንደሚያደርግ የተመላከተ በመሆኑና፣ የሸማቾች ማህበር የመንግስትን ስራ የማይሰራ በመሆኑ ከቅጣትና ከአገልግሎት ገቢ የሚገኘው ገንዘብ የመንግስት ገንዘብ በመሆኑ

በመንግስት የፋይናንስ ህግና ስርዓት መሰረት ተግባራዊ መደረግ ያለበት በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል።

66. ተቋሙ የፓስፖርት ምዝገባ ቀን ቀጠሮ ያሳለፉ ግለሰቦች የሚስተናገዱበት ህጋዊ ፋይንንስ ስርዓትን ተከትሎ የሚሰራበትን የአሰራር ስርዓት ባለመዘርጋቱ የሀገሪቱን የፋይናንስ ህግ ከመጣሱም በላይ መንግስት ማግኘት ያለበትን ገቢ በማሳጣት የሀገር ሀብት ያለአግባብ እንዲባክን በር ይከፍታል፡፡

ተቋሙ የፓስፖርት ስርጭትን ለማካሄድ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤

67. ተቋሙ ከመልዕክት አስተላላፊ ተቋማት ጋር የፓስፖርት ስርጭትን ለማካሄድ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል።

68. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶችና ከተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ፤

- ተቋሙ ከኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት ጋር በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገራት የፓስፖርት ስርጭትን ለማካሄድ መጋቢት 03/ 2013 ዓ.ም የተገባ ውል ቢኖርም በደብዳቤ ቁጥር ኢ.ሚ6/492/15461 በቀን 20/12/2015 የኢሚግሬሽን ዜግነት አገልግሎት ለፖስታ አገልግሎት ድርጅት በላከው ደብዳቤ አገልግሎቱን አቋርጧል፡፡ ከመስከረም 2016 ዓ.ም እስከ ህዳር 30/2016 ዓ.ም ድረስ ተቋሙ እራሱ ፓስፖርት የማደል ስራውን ሲያከናውን የቆየ ቢሆንም ከታህሳስ 2016 ዓ.ም ጀምሮ በኢሚግሬሽን ሸማቾችና ህብረት ስራ ማህበር ውል በመዋዋል የፓስፖርት እደላ ስራውን በተቋሙ ግቢ ውስጥ እንዲያድሉ ያደረገ መሆኑ፤
- የኢትዮጵያ ፌደራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ ማናቸውም የመንግስት ገንዘብ የሚሰበሰበው ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያሳትመው ወይም እንዲታተም በሚፈቅደው ደረሰኝ ብቻ እንደሆነ የተገለጸ ቢሆንም ተቋሙ ፓስፖርት ለመውሰድ ከሚመጡ ተገልጋዮች ከመስከረም 2016 ዓ.ም ጀምሮ ብር 50 (ሀምሳ ብር) ያለደረሰኝ ሲቀበልና ሲሰበስብ የቆየ ሲሆን ከታህሳስ 2016 ዓ.ም ጀምሮ ብር 100 (አንድ መቶ ብር) የሚቀበል ሲሆን፤ በገንዘብ ሚኒስቴር እውቅና ባለው የሂሳብ ቁጥር ሳይሆን በግለሰቦች ስም በተከፈተ በሂሳብ ቁጥር 1000569485782 ገቢ እንደሚደረግ የተገለጸ መሆኑን፤

- ተቋሙ ከ20/01/2016 ዓ.ም እስከ 18/05/2016 ዓ.ም በዋናው መ/ቤት እና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በቁጥር 85,696 (ሰማንያ አምስት ሺህ ስድስት መቶ ዘጠና ስድስት) ፓስፖርት ከእያንዳንዱ ተገልጋይ ሀምሳ ብር ያለደረሰኝ በመቀበል ያደለ ሲሆን ለዚህም በድምሩ በብር 4,284,800 (አራት ሚሊየን ሁለት መቶ ሰማንያ አራት ሺህ ስምንት መቶ ብር) የሰበሰበ ሲሆን፣ በገንዘብ ሚኒስቴር በተፈቀደለት በሂሳብ ቁጥር ገቢ ያላደረገ እና ከላይ በተጠቀሰው የግለሰብ አካውንትም ገቢ ስለመደረጉ ማስረጃው ያልቀረበ መሆኑ፤ **(የፓስፖርት ስርጭትን የሚያሳይ ሰንጠረዥ በአባሪ ስድስት ተያይዟል)**
- ተቋሙ ከታህሳስ 2016 ዓ.ም ጀምሮ የፓስፖርት እደላውን በመ/ቤቱ ሰራተኞች በተቋቋመ ሸማቾች ማህበር እንዲያድልለት በተቋሙ ግቢ ውስጥ የማደያ ቦታ በማዘጋጀት ስራውን አሳልፎ የሰጠ እና ለዚህም ለአገልግሎት ብር 100 (አንድ መቶ ብር) ማህበሩ የሚቀበልና የሚሰበስብ መሆኑ፤
- ተቋሙ የፓስፖርት እደላ ሥራው በተቋሙ ሰራተኞች ማሰራት የሚችል በመሆኑ ለሌላ አካል አሳልፎ መስጠቱ ተገቢነት የሌለው መሆኑ፤ ይሁን እና የፓስፖርት እደላ ሥራውን ለሌላ አካል አሳልፎ መስጠት ቢኖርበት እንኳን የመንግስትን የግዥ ህግ መሰረት አድርጎ ያልሰጠ መሆኑ፤

- ተቋሙ ቪዲቸር (Viditure) ከተባለ የግል ድርጅት ጋር እ.ኤ.አ ከመስከረም 6/2021 እስከ መስከረም 30/2024 የሚቆይ በ28/12/2013 ዓ.ም በገባው የውል ስምምነት መሰረት ከሀገር ውጭ ያሉ ነዋሪዎች ለፓስፖርት አገልግሎት አንላይን ሲያመለክቱ ሰነዱን አጣርቶ ወደ ኢሚግሬሽን የሚያስተላልፍ እና ፓስፖርቱ ተዘጋጅቶ ሲያልቅ ከኢሚግሬሽን ተቀብሎ ወደ ደንበኛው ተቋሙ ካወጣው የአገልግሎት ክፍያ በተጨማሪ አንድ መቶ ዶላር (100$) በማስከፈል የሚያስተላልፍ ሲሆን ይህንን ስራ ለመስራት የተመረጠበትን መስፈርት፣ የግዥ ሂደት እና ፓስፖርትን ለማሰራጨት ፈቃድ (License) ያለው መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤
  - ቪዲቸር ይህንን የፓስፖርት ስራ ለመስራት በሀገሪቱ የንግድ ህግ መሰረት ንግድ ፈቃድ ያላወጣ እና በታክስ ህጉ መሰረት ግብር የማይከፍል መሆኑ፤
  - የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 እና በደንብ ቁጥር 449/2011 በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት ላይ የፓስፖርት አገልግሎትን

በውክልና እንደሚሰጥ የተገለጸ ነገር ባይኖርም አገልግሎቱን ቪዲቸር ለተባለው የግል ድርጅት የሰጠ መሆኑ፣

- ተቋሙ በደንብ ቁጥር 449/2011 በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት መሰረት ለኢትዮጵያውያንና ለውጭ አገር ዜጎች የኢሚግሬሽን አገልግሎት መስጠትና ደህንነቱን የጠበቀ ቁጥጥር ያደርጋል ቢልም ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ መያዝ ያለበት የግለሰቦች መረጃን ያለምንም የህግ አግባብ (የመንግስትን የግዥ መመሪያን ሳይከተል) ቪዲቸር ለተባለ ለግል ድርጅት አሳልፎ የሰጠ መሆኑ፤

- የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 እና በደንብ ቁጥር 449/2011 ላይ ተቋሙ መደበኛ ስራውን ለሶስተኛ ወገን በማስተላለፍ ማሰራት ስለመቻሉ ያልተገለፀ/ያልተቀመጠ/ በመሆኑ የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት፣ ቪዲቸርም ሆነ የተቋሙ የሸማቾች ማህበር ፓስፖርትን ማሰራጨት/ማደል ስራዎችን መስጠቱ የህግ መሰረት የሌለው መሆኑን፤

ለማወቅ ተችሏል፡፡

69. የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ቪዲቸርን በተመለከተ የመልእክት አስተላላፊ ፈቃድ (License) የሌለው መሆኑንና በምን መልኩ እንደገባ ማስረጃ እስከ 19/04/2016 ዓ.ም እንደሚያቀርቡ በማጠቃለያ ጥያቄ ወቅት የገለጹ ቢሆንም ማስረጃው ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ቀን ድረስ ያልቀረበ መሆኑ፤ እንዲሁም ፓስፖርት ለመውሰድ ከሚመጡ ተገልጋዮች ሀምሳ ብር (50) ያለደረሰኝ የሚቀበሉ መሆኑን በተመለከተ ምላሽ አልሰጡም።

70. የተቋሙ ኃላፊዎች በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት አስተያየት ፓስፖርት በፊት የሚያሰራጨዉ የኢትዮጲያ ፖስታ አገልግሎት መሆኑን ከፖስታ ቤት ጋር ዉሉን አቋርጠው አሁን ለተቋሙ ሸማቾች ማህበር የማሰራጨት ስራዉን በውል ተሰጥቶት ስራዉን እየተሰራ እንደሚገኝ፣ በደንብ ቁጥር 449/2011 ላይ በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት ተቋሙ ውል ይዋዋላል በተጨማሪም አላማውን ለማስፈጸም የሚያግዙ ሌሎች ተዛማች ተግባራትን ያከናውናል የሚል ስላለ ተቋሙ የፓስፖርት ማደል ስራዉን ለሶስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠቱ ህጉን የተከተለ መሆኑን፣ ይህን ስራ ሲሰሩ የተቋሙን ዋና ስራ አሳልፈው አለመስጠታቸውን ከምዝገባ እስከ ህትመት ድረስ

ያለውን ሳይሆን ፓስፖርት ማደሉን አሳልፌው የሰጡ መሆኑንና ቅጣቱም ሆነ አገልግሎቱ በፍላጎት ላይ የተመሰረተ እንጂ በግዳጅ አለመሆኑን፣ የቪዲቸር ፓስፖርት ስርጭት ስራው የተሰጠበት መንገድ አግባብ አይደለም እንጂ ስራን አሳልፎ መስጠት ግን ተቋሙ መብት ያለው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

71. የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ይህንን ፖስፖርት የማደሉ ሥራ በተቋሙ ሊሰራ ይገባል የሚል አቋም ያለን ቢሆንም ተቋሙ ለሌላ አካል መስጠት አለብኝ ብሎ ካለ እንኳን የመንግስትን የግዥ ስርዓት በተከተለ መልኩ መከናወን ያለበት መሆኑ፣ ፖስፖርት የማደል ስራውም ሆነ ለፖስፖርት አገልግሎት አመልካቾች በወቅቱ ባለመስተናገዳቸው ምክንያት በቅጣት ማስተናገድ መቻል ስራው የተቋሙ በመሆኑ እና ከነዚሁ የሚመነጨው ገቢ ከመንግስት ሥራ የሚመነጭ ገቢ በመሆኑ ከህግ አግባብ ውጭ የመንግስትን ገንዘብ መሰብሰቡ አግባብ ባለመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል።

72. ተቋሙ ከመልክት አስተላላፊ ተቋማት ጋር የፓስፖርት ስርጭትን ለማካሄድ የሚያስችል ህጋዊ መሰረት ያለው የአሰራር ስርዓት ባለመዘርጋቱ የግለሰብ መረጃዎች ደህንነት ለስጋት የሚዳረግ መሆኑ፣ እንዲሁም የህገሪቱ የግዥ፣ የንግድ እና የታክስ ህጎች እንዲጣሱ ከማድረጉም በላይ አገራችን ከታክስ ማግኘት የምትችለውን የውጭ ምንዛሬ እንዳታገኝ አድርጓል፡፡

ተቋሙ የፓስፖርት የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት፣ ተደራሽነትና ሽፋን ደረጃን በመገምገም፣ ጥናት ማድረጉን በተመለከተ፤

73. ተቋሙ የፓስፖርት የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት፣ ተደራሽነትና የሽፋን ደረጃ ለመገምገም፣ ለመቆጣጠርና ለመደገፍ የሚያስችል ጥናት በማካሄድ በአሰራር ሂደት የታዩ ችግሮች ላይ የመፍትሄ ሀሳብ የሚሰጥበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

74. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች፣ ከተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና በተደረገ የአካል ምልከታ፡-

- በኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት የአስቸኳይ ፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥን ወደ መደበኛ ስርዓት ለማስገባት ነሀሴ 2014 ዓ.ም የተዘጋጀ ሰነድ ቢኖርም ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፤

- የተገልጋይና የአገልግሎት ሰጪ እርካታን በተመለከተ ግንቦት በ2013 ዓ.ም ጥናት የተከናወነ ሲሆን በምክረሀሳቡ መሰረት ማሻሻያዎች ስለመደረጋቸው ክትትል ያልተደረገ መሆኑ፤
- በ2015 በጀት ዓመት ተቋማዊ የመልም አስተዳደር እቅድ ላይ የተደራሽነት ችግር መኖሩንና ተገልጋዩ የፓስፖርት አገልግሎት ለማግኘት ጊዜውንና ገንዘቡን ሰውቶ ከሩቅ ቦታ ወደ ማዕከል እንደሚመጣ የተገለጸ መሆኑ፤
- በተቋሙ የአምስት ዓመት (2014-2018 ዓ.ም) ስትራቴጂክ እቅድ ላይ በ2013 ዓ.ም አስራ ሁለት /12 ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የነበሩ ሲሆን በ2014 ዓ.ም ሁለት/2 ፣ በ2015 ዓ.ም ሶስት/3 እና በ2016 ዓ.ም አምስት/ 5 በድምሩ 10 አዲስ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን በመክፈት የፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጡን ተደራሽ ለማድረግ የታቀደ ቢሆንም ያልተተገበረ መሆኑን፤

ለማወቅ ተችሏል፡፡

75. ስለጉዳዩ የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ አዳዲስ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን በመክፈት አገልግሎቱን ተደራሽ ለማድረግ ከፍተኛ የሆነ በጀት የሚፈልግና ለተቋሙ የሚመደበው በጀት ተግባራቱን ለማከናወን የሚያስችል አለመሆኑ እና የተባባሪ ባለድርሻ አካላቶች አለመገኘት ዋነኛ ምክንያቶች ቢሆንም ካለው የተገልጋዮች ፍላጎት አንጻር በሚቀጥሉት ዓመታቶች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላቶች ጋር በመነጋገር ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ እንደሆነ ገልጸዋል።
76. የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ይህንን ቢሉም ቅርንጫፉን ለመክፈትና አገልግሎቱን ለማስፋት በጀት ጠይቀው የተከለከሉ ስለመሆናቸው ማስረጃ ያላቀረቡ በመሆኑ የሰጡትን መልስ ለመቀበል ያዳግተናል፡፡
77. ተቋሙ የፓስፖርት የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት ጥናት የተካሄደ ቢሆንም የተደራሽነትና ሽፋን ደረጃን ለመገምገም፣ ለመቆጣጠርና ለመደገፍ የሚያስችል ጥናት በማካሄድ ተግባራዊ ባለማድረጉ በአሰራር ሂደት የታዩ ችግሮች መፍትሄ እንዳይሰጣቸው፤ አገልግሎቱን በማስፋት ተደራሽ እንዳይሆን በማድረግ ተገልጋዮችን ለአላስፈላጊ ወጪና እንግልት ከመዳረጉም በላይ ተቋሙ የያዘውን የጉዞ ሰነዶችን አገልግሎት ለተጠቃሚው ተደራሽ የማድረግ ተልእኮ እንዳያሳካ ያደርጋል፡፡

ተቋሙ የፓስፖርት አገልግሎትን ለመስጠት የቢሮው አቀማመጥ የስራ ፍሰትን ባማከለ መልኩ መደራጀቱን በተመለከተ፤

78. በተቋሙ የፓስፖርት አገልግሎትን ለመስጠት የቢሮው አቀማመጥ የስራ ፍሰትን ባማከለ መልኩ ሊደራጅና መጠለያ ያለው ወረፋ መጠበቂያ እንዲሁም መጸዳጃ ሊኖር ይገባል፡፡

79. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች፣ ከተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና በተደረገ የአካል ምልከታ፡-

- በዋናው መ/ቤትም ሆነ በናሙና ተመርጠው በታዩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የፓስፖርት አገልግሎትን ለመስጠት ክፍሎቹ ጠባብና የቢሮው አቀማመጥ የስራ ፍሰትን ባማከለ መልኩ ያልተደራጀ፣ የስራ ክፍሎቹን አገልግሎት የሚገልጽ ጠቋሚ ምልክት የሌለው መሆኑ፤
- በ2015 በጀት ዓመት ተቋማዊ የመልካም አስተዳደር እቅድ ላይ ተገልጋዩ አገልግሎቱን ለማግኘት የት መሄድ እንደሚገባው በግልጽ እንዲያውቅ ያልተደረገ እና በተለያዩ ቢሮዎች የሚመላለስበት ሁኔታ እንዳለ የተገለጸ መሆኑ፤
- ከተገልጋዩ ቁጥር ጋር ተመጣጣኝ መጠለያ ያለው ወረፋ መጠበቂያ የሌለውና አገልግሎት ፈላጊዎች በዝናብና በጸሀይ ሜዳ ላይ የሚሰለፉበት ሁኔታ መኖሩ፤ ለማሳያ፡-
    - በዋና መ/ቤት መጠለያ ያለው ወረፋ መጠበቂያ ቢኖርም ካለው የተገልጋይ ቁጥር ጋር ተመጣጣኝ አለመሆኑ፤ ለአስቸኳይ ፓስፖርት ፈላጊዎች መጠለያ ያለው ወረፋ መጠበቂያ አለመኖሩና በጸሀይና በዝናብ የሚሰለፉት ሁኔታ መኖሩ፤

ፎቶ1 በዋና መ/ቤት ፓስፖርት አገልግሎት ፈላጊዎች በጸሀይ ሜዳ ላይ ተሰልፈው ሲጠባበቁ

- **በናሙና ተመርጠው በታዩ ሀዋሳ፣ ሆሳዕና እና ጅማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ምንም አይነት ወረፋ መጠበቂያ የሌለ መሆኑና ተገልጋዮች ሜዳ ላይ ተሰልፈው የሚጠብቁ መሆኑ፤**

ፎቶ2 በሆሳዕና እና በጅማ ቅ/ጽ/ቤት መጠለያ ያለው ወረፋ መጠበቂያ ባለመኖሩ ፓስፖርት አገልግሎት ፈላጊዎች ሜዳ ላይ ተሰልፈው

- በደብዳቤ ቁጥር ጅማ ኢ/ቅ/ጽ/ቤት 00/575 በቀን 25/12/2014 ዓ.ም የጅማ ኢሚግሬሽን ቅ/ጽ/ቤት ለጉ/ሰ/ዝ/አስ/ዳይሬክቶሬት በላኩት ደብዳቤ የባለጉዳይ ማረፊያ አዳራሽ ወድቆ ባለጉዳይ ላይ ጉዳት ያደረሰ መሆኑን፤

- ደረጃውን የጠበቀና የሰራተኛውንና የተገልጋዩን ቁጥር ያገናዘበ መጸዳጃ ቤትን በተመለከተ፤
  - በዋናው መ/ቤትም ሆነ በናሙና ተመርጠው በታዩ ሀዋሳ፣ ሆሳዕና እና ጅማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መጸዳጃ ቤቶቹ በር የሌላቸው፣ ንጽህና የሌላቸው እና የተገልጋዩን ቁጥር ያላገናዘበ መሆኑ፤
  - በጅጅጋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ለተገልጋዮች የተዘጋጀ መጸዳጃ ቤት የሌለ መሆኑን፤

ፎቶ3 በዋና መ/ቤት በራቸው የተገነጣጠለ እና ንጽህና የሌላቸው መጸዳጃ ቤቶች

ፎቶ4 በሀዋሳ እና ጅማ ቅ/ጽ/ቤቶች በር እና ንጽህና የሌላቸው መጸዳጃ ቤቶች

ለማወቅ ተችሏል፡፡

80.ስለጉዳዩ የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ

- አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ የቢሮ አደረጃጀቱ ምቹ ያለመሆን የመፀዳጃ ክፍሎቹ ከደረጃ በታች መሆናቸውና ለደንበኞች አገልግሎት በቂ ስፍራ ባለመኖሩ የለውጥ አመራሩ ቅድሚያ ሰጥቶ ምቹ የአገልግሎት መስጫ ቦታ በማዘጋጀት አገልግሎቱን ለማመዘን ዝግጅቱን በማጠናቀቅ ላይ መሆኑን፣
- ኦዲት በተደረገባቸው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሀዋሳ፣ ሆሳዕናና ጅማ የደንበኞች ወረፋ መያዣ ሼድ የሌላቸው ቢሆንም ሁሉንም ቅርንጫፎች በአንድ በጀት ዓመት ግንባታ ለማከናወን የበጀት ውስንነት ስለሚኖር በተያዘው ፕሮግራም ባለፉት ዓመታት በሌሎች ቅርንጫፎች በአዳማ፣አሶሳና ጋምቤላ የደንበኞች ወረፋ መያዣ ሼድ የተገነባ መሆኑን በሌላ በኩል በኦዲቱ ከታዩት የጅማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ቢሮና ሼድ ግንባታ ውል ተከናውኖ አሁን ላይ ግንባታው በመጠናቀቅ ላይ መሆኑን፣

ገልጸዋል፡፡

81.በተቋሙ የፓስፖርት አገልግሎትን ለመስጠት የቢሮው አቀማመጥ የስራ ፍሰትን ባማከለ፣ አገልግሎት ሰጪ ክፍሎችን ጠቋሚ ምልክት በማድረግ ገላጭ በሆነ መልኩ ባለመደራጀቱና መጠለያ ያለው ወረፋ መጠበቂያ እንዲሁም ንጹህና ከተገልጋዩ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ መጸዳጃ ቤት ባለመኖሩ ተገልጋዮች የተመሩበትን ቢሮ በመፈለግ

ጊዜያቸውን እንዲያባክኑ፣ በዝናብና በጸሀይ ወረፋ በመጠበቅ እንዲጉላሉ ከማድረጉም በላይ የሰራተኛውና የተገልጋዩ ጤና እና ደህንነት እንዳይጠበቅ ያደርጋል፡፡

ተቋሙ የሰራተኞች የስነ ምግባር መመሪያና የብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል የሚያስችል አሰራር በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤

82.በተቋሙ የሰራተኞች የስነ ምግባር መመሪያ ተዘጋጅቶ ተጠያቂነት ያለበት አሰራር በመዘርጋት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

83.ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች፣ ከተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና በተደረገ የአካል ምልከታ፡-

- የሰራተኞች የስነ ምግባር መመሪያ የተዘጋጀ ሲሆን ጸድቆ ለሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በመላክ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑንና
- የተቋሙ ሰራተኞች ተገልጋዩን በአክብሮትና በትህትና የማያስተናግዱ መሆኑ፤ ለማሳያ፡-
    - የስነምግባር ችግር ያለባቸው የተቋሙ ሰራተኞች መኖራቸው ከበር ጥበቃ ጀምሮ አስተባባሪዎችና አገልግሎት የሚሰጡ ኦፊሰሮች ተገልጋዩን የማመናጨቅ፣ አልባሌ ቃላት የመጠቀም አልፎም የመጎተት፣ የመገፍተርና የመማታት ሁኔታዎች መኖራቸውን በኦዲቱ ወቅት በተደረገ ምልከታ የታወቀ መሆኑ፤
    - እንዲሁም በ2015 በጀት ዓመት ተቋማዊ የመልካም አስተዳደር እቅድ ላይ ከተገልጋይ ጋር በቀጥታ የሚገናኙ ሰራተኞች ከተገልጋዩ ጋር በሚኖራቸው መስተጋብር በትህትና ከመቅረብ ይልቅ የማመናጨቅና የመሳደብ ባህሪ እንደሚያሳዩ የተገለጸ መሆኑ፤
    - ተገልጋዮች ሊያሟሉት የሚገባቸውን ማስረጃዎች እንዲያሟሉ በትህትና የማይገልጹላቸው መሆኑ፤
    - በቀን 6/5/2014 የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት ባቀረበው የቅሬታ አቤቱታ ሰሚ ሁለተኛ ሩብ ዓመት ሪፖርት ላይ አንዳንድ ቡድን መሪዎችና ባለሙያዎች የተገልጋይን ማስረጃ በጥንቃቄ ሳያጤኑ ማስረጃ ነጥቀው ከግቢ የሚያባርሩ፣ በዋናው ማስረጃቸው ላይ አላስፈላጊ ጽሁፍ መጻፍና መሰረዝ፤ ዶክሜንቱን እንዳይጠቀም የሚያደርጉና እንደዚህ አይነት ከመርህ ውጭ የሆኑ ስራዎች በየቀኑ እንደየሚታዩ የተገለጸ መሆኑ፤

- ተቋሙ በፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የሚታዩ የብልሹ አሰራር ችግሮችን ለመከላከል የሚያስችል አሰራር ያልዘረጋና የተጠያቂነት አሰራሩ ያልተጠናከረ (ብልሹ አሰራር ሲፈጽሙ የተገኙ የተቋሙ ሰራተኞችን ተከታትሎ እርምጃ መውሰድና ማስወሰድ ላይ ክፍተት ያለ) መሆኑ፤
  - የመልካም አስተዳደር እቅድ ከ2013-2015 ዓ.ም የተዘጋጀ ቢሆንም አፈጻጸሙን በተመለከተ ሪፖርት ተዘጋጅቶ የማይገመገም መሆኑ፤
  - በቀን 6/5/2014 የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት ባቀረበው የቅሬታ አቤቱታ ሰሚ ሁለተኛ ሩብ ዓመት ሪፖርት ላይ ትክክለኛ ማስረጃ ለሌለውና ህጋዊ ላልሆነ ተገልጋይ ፓስፖርት የሚሰጥበት ሁኔታ እንዳለ የተገለጸ መሆኑ፤
  - ከ2014 ዓ.ም በፊት በዋና መ/ቤትና በቅርንጫፎች በዲስፕሊን ጉድለት ምክንያት የተከሰሱ የተቋሙ ሰራተኞች ክሱ ያለበት ሁኔታ ሳይታወቅና ውሳኔ ሳይሰጣቸው ጉዳያቸው ተንጠልጥሎ ያለ አስራ ሁለት (12) ሰራተኞች መኖራቸው፤ **(ዝርዝራቸው በአባሪ ስምንት ተያይዟል)**
  - ከህዳር 2013 ዓ.ም እስከ ሰኔ 2013 ዓ.ም በህገወጥ መንገድ ፓስፖርት እንዲታተም ያደረጉ ሀያ ሶስት (23) ሰራተኞች በዲሲፕሊን የተከሰሱ ሲሆን አስራ ሁለቱ (12) በሙስና ተከሰው ጉዳያቸው በጠ/ዐ/ህግ አማካኝነት በህግ ሂደት ውሳኔ የተሰጣቸው ቢሆንም አስራ አንዱ (11) ግን ክሳቸው ምን ላይ እንደደረሰ የማይታወቅ መሆኑን፤ **(ዝርዝራቸው በአባሪ ዘጠኝ ተያይዟል)**

ለማወቅ ተችሏል፡፡

84.ስለጉዳዩ የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ

- የፀደቀ የሥነ ምግባር መመሪያው ለቅርንጫፍ ጽ/ቤት የተላከ መሆኑን ቀደም ሲል በተሰጠው ምላሽ የተላከበትን ደብዳቤ ቅጂ አባሪ አድርገው የላኩ መሆኑንና ተግባራዊነቱን ክትትል ለማድረግ ቀጣይ በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ድንገተኛ ቁጥጥር ለማድረግ ፕሮግራም የተያዘ መሆኑን ፤
- የዲሲፕሊን ችግር ያለባቸው ሠራተኞችን በሚመለከት በመስሪያ ቤቱ የዲሲፕሊን ኮሚቴ ጉዳቸው የሚታይ እና የእርምት እርምጃ እየተወሰደ እንደሚገኝ፤

- ከህዳር 2013 ዓ.ም እስከ ሰኔ 2013 ዓ.ም በህገወጥ መንገድ ፖስፖርት እንዲታተሙ ያደረጉት የ23 ሰራተኞች የዲስፕሊን ክስ ውስጥ የ11 ሠራተኞች በብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት አማካኝነት የተያዙ እና ክስ የተመሰረተባቸው ሲሆን የክስ ሂደትን በተመለከተ የሰውና የሰነድ ማስረጃ ባለመገኘቱ አቃቤ ህግ ክስ እንዲቋረጥ ማድረጉን፤

ገልጸዋል፡፡

85.የተቋሙ ኃላፊዎች በረቂቅ ሪፖርቱ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት አስተያየት የሰራተኞች ስነምግባርን በተመለከተ በዲሲፒሊን ችግር የታሰሩ ፍርድ የተፈረደባቸዉ ሰዎች መኖራቸውን፤ በር ላይ አንዳንድ ችግር ስናይ የመቀያየር ነገር መኖሩን፤ የሰራተኛውን የባህሪ ችግር ያመጣዉ ተገልጋዩ የተቀጠረዉም ያልተቀጠረዉም በመምጣቱና የሰዉ መብዛት መሆኑን አሁን ግን ቢሮ ለመቀየር ማሰባቸውን እና ያኔ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን እንደሚጠቀሙና በካሜራ እንደሚቆጣጠሩ፣ የአገልጋይነት ክፍተት አሁንም መኖሩንና ብዙ የስነምግባር ችግር ያለባቸው ሰራተኞች መኖራቸውንና በቅርቡ በሚሰራው ሪፎርም የሚስተካከል መሆኑን ገልጸዋል።

86.የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች የፀደቀ የሥነ ምግባር መመሪያው ለቅርንጫፍ ጽ/ቤት የተላከ መሆኑንና የተላበከትን ደብዳቤ ቅጂ አባሪ አድርገው የላኩ መሆኑን ቢገልጹም ማስረጃው ለኦዲት ቡድኑ ያልደረሰ በመሆኑ፤ የ11 ሠራተኞች በብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት አማካኝነት የተያዙ እና ክስ የተመሰረተባቸውን የክስ ሂደት በተመለከተ የሰውና የሰነድ ማስረጃ ባለመገኘቱ አቃቤ ህግ ክስ እንዲቋረጥ አድርጓል ቢሉም ክሱ መቋረጡን የሚያሳይ ማስረጃ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

87.ተቋሙ የሰራተኞች የስነ ምግባር መመሪያ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ባለማድረጉና በፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የሚታዩ የብልሹ አሰራር ችግሮችን ለመከላከል የሚያስችል ተጠያቂነት ያለበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ባለማድረጉ በተቋሙ የስነምግባር ጥሰቶች እንዲበራከቱና ከተገልጋይ ጋር በሚፈጠር ግንኙነት ሰራተኞች ያላግባብ ለመጠቀም እንዲሞክሩ በር የሚከፍት ከመሆኑም በላይ ተቋሙ መልካም ገጽታ እንዳይኖረው ያደርጋል፡፡

በተቋሙ የተገልጋይ ቅሬታ መፍቻ ስርዓት መኖሩና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤

88. በተቋሙ የተገልጋይ ቅሬታ መፍቻ ስርዓት ሊኖርና የሚቀርቡ ቅሬታዎችም በወቅቱ የሚፈቱበት የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል።

89. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች፣ ከተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና በተደረገ የአካል ምልከታ፡-

- በተቋሙ ዋና መ/ቤት በአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት ስር የቅሬታ ሰሚ ቢሮ 138 ቁጥር ቢኖርም የሚቀርቡ ቅሬታዎች ስለመፈታታቸው የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤
- የቅሬታ አቤቱታ ሰሚ ሁለተኛ ሩብ ዓመት ሪፖርት በቀን 6/5/2014 ዓ.ም ለዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት እና ለምክትል ዋና ዳይሬክተሮች የተላከ ሲሆን በሪፖርቱ በወሩ ከቀረቡ 85 ቅሬታዎች ውስጥ 68 ቱን መፍታት እንደተቻለ ቢገለጽም የቀረበውን ቅሬታ እና ቅሬታው መፈታቱን የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፡-
- የቅሬታ አቀራረብ አሰራር ስርዓት (ቅሬታው የሚጣራበት እና የሚሄድበት ሂደት የሚወስደው ጊዜ፣ ቅሬታ የቀረበባቸው ሰዎች የሚወሰድባቸው እርምጃ ወዘተ) ምን መምሰል እንዳለበት የሚገልጽ አሰራር አለመኖሩ፤
- በ2015 ዓ.ም እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በተቋሙ አገልግሎት አሰጣጥ ባለመርካት 750 ቅሬታ የቀረበ መሆኑንና ከቀረበው ቅሬታ ዉስጥ ለ 679 (90.5%) ቅሬታዎች ተገቢዉን ምላሽ መስጠቱን ቢገልጹም የቀረበውን ቅሬታ እና ቅሬታው መፈታቱን የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ
- በ06/06/2016 ዓ.ም የኦዲት ቡድኑ በቅሬታ ክፍል በመገኘት ባደረገው የአካል ምልከታ ቅሬታ ክፍሉ ከተቋቋመበት ዓላማ ውጭ የአስቸኳይ ፓስፖርት ፈላጊዎች በመመሪያው መሰረት በአስቸኳይ እንዲስተናገዱ መረጃቸው የሚጣራበት ክፍል የሆነ መሆኑን፤
    - በክፍሉ የተገልጋዩን ቅሬታ በአግባቡ አዳምጠውና መረጃውን አጣርተው የሚያስፈልገውን መረጃ እንዲያመጡ የማያደርጉ መሆኑ፤
    - በአገልግሎቱ ደስተኛ የሆኑ ባለጉዳዮችን ብቻ አስገብተው መዝገብ ላይ አስተያየታቸውን እንዲያሰፍሩ የሚያደርጉ መሆኑን፤

ለማወቅ ተችሏል፡፡

90.በተጨማሪም በናሙና ተመርጠው በታዩት ቅ/ጽ/ቤቶች የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና የመስክ ምልከታ ራሱን ችሎ የተደራጀ ቅሬታ የሚቀርብበት ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፣ ተገልጋዮች ከተለያዩ ክልሎች መጥተው ዋናው መ/ቤት ቅሬታ የሚያቀርቡበት ሁኔታ መኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

91.ስለጉዳዩ የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ቅሬታ ክፍል ከተቋቋመበት ዓላማ አንጻ ፓስፖርት ይሰጠኝ ጥያቄ ኖሯቸው ያልተስተናገዱትን ተቀብሎ በተቀመጠው መመሪያ መሠረት ማግኘት ሲገባቸው ያላገኙ መሆናቸውን ማስረጃዎችን አይቶ፣ አጣርቶና መርምሮ ለውሳኔ ለኃላፊ ማቅረብ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

92.የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ይህንን ይበሉ እንጂ በዋናነት የአስቸኳይ ፓስፖርት ፈላጊ ተገልጋዮች መረጃ ተጣርቶ የሚመራበት ቢሮ 101 ቁጥር እንጂ በቅሬታ ክፍል ባለመሆኑ ምላሻቸውን ለመቀበል ያዳግታል።

93.በተቋሙ የተገልጋይ ቅሬታ መፍቻ ስርዓት በቅ/ፅ/ቤቶች ራሱን ችሎ ያልተደራጀ እና በዋና መ/ቤት ደግሞ የተቋቋመበትን ተግባር የማይፈጽም በመሆኑ፤ የሚቀርቡ ቅሬታዎችም በምን ያህል ጊዜ መፈታት እንዳለባቸው የሚገልጽ ስታንዳርድ የሌለው በመሆኑ ተገልጋዩ በተቋሙ ላይ ያለውን አመኔታ እንዲያጣ፣ ከክልሎች በመመላለስ ለአላስፈላጊ ወጪ እንዲዳረጉና በአገልግሎት አሰጣጡ እንዳይረኩ ከማድረጉም በላይ በተቋሙ ተጠያቂነት እንዳይሰፍን ያደርጋል፡፡

ለ/ የፓስፖርት ግብዓቶች ግዥ አፈጻጸም ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤

በተቋሙ የፓስፖርት ግብዓቶች የግዥ ዕቅድ ስለመኖሩና ግዥው በውሉ መሰረት መከናወኑን በተመለከተ፤

94.ተቋሙ የፓስፖርት ግብዓቶች የግዥ ዕቅድ ሊኖረውና ግዥውም በዕቅዱ እና በተገባው ውል መሰረት ተግባራዊ ስለመደረጉ የሚከታተልበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

95.ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች እና ከተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ፡-

- ተቋሙ የፓስፖርት ግብዓቶች የግዥ ዕቅድ በወጥነት የማያቅድ እና ግዥውም በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ ስለመደረጉ የማይከታተል መሆኑ፤ ለማሳያ፡-

- በ19/12/2015 ዓ.ም ተቋሙ ከ2013-2015 ዓ.ም የግዥ እቅድና በዕቅዱ መሰረት ግዥው መከናወኑን የሚያሳይ ማስረጃ እንዲያቀርብ ቢጠየቅም የቀረበው መረጃ የ2013 እና በ2014 ዓ.ም የግዥ እቅድ ብቻ መሆኑና የ2015 ዓ.ም እቅድ ተጠይቆ ያልቀረበ መሆኑ፤
- ከ2013-2015 ዓ.ም የግዥ እቅድ አፈፃፀም ያልቀረበ መሆኑ፤ ግዥው በእቅድ መሰረት ስለመከናወኑ የማይከታተልና የግዥ ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በማዘጋጀት የማይገመገም መሆኑ፤
- በደብዳቤ ቁጥር ኢ.ሚ.6/492/8949 በቀን 21/12/2012 ዓ.ም የ2013 ዓ.ም የግዥ ዕቅድን ለማሳወቅ ለመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በተላከ ደብዳቤ መደበኛ ፓስፖርት 32 እና 64 ገጽ ብዛት 1,000,000 (አንድ ሚሊየን) እና ሆሎግራፊክ ፓስፖርት ላሚኔሽን ብዛት 1,154,000.00 (አንድ ሚሊየን አንድ መቶ ሀምሳ አራት ሺ.ህ) በጨረታ ለመግዛት የታቀደ ቢሆንም ግዥው በእቅዱ መሰረት ስለመከናወኑ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤
- በደብዳቤ ቁጥር ኢ.ሚ.6/492/32384 በቀን 27/12/2013 ዓ.ም የ2014 ዓ.ም የግዥ ዕቅድን ለማሳወቅ ለመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በመሸኛ ደብዳቤ የተላከ ቢሆንም የፓስፖርት ደብተርና ላሚኔት ለመግዛት ያልታቀደ መሆኑ፤

- ከንብረት ክፍል ተጠይቀው ከቀረቡ የፓስፖርት ቡክሌት እና ላሚኔት ገቢ እና ወጪ ማስረጃዎች
  - እ.ኤ.አ በ2020 እና በ2022 መደበኛ ፓስፖርት ገቢ ያልተደረገ ሲሆን እ.ኤ.አ በ2021፣ 2023 እና 2024 በአጠቃላይ ብዛት 1,296,800 (አንድ ሚሊየን ሁለት መቶ ዘጠና ስድስት ሺ.ህ ስምንት መቶ) መደበኛ ፓስፖርት ገቢ ተደርጎ እ.ኤ.አ ከ2020 እስከ 2023 በአጠቃላይ ብዛት 1,812,551 (አንድ ሚሊየን ስምንት መቶ አስራ ሁለት ሺ.ህ አምስት መቶ ሀምሳ አንድ) ወጪ መደረጉን ከቀረበው ማስረጃ የታወቀ መሆኑ፤
  - እ.ኤ.አ በ2020 ላሚኔት ገቢ ያልተደረገ ሲሆን እ.ኤ.አ ከ2021 እስከ 2024 በአጠቃላይ ብዛት 1,320,000 (አንድ ሚሊየን ሶስት መቶ ሀያ ሺ.ህ) ላሚኔት ገቢ ተደርጎ እ.ኤ.አ ከ2020 እስከ 2024 በአጠቃላይ ብዛት 792,400 (ሰባት

መቶ ዘጠና ሁለት ሺህ አራት መቶ) ላሚኔት ወጪ መደረጉን ከቀረበው ማስረጃ የታወቀ መሆኑ፤ **(ገቢና ወጪ የተደረጉ ፓስፖርትና ላሚኔት ዝርዝር በአባሪ አስር ተያይዟል)**

- ተቋሙ ከሁለት ድርጅቶች (እስራኤል ሀገር ካለ ሱፐርኮም /SUPERCOM ከተባለ ድርጅት ላሚኔት ለማስመጣት እና ፈረንሳይ ካለ አይዴሚያ/ IDEMIA ከተባለ ድርጅት ፓስፖርት ለማስመጣት) ጋር የውል ስምምነት እንዳለው የገለጹ ቢሆንም ዋናው የውል ስምምነት ሰነድ ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረበ መሆኑ፤
- እ.ኤ.አ በሰኔ 10/2021 ተቋሙ ሱፐርኮም ከተባለው ድርጅት የላሚኔት ግዥ ለመፈጸም በተገባው ስምምነት ላይ ተጨማሪ ውል ቁጥር 2 (ADDENDUM NO.2 to the agreement for procurement of secure blank documents) የተዘጋጀ ሲሆን ሱፐርኮም የተባለው ድርጅት ብቻ የፈረመበት እና በውል ሰጪው በኩል ያልተፈረመ መሆኑ፤
- እ.ኤ.አ በመስከረም 2022 ተቋሙ ሱፐርኮም ከተባለው ድርጅት የላሚኔት ግዥ ለመፈጸም በተገባው ስምምነት ላይ ተጨማሪ ውል ቁጥር 3 (ADDENDUM NO.3 to the agreement for procurement of secure blank documents) የተዘጋጀ ሲሆን ሁለት ሚሊየን ላሚኔት (2,000,000) በአንድ ሚሊየን ስድስት መቶ ሰማንያ ሺህ የአሜሪካ ዶላር /USD1,680,000 ከ4-8 ሳምንት ውስጥ ለማስገባት የተፈረመ ሲሆን በስምምነቱ መሰረት ግዥው ስለመፈጸሙ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤
- ተቋሙ እ.ኤ.አ የካቲት 5/2016 ፈረንሳይ ካለ አይዴሚያ/ IDEMIA ከተባለ ድርጅት ፓስፖርት ለማስመጣት ለተገባው የውል ስምምነት ማሻሻያ ቁጥር 3 እ.ኤ.አ 25/11/2022 የተፈረመ ሲሆን በስምምነቱ አንድ ሚሊየን አራት መቶ ሰባ ሺህ (1,470,000) መደበኛ ፓስፖርት፣ ሀያ ሺህ (20,000) ሰርቪስ ፓስፖርት እና አስር ሺህ (10,000) ዲፕሎማቲክ ፓስፖርት በ30 ሳምንታት ውስጥ ማስገባት እንደሚጀመር የሚገልጽ ቢሆንም በስምምነቱ መሰረት ግዥው ስለመፈጸሙ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑን፤

ለማወቅ ተችሏል፡፡

96.ስለጉዳዩ የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ ወቅት እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ

- የመጀመሪያውን የውል ስምምነት ማግኘት አለመቻሉንና የመጀመሪያው ድርጅት አይዴሚያ አለመሆኑንና አይዴሚያ ድርጅቱን ሲገዛው በስሩ ያሉ ደንበኞችን ጭምር መሆኑን፤ ሌሎቹን ስምምነቶች በተመለከተ ስምምነቱ በሁለቱም በኩል የተፈረመ መሆኑንና ግዥው መፈጸሙን ገልጸው ማስረጃውን እስከ 19/04/2016 ዓ.ም እንደሚያቀርቡ በማጠቃለያ ጥያቄ ወቅት የገለጹ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ማስረጃው ያልቀረበ መሆኑን፤
- የ2015 ግዥ እቅድ በኢጇፒ የታቀደ ሲሆን የፓስፖርት እቅድ በጥቅል ህትመት ተብሎ የታቀደ መሆኑን፤ የግዥ አፈፃፀም በተመለከተ ለእቅድ ክትትል ዳይሬክቶሬት በወቅቱ ያቀረቡ መሆኑን፤
- በዓመታዊ እቅድ የፓስፖርት ግዥ የታቀደው የሥራ ክፍሎች እቅድ እንዲያዝላቸው ፍላጎት ሲቀርብ ሲሆን ኤልሲ ከመክፈት ጀምሮ ግዥውን እስከመፈፀም ቀድሞ በነበሩ በዋና ኃላፊዎች ይከናወን ስለነበር ያልተገዛበት ምክንያት ቀድሞ በነበሩ ኃላፊዎች በኩል መልስ ቢሰጥበት፤
- የፓስፖርት ግዥ ውል በተመለከተ በተመሳሳይ ግዥ ዳይሬክቶሬት ምንም አይነት ተሳትፎ ያልነበረው መሆኑን፤

ገልጸዋል፡፡

97. የተቋሙ ኃላፊዎች በረቂቅ ሪፖርቱ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት አስተያየት የግዥ እቅድን በተመለከተ የ2016 ዓ.ም የግዥ ዕቅድ መኖሩንና ከዚህ በፊት ስለነበረው ግን እንደማያውቁ ገልጸዋል።

98. የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች የ2015 የፓስፖርት ግዥ እቅድ በጥቅል ህትመት ተብሎ በኢጇፒ የታቀደ መሆኑን ቢገልጹም የኦዲት ቡድኑ በተቋሙ ካሉ ባለሙያዎች ጋር የኢጇፒ ሲስተም ላይ በመግባት ባደረገው ምልከታ የፓስፖርት ግብዓት ያልታቀደ በመሆኑ፤ ግዥው በእቅድ መሰረት ስለመከናወኑ ኃላፊነት ወስደው ተረክበው እየሰሩ ያሉ ኃላፊዎች ምላሽ መስጠት ሲገባቸው ኤልሲ ከመክፈት ጀምሮ በዋና ኃላፊዎች መከናወኑንና ቀድሞ በነበሩ ኃላፊዎች በኩል መልስ ቢሰጥ ተብሎ የተሰጠውን ምላሽ በኦዲቱ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

99. ተቋሙ የፓስፖርት ግብዓቶች የግዥ ዕቅድና የውል ስምምነት አዘጋጅቶ ግዥውም በዕቅዱና በውል ስምምነቱ መሰረት ባለመፈጸሙ የፓስፖርት እጥረት እንዲያጋጥም

በማድረግ ተገልጋዩ ህብረተሰብ ቀልጣፋ አገልግሎት እንዳያገኝና እንዲንገላታ፣ ፓስፖርት ለማግኘት ረዥም ጊዜ እንዲጠብቅ እና የመንግስት ገንዘብ እንዲባክን ከማድረጉም በላይ ለብልሹ አሰራር በር ይከፍታል።

ተቋሙ ለፓስፖርት ግብዓቶች ግዥ የግዥ መስፈርት ማዘጋጀቱን በተመለከተ፤

100. ተቋሙ ለፓስፖርት ግብዓቶች ግዥ የግዥ መስፈርት ሊያዘጋጅና ግዥውም በተዘጋጀው መስፈርት መሰረት ስለመከናወኑ የሚያረጋግጥበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

101 ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች እና ከተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ፡-

- ተቋሙ ለፓስፖርት ግብዓቶች ግዥ የግዥ መስፈርት ቢኖርም ግዥው በተዘጋጀው መስፈርት መሰረት ስለመከናወኑ የሚያረጋግጥበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፤
- በቀን 6/5/2014 ዓ.ም የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት ባቀረበው የቅሬታ አቤቱታ ሰሚ ሁለተኛ ሩብ ዓመት ሪፖርት ላይ የስቲከርና የላሚኔት ጥራት ጉድለት በመኖሩ ተገልጋዮች ሲወስዱት በቀላሉ የሚላላጥና ከጉዞ እንደሚስተጓጎሉ የተገለጸ መሆኑ፤
- ከ10 ዓመት በፊት የፓስፖርት ግብዓት ወደ ሀገር ሲገባ በአይን፣ በዩቪ እና በላብራቶሪ ይታይ እንደነበርና አሁን ግን ይህ ስርዓት አለመኖሩን፤

ገልጸዋል፡፡

102 ስለጉዳዩ የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ከዚህ በፊት በነበረው ፓስፖርት ግዥ በተመለከተ ኤልሲ ከመክፈት ጀምሮ ግዥ ዳይሬክቶሬት ምንም ተሳትፎ ያልነበረው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

103 ተቋሙ የፓስፖርት ግብዓቶች ግዥ በተዘጋጀው የግዥ መስፈርት መሰረት ስለመከናወኑ የሚያረጋግጥበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ባለማድረጉ ተገልጋዩን ህብረተሰብ ጊዜ እና ጉልበት እንዲባክን ከማድረጉም በላይ ተቋሙን ለድጋሚ ህትመት በመዳረግ ኪሳራ ያስከትላል።

ሐ/ የፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ የክትትል እና የስልጠና ስርዓት መኖሩንና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፤

ተቋሙ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ማደራጀቱን በተመለከተ

104 ተቋሙ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን የፓስፖርት አገልግሎትን ለመስጠት በሚያስችል መልኩ (በግብዓትና በቴክኒክ) ሊያደራጅና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

105 ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች፣ ከተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና በተደረገ የአካል ምልከታ፡-

- ተቋሙ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን የፓስፖርት አገልግሎትን ለመስጠት በሚያስችል መልኩ (በግብዓትና በቴክኒክ) ያላደራጀ መሆኑ፤
- ተቋሙ በ18/03/2016 ዓ.ም ከ2013-2015 ዓ.ም ድረስ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በደብዳቤ ድጋፍ እንዲደረግላቸው የጠየቁበትና በዚሁ መሰረት ድጋፍ መደረጉን የሚያሳይ ማስረጃ እንዲያቀርብ ተጠይቆ ያላቀረበ መሆኑ፤ ቅ/ጽ/ቤቶችም ድጋፍ በሚጠይቁበት ወቅት ምላሽ የማይሰጣቸው መሆኑ፤ ለማሳያ፡-
    - በደብዳቤ ቁጥር ደኢ.ሚ/1084/2016 በቀን 2/2/2016 ዓ.ም የደሴ ኢሚግሬሽን ቅ/ጽ/ቤት ለጉዞ ሰነዶች አሰጣጥ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ለጄነሬተር ጥገና የሚያስፈልጉ መለዋወጫ እቃዎች፣ የኢና (የፓስፖርት ምዝገባ ሲስተም) ኮምፒዉተርና መለዋወጫ፣ ሰፋ ያለ የሰነድ ማጥራትና የባለጉዳይ ማረፊያ አዳራሽ እና የግቢ አጥር እንዲሟሉ የጠየቁ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ምላሽ ያላገኙ መሆኑ፤
    - በደብዳቤ ቁጥር ሆሰኢ.ሚ/342/15 በቀን 14/09/15ዓ.ም የሆሳዕና ኢሚግሬሽን ቅ/ጽ/ቤቶች ለሰነዶች ምዝ/አሰ/ዳይሬክቶሬት የኦንላይን አገልግሎት እንዲፈቀድ የጠየቁ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ምላሽ ያላገኙ መሆኑ፤
    - ደብዳቤ ቁጥር ጅማኢ/ቅ/ጽ/ቤት001/595 በቀን 02/05/2015 ዓ.ም የጅማ ኢሚግሬሽን ቅ/ጽ/ቤት ለጉ/ሰ/ዝ/አሰ/ዳይሬክቶሬት የተበላሹ ኮምፒዩተር እንዲሰራላቸው የጠየቁ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ምላሽ ያላገኙ መሆኑን፤

ለማወቅ ተችሏል፡፡

106 የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ ወቅት የኢና (የፓስፖርት ምዝገባ ሲስተም) ኮምፒውተር ከገበያ ውጭ የሆነና መለዋወጫዎቹ ገበያ ላይ የሌሉ መሆኑ፤ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ላይ የአይቲ አደረጃጀትና የሰው ኃይል ባለመኖሩ እንደ አሰራር ችግር መሆኑን፤ ሙሉ መረጃ የመያዝ ክፍተት መኖሩን ገልጸዋል፡፡

107 ተቋሙ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን የፓስፖርት አገልግሎትን ለመስጠት በሚያስችል መልኩ (በግብዓትና በቴክኒክ) ባለማደራጀቱ በዕቅድ የተያዙ ተግባራት በሚፈለገው ልክ እንዳይከናወኑ ከማድረጉም በላይ አገልግሎት አሰጣጡ ቀልጣፋ እንዳይሆን ያደርጋል።

ተቋሙ ዕቅድ በማዘጋጀት አፈጻጸሙን በወጥነት መገምገሙን በተመለከተ፤

108 ተቋሙ ስትራቴጂክ ዕቅድ በማዘጋጀት በስትራቴጂክ ዕቅዱ መሰረት ዓመታዊ ዕቅድ ሊያዘጋጅና ዳይሬክቶሬቶችም (የስራ ክፍሎችም) በተቋሙ ዕቅድ መሰረት የስራ ክፍላቸውን ዕቅድ አዘጋጅተው አፈጻጸማቸውን በወጥነት የሚከታተሉበት፣ የሚገመግሙበትና ግብረመልስ የሚሰጡበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል።

109 በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች፣ ከተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና በተደረገ የአካል ምልከታ፡-

- ተቋሙ ስትራቴጂክ ዕቅድ እንደሚዘጋጅ፣ በስትራቴጂክ ዕቅዱ መሰረትም ዓመታዊ ዕቅድ እንደሚዘጋጅና ዳይሬክቶሬቶችም (የስራ ክፍሎችም) በተቋሙ ዕቅድ መሰረት የስራ ክፍላቸውን ዕቅድ እንደሚያዘጋጁ ለማወቅ ተችሏል፡፡

110 ይሁን እንጂ

- የስራ ክፍሎቹ አፈጻጸማቸውን በወጥነት የሚከታተሉበት፣ የሚገመግሙበትና ግብረመልስ የሚሰጡበት ስርዓት አለመኖሩን፤
- ማኔጅመንቱም በሚያደርጋቸው ስብሰባዎች ቃለ-ጉባኤ የማይያዝና በዘርፍ አፈጻጸማቸውን የሚገመግሙበትና ግብረመልስ የሚሰጡበት ስርዓት አለመኖሩን፤

ለማወቅ ተችሏል፡፡

111 በተጨማሪም በናሙና ተመርጠው በታዩት ቅ/ጽ/ቤቶች የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና የመስክ ምልከታ፡-

- በሀዋሳ፣ ሆሳዕና፣ ጅማ እና ድሬዳዋ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ዓመታዊ ሪፖርት የሚልኩ ቢሆንም በዋናው መ/ቤት ተደራጅቶ የማይያዝ መሆኑን፤

- ጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤት እቅድ አለመኖሩንና የየቀኑን ሪፖርት እንደሚልኩ፤

ገልጸዋል።

112 ስለጉዳዩ የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ

- የተቋሙ ዳይሬክቶሬቶች እቅዳቸውን ሲያዘጋጁ የግምገማ፣ ሪፖርት ዝግጅትና ድጋፍ እና ክትትል አግባባቸውን በእቅዳቸው እንዲያካትቱ እና የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርታቸውን ከፈጻሚዎቻቸው ጋር እንዲገመግሙ አቅጣጫ የሚሰጥበት እና ክትትል የሚደረግበት አሰራር ያለ መሆኑን፣
- በተቋም ደረጃ ወጥነት ያለው የዘርፍ ግምገማ የማድረግ ክፍተቶች የነበሩ መሆኑ እና በዘርፍ ደረጃ የሚያዙ ቃለ ጉባ-ኤዎች የሌሉ መሆናቸውን፤
- በተቋማዊ የእቅድ ግምገማ መርሃ ግብር እና አልፎ አልፎ የሚደረጉ የማኔጅመንት ስብሰባ ቃለ-ጉባኤዎችን ለክዋኔ ኦዲት ቡድኑ ያቀረብን ሲሆን ወጥነት ያለው የማኔጅመንት ስብሰባ ቃለ-ጉባኤ የመያዝ ክፍተት የነበረ መሆኑ ትክክል ቢሆንም አሁን ላይ በቋሚነት ራሱን የቻለ ቃለ ጉባኤ በማዘጋጀት ማንኛውንም የማኔጅመንት ስብሰባዎች በቃለጉባኤ ማስደገፍ ስራዎች እየተሰሩ እንደሆነ፤
- እያንዳንዱ የተላከለትን ወርሃዊ እና የሩብ ዓመት ሪፖርቶች እንዲሁም የ6 ወር እና ዓመታዊ ሪፖርቶች እያዘጋጁ እንደሚያቀርቡ፡፡

ገልጸዋል፡፡

113 የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች አልፎ አልፎ የሚደረጉ የማኔጅመንት ስብሰባ ቃለ-ጉባኤዎችን ለክዋኔ ኦዲት ቡድኑ ያቀረቡ መሆኑን ቢገልጹም ምንም አይነት የማኔጅመንት ቃለጉባኤ ያልቀረበ በመሆኑ ምላሻቸውን ለመቀበል ያዳግታል፡፡

114 የተቋሙ የስራ ክፍሎች በተቋሙ ዕቅድ መሰረት የስራ ክፍላቸውን ዕቅድ አዘጋጅተው አፈጻጸማቸውን በወጥነት የሚከታተሉበት እንዲሁም ማኔጅመንቱም በሚያደርጋቸው ስብሰባዎች ቃለ-ጉባኤ በመያዝ በዘርፍ አፈጻጸማቸውን የሚገመግሙበትና ግብረመልስ የሚሰጡበት የአሰራር ስርዓት ባለመኖሩ በተቋሙ ያሉ ችግሮች በወቅቱ እንዳይለዩ፣ በተቋሙ አቅም የሚፈቱ ጉዳዮች እንዳይፈቱና በማኔጅመንት ስብሰባ የተሰጡ አቅጣጫዎች ስለመፈጸማቸው ክትትል ለማድረግ እንዳይቻል ያደርጋል፡፡

ተቋሙ የፓስፖርት መረጃ ህትመት ጥራትና ቁጥጥር ስራን መስራቱን በተመለከተ፤

115 ተቋሙ የፓስፖርት መረጃ ህትመት ጥራትና ቁጥጥር ስራን በመስራት ፓስፖርት በአለም አቀፍ ስታንዳርድ መሰረት መታተሙን የሚከታተልበትና የሚቆጣጠርበት አሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

116 ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች፣ ከተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና በተደረገ የአካል ምልከታ፡-

- በቀን 6/5/2014 የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት ባቀረበው የቅሬታ አቤቱታ ሰሚ ሁለተኛ ሩብ ዓመት ሪፖርት ላይ በጉዞ ሰነዶች ላይ የሚሞሉ መረጃዎች እድሜ፣ ጾታ፣ የትውልድ ቦታ ወዘተ ስህተት የሚፈጠር መሆኑና ተገልጋዩ ይህንን ስህተት ለማስተካከል ለእንግልት የሚዳረግ እንደሆነ የተገለጸ መሆኑ፤
- ተቋሙ የፓስፖርት መረጃ ህትመት ጥራትና ቁጥጥር ስራን የሚሰራው (Passport reader and 2d bar code) የተባለ መሳሪያ በመጠቀም ሲሆን በተለያዩ ምክንያቶች የሚወድቁ ፓስፖርት ቡክሌትና ላሚኔት መኖሩ ለማሳያ፡-
    - ከ2013 ዓ.ም እስከ 2015 ዓ.ም ድረስ 19,632 ላሚኔት እና 4,151 ፓስፖርት ቡክሌት በህትመት ወቅት በተከሰተ የጥራት ጉድለት ምክንያት የወደቀ መሆኑን፤

ለማወቅ ተችሏል፡፡ **(በህትመት ጥራት ጉድለት የወደቁ ፓስፖርት እና ላሚኔት ብዛት በአባሪ ሰባት ተያይዟል)**

117 ስለጉዳዩ የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ የላሚኔት እና ቡክሌት ችግሮች ጋር በተገናኘ የሚወድቁ ቢኖሩም ከጥራት ጋር የተገናኘ ችግር ሳይሆን ከሠራተኛ ትኩረት ፣ ከማሽን ጥራት፣ ከአገልግሎት ብዛት፣ ከኤስታፕላይዘር ፓወር እና ከመረጃ ጥራት የተገናኙና ከግብዓት ጋር ብዙም ግንኙት የሌላቸው ምክንያቶች መሆኑን ገልጸዋል፡፡

118 ተቋሙ የፓስፖርት መረጃ ህትመት ጥራትና ቁጥጥር ስራን በመስራት ፓስፖርት በአለም አቀፍ ስታንዳርድ መሰረት መታተሙን ቁጥጥር ባለማድረጉ በህትመት ወቅት ብክነት በመፍጠር ተቋሙን ለተጨማሪ ወጪ ይዳርጋል።

ስልጠና የሚሰጥበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤

119 ተቋሙ በፓስፖርት አገልግሎት ዙሪያ በክፍተት ላይ የተመሰረተ ስልጠናዎችን የሚሰጥበትና ስልጠናው ያስገኘው ውጤት የሚገመገምበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

120 በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች፣ ከተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና በተደረገ የአካል ምልከታ፡-

- ተቋሙ በደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥና ቅሬታ አፈታት ክህሎት ዙሪያ ለ157 ሰራኞች ከህዳር 1-12/2013 ዓ.ም ስልጠና ሰጥቷል፡፡

121 ይሁን እንጂ

- ተቋሙ በፓስፖርት አገልግሎት ዙሪያ በክፍተት ላይ የተመሰረተ ወጥነት ያለው ስልጠና የማይሰጥ እና ስልጠናው ያስገኘው ውጤት የማይገመገም መሆኑ ለማሳያ ፡-
    - ከ2013 ዓ.ም እስከ 2016 ዓ.ም በፓስፖርት አገልግሎት ዙሪያ አንድ ጊዜ ብቻ ስልጠና የተሰጠ መሆኑ፤
    - ለህትመትና ስርጭት የስራ ክፍል ሰራተኞች ፓስፖርትን በተመለከተ 2014 ዓ.ም ስልጠና የተሰጠ ቢሆንም ከዛ በፊትም ሆነ ከዛ በኋላ የተሰጠ ስልጠና አለመኖሩን የገለጹ መሆኑ፤
    - ለኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የስራ ክፍል ሰራተኞች የተሰጠ ስልጠና አለመኖሩን፤
    - ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አስተባባሪ የስራ ክፍል ሰራተኞች ከ2013-2015 ዓ.ም የተሰጠ ስልጠና አለመኖሩን፤

ለማወቅ ተችሏል፡፡

122 እንዲሁም በናሙና ተመርጠው በታዩት ቅ/ጽ/ቤቶች የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና የመስክ ምልከታ በክፍተት ላይ የተመሰረተ፣ ሁሉንም ሰራተኞች አካታች የሆነ እና ወጥነት ያለው ስልጠና የማይሰጥ መሆኑን ገልጸዋል፤

123 ስለጉዳዩ የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ

- በፓስፖርት አገልግሎት በክፍተት ላይ የተመሰረተ ስልጠናዎች የሚሰጥበትና ስልጠናው ያስገኘው ውጤት የሚገመገምበት የአሰራር ስርዓት ከመተግበር አንጻር በፍላጎት ላይ የተመሰረተ ለስልጠና ከተያዘው በጀት አንጻር ትኩረት የሚሹ

የስልጠና ርእሰ ጉዳዮች በእቅድ በማካተት ተግባራዊ ማድረግ መቻሉን፤ የጉዞ ሰነዶች አይነቶች (ለማን እንደሚሰጡ፤ ተገልጋዮች ማሟላት ስላለባቸው ጉዳዮች፤ የሰራተኞች ሚና ወዘተ) ፤ ደንበኞች አያያዝ (custmer handling) እና በተቋሙ ተልእኮ፤ እሴቶችና ተግባራት (ህትመትና ስርጭት፤ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፤ ፓስፖርት እና ከሌሎች የተቋሙ ተግባራት ጋር የተያያዙ ርእሰ ጉዳዮች) ስልጠና መስጠቱን፤ ሆኖም ግን የስልጠናውን ቀጣይነት፤ ወጥነትና ተደራሽነት ከማሳደግ አንጻር የነበሩ ተግዳሮቶች የበጀት እጥረት፤ የስራ ጫና መኖር፤ የጸጥታ ሁኔታ መሆናቸውን፤ በነበሩ ተግዳራቶች ምክንያት በሚፈለገው መጠን የስልጠና ተግባራት ለማከናውን አስቸጋሪ ቢሆንም የነበሩ ችግሮችን ተቋቁሞ ሰራተኞች በሚሰሩት ስራዎች ላይ በስልጠና ዳይሬክቶሬት እና በሚሰሩበት የስራ ሂደት በኩል በቂ ነው ብሎ መወሰድ ባይቻልም በተቻለ መጠን ግን ሰራተኛው ስራውን በእውቀት ላይ መሰረት በማድረግ እንዲሰራ የሚያስችሉ ስልጠናዎችን ለመስጠት መሞከሩን ገልጸዋል፡፡

124 የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች የጉዞ ሰነዶች አይነቶች ፣ደንበኞች አያያዝ (custmer handling) እና በተቋሙ ተልእኮ፤ እሴቶችና ተግባራት (ህትመትና ስርጭት፤ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፤ ፓስፖርት እና ከሌሎች የተቋሙ ተግባራት ጋር የተያያዙ ርእሰ ጉዳዮች) ስልጠና መስጠቱን ቢገልጹም በደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥና ቅሬታ አፈታት ክህሎት ዙሪያ በ2013 ዓ.ም ከተሰጠው ስልጠና ውጪ ሌሎቹ ስልጠናዎች መሰጠታቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ባለመቅረቡ ምላሻቸውን ለመቀበል ያዳግታል፡፡

125 ተቋሙ በፓስፖርት አገልግሎት ዙሪያ በክፍተት ላይ የተመሰረተ ስልጠናዎችን በመስጠት ስልጠናው ያስገኘውን ውጤት ባለመገምገሙ በኢሚግሬሽን ዘርፉ አዲስ የሚመጡ ጉዳዮችን እንዳይታወቅ፤ በሰራተኞች የአቅም ውስንነት እንዲታይ ከማድረጉም በላይ ተቋሙ የተሰጠውን ሀላፊነት በአግባቡ እንዳይወጣ ያደርጋል።

ተቋሙ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤

126 ተቋሙ በፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮችን እና ሚዲያዎችን በመጠቀም ለህብረተሰቡና ባለድርሻ አካላት ቀጣይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

127 በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች፣ ከተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና በተደረገ የአካል ምልከታ፡-

- በዋና መ/ቤት ለተገልጋዮች ተቋሙ ስለሚሰጠው አገልግሎት በግቢው ውስጥ በስቲከር ግንዛቤ እንደሚሰጥ ለማወቅ ተችሏል፡፡

128 ይሁን እንጂ

- የፓስፖርት አገልግሎት ለማግኘት በቅድሚያ ተገልጋዮች አሟልተው መምጣት ስላለባቸው መረጃ ግንዛቤ የማይሰጥ መሆኑ፤
- 2015 በጀት ዓመት ተቋማዊ የመልካም አስተዳደር እቅድ ላይ ተገልጋዩ የተሟላ መረጃ የሚያገኝበት አሰራር አለመኖሩ፣ ተገልጋዩ በቂ መረጃ ስለማይሰጠው ለረጅም ጊዜ ከተመላለሰ /ከተሰለፈ/ በኋላ አገልግሎቱ አይገባህም ብሎ የመመለስ ሁኔታዎች እንዳሉ የተገለጸ መሆኑ፤
- ተቋሙ በፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮችን እና ሚዲያዎችን በመጠቀም ለህብረተሰቡና ባለድርሻ አካላት ተደራሽ የሆነ እና ቀጣይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑን፤
- ህብረተሰቡ በስልክ ስለአገልግሎቱ መረጃ የሚጠይቅበት የስልክ መስመር የሌለው መሆኑ፤
- ተገልጋዩ ግልጽ የሆነ መረጃ ማግኘት አለመቻሉን፤

ለማወቅ ተችሏል።

129 እንዲሁም በናሙና ተመርጠው በታዩት ቅ/ጽ/ቤቶች የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና የመስክ ምልከታ

- በሆሳዕና ቅ/ጽ/ቤት በፓስፖርት አሰጣጥ ላይ ለተገልጋዮች ስራ ሳይጀምሩ በፊት ግንዛቤ የሚሰጣቸው ሲሆን በቅድሚያ ከመስጠት አንጻር ውስንነቶች መኖራቸውን፤
- ሀዋሳ፣ ጅጅጋ፣ ደሴ እና ድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ወጥነት ያለው ግንዛቤ የማይሰጡ መሆኑን፤

ገልጸዋል፡፡

130 የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ ወቅት በሰጡት ምላሽ አዲሱ አስተዳደር ከመጣ በኋላ በግንዛቤ መፍጠር ዙሪያ ክፍተት መኖሩ ታይቶ በተለያዩ

የማህበራዊ ሚዲያዎችና በግቢው ውስጥ በስቲከር ግንዛቤ የሚሰጥ መሆኑን፤ መግለጫ በየ ሶስት ወሩ እንደሚሰጥ እና ተደራሽ ከመሆኑ አኳያ ክፍተት መኖሩን ገልጸዋል፡፡

131 ተቋሙ በፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮችን እና ሚዲያዎችን በመጠቀም ለህብረተሰቡና ባለድርሻ አካላት ተደራሽ የሆነ እና ቀጣይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ባለማድረጉ ተገልጋዩ ተቋሙ ስለሚሰጠው አገልግሎትና ፓስፖርት ለማውጣት ምን አይነት ማስረጃዎችን አሟልቶ መምጣት እንዳለበት እንዳያውቅና የመረጃ እጥረት እንዲገጥመው በማድረግ ለአላስፈላጊ ወጪ እና ጊዜው እንዲባክን ከማድረጉም በላይ ለደላሎች ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

ተቋሙ ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን የህብረተሰብ አካላት ተጠቃሚ ማድረጉን በተመለከተ፤

132 ተቋሙ የፓስፖርት አገልግሎትን ለመስጠት ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን የህብረተሰብ አካላት ተጠቃሚ የሚያደርግበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል።

133 ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች፣ ከተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና በተደረገ የአካል ምልከታ፡-

- ተቋሙ የፓስፖርት አገልግሎትን ለመስጠት ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን የህብረተሰብ አካላት ተጠቃሚ የሚያደርግበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣ ለማሳያ፡-
    - በዋናው መ/ቤት ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን የህብረተሰብ አካላት ከውጭ ጀምሮ ረጃጅም ሰልፎችን ተሰልፈው የሚገቡ መሆኑ፤ የባለጉዳይ መግቢያ በር ረጅም ደረጃ ያለውና አካልጉዳተኞችንና አቅመደካሞችን ያገናዘበ አለመሆኑ፣

ፎቶ5 ረጅም ደረጃ ያለውና አካልጉዳተኞችንና አቅመደካሞችን ያላገናዘበ የባለጉዳይ መግቢያ በር

- በእድሜ ለገፉ እና ለነብሰጡር ሴቶች ትኩረት ተሰጥቶ ቅድሚያ የማይሰጥና ቅድሚያ እንደሚያገኙ የሚያሳይ ገላጭ ነገር የሌለ መሆኑን፤
- 2015 በጀት ዓመት ተቋማዊ የመልካም አስተዳደር እቅድ ላይ የተቋማዊ አገልግሎት አሰጣጡ ለአካል ጉዳተኞች፣ ለነፍሰጡሮች እና ለአረጋውያን የተለየ አገልግሎት መስኮቶች አለመኖሩ የተገለጸ መሆኑ፤
- ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት ጊቢ ውስጥ ከገቡ በኋላ ለብቻቸው የሚስተናገዱበት ክፍል አለመኖሩ፤ አገልግሎት የሚሰጣቸውም ዜግነት ከሚጣራበት ክፍል ጋር አንድ ላይ ያለና ቢሮውም ለህጻናት ለአገልግሎት የማይመች ቦታ (ሽንት ቤት አጠገብ) መሆኑና የሚያስተናግደውም ባለሙያ አንድ ብቻ መሆኑ፤
- አካል ጉዳተኞች በየክፍሉ ገብተው ለመስተናገድ የማይመች የክፍል አደረጃጀት ያለው መሆኑና ዊልቸር የሚጠቀሙ አካል ጉዳተኞች አገልግሎቱን እስኪያገኙ ውጭ ጸሀይ ላይ የሚጠብቁበት ሁኔታ መኖሩን፤

ለማወቅ ተችሏል፡፡

134 እንዲሁም በናሙና ተመርጠው በታዩት ቅ/ጽ/ቤቶች በተደረገ የመስክ ምልከታ በሆሳዕና ቅ/ጽ/ቤት ልዩ ድጋፍ የሚሹ ባለጉዳዮች ያለ ወረፋ እንደሚስተናገዱ የሚገልጽ ማስታወቂያ ቢኖርም በሌሎቹ (ሀዋሳ፣ ጅማ፣ ጅጅጋ እና ድሬዳዋ) ቅ/ጽ/ቤቶች ገላጭ ማስታወቂያ የሌለ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

135 የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ ወቅት ለአገልግሎት ምቹ አለመሆኑና ለህጻናት አገልግሎት መስጠት የጀመሩት በቅርቡ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

136 ተቋሙ የፓስፖርት አገልግሎትን ለመስጠት ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን የህብረተሰብ አካላት ተጠቃሚ የሚያደርግበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ባለማድረጉ አገልግሎቱን ለማግኘት መጉላላት እንዲገጥማቸው ከማድረጉም በላይ በአገልግሎቱ እርካታ እንዲያጡ ያደርጋል፡፡

መ/ በቴክኖሎጂ የተደገፈ ውጤታማ የመረጃ አያያዝ፣ ጥገና እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር መኖሩንና ተግባራዊነቱን መገምገም፤

ተቋሙ ዘመናዊ የመረጃ ማዕከላትን (data center)፣ ምትክ ቅጂ (Backup) እና የአደጋ ጊዜ መጠባበቂያ ማዕከላት (Disaster recovery sites) ማደራጀቱን በተመለከተ፤

137 ተቋሙ ዘመናዊ የመረጃ ማዕከላትን (data center)፣ ምትክ ቅጂ (Backup) እና የአደጋ ጊዜ መጠባበቂያ ማዕከላት (Disaster recovery sites) ሊያደራጅና የፓስፖርት መረጃዎች ለአደጋ እንዳይጋለጡ ተገቢውን ደህንነትና ጥበቃ የሚያደርግበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

138 ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች፣ ከተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ፡-

- ተቋሙ ዘመናዊ የመረጃ ማዕከል (data center) እና የአደጋ ጊዜ መጠባበቂያ ማዕከላት (Disaster recovery sites) የሌለው መሆኑ፤
- በ 2013 ዓ.ም የምዝገባ ሲስተሙን አፕሊኬሽንና ዳታቤዝ ማግኘት እንዳልተቻለ (ወደ ሲስተም መግባት አለመቻሉ) እንዲሁም ለአንድ ሳምንት (ከታህሳስ 9-15/2013 ዓ.ም) እስኪስተካከል ድረስ አገልግሎት ተቋርጦ መቆየቱን፤

ለማወቅ ተችሏል፡፡

139 ስለጉዳዩ የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ

- ዘመናዊ የመረጃ ማዕከል የሌላቸው መሆኑን፣ የአደጋ ጊዜ መጠባበቂያ ማዕከልን በተመለከተ በአሁን ሰዓት አገልግሎት ሙሉ ለሙሉ ያልጀመረ ሲሆን ፣ የወጪ ገቢ የቦርደር ኮንትሮል ሲስተም የአደጋ ጊዜ ማዕከል በፉሪ/ለቡ ባቡር ጣቢያ ዘመናዊ ዳታ ማዕከል ውስጥ እንዳለ ግንዛቤ ውስጥ እንዲገባ እና ሌሎች ቀሪ ሲስተሞችን ወደ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ዘመናዊ የዳታ ሴንተር ማዕከል ለመዘርጋት ስራዎች የተጀመሩ መሆኑን እና የጋራ መግባቢያ ሰነድም በሁለቱም መስሪያ ቤቶች ከፍተኛ አመራር መፈረሙን፤
- በታህሳስ 9-15 2013 የዳታ ስቶር ሲስተም ችግር ደርሶበት እንደነበረና አገልግሎትም ተቋርጦ የነበር ቢሆንም ሲስተሙ ያለምንም ዳታ መጥፋት ማስተካከል መቻሉን እና ለችግር ጊዜ ከተቀመጠ ባካፕ ሲስተም በጣም የአስቸኳይ

አስቸኳይ በህክምና፣ በውጪ ጉዳይ እንዲሁም በጠቅላይ ሚኒስቴር የቀረቡ ጥያቄዎችን በመመዝገብ ፓስፖርት አገልግሎት የተሰጠ መሆኑን፤

ገልጸዋል፡፡

140 ተቋሙ ዘመናዊ የመረጃ ማዕከላትን (data center) እና የአደጋ ጊዜ መጠባበቂያ ማዕከላት (Disaster recovery sites) አደራጅቶ የፓስፖርት መረጃዎች ለአደጋ እንዳይጋለጡ ተገቢውን ደህንነትና ጥበቃ የሚያደርግበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ባለማድረጉ በስትራቴጂክ እቅዱ የያዘውን ዘመናዊ የቴክኖሎጂ ስርዓት መገንባትና ማስተዳደር ግብ እንዳያሳካ፤ አገልግሎቱን በሚፈለገው የአገልግሎት ስታንዳርድ እና የጥራት ደረጃ እንዳይሰጥ እና ተጨማሪ ፍላጎት እንዳይጨምር ከማድረጉም በላይ በተቋሙ ያሉ መረጃዎችን አደጋ ላይ ይጥላል፡፡

የፓስፖርት መረጃ ጥራት እና ደህንነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የአሰራር ስርአት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤

141 ተቋሙ የፓስፖርት መረጃ ጥራት እና ደህንነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የአሰራር ስርአት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

142 ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች፣ ከተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና የመስክ ምልከታ፡-

- ተቋሙ የፓስፖርት መረጃ ጥራት እና ደህንነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የአሰራር ስርአት በመዘርጋት ተግባራዊ ያላደረገና መረጃዎች የሚጣሩት በልምድ መሆኑን፤
- ተቋሙ የ2015 በጀት አመት አመታዊ እቅድ አፈጻጸም ላይ አጠራጣሪ ሰነዶችን ለመለየት የሚያስችሉ የተለያዩ መሳሪያዎችን ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ የማጣራት ስራዎችን በመስራት ችግሩን ለመቀነስ እየተሰራ መሆኑን ቢገልጽም በዋናው መ/ቤት የልደት ሰርተፊኬት እና የአዲስ አበባ መታወቂያን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ከሚጠቀምበት 4 ዩቪ ላይት ውጭ ሌላ መሳሪያ የሌለው መሆኑን፤

ለማወቅ ተችሏል፡፡

143 እንዲሁም በናሙና ተመርጠው በታዩት ቅ/ጽ/ቤቶች የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና የመስክ ምልከታ የፓስፖርት መረጃ ጥራት ለማረጋገጥ የሚያስችል

መሳሪያ የሌላቸው መሆኑንና በጥርጣሬ የሚታዩ ሰነዶችን ለማረጋገጥ እየተቸገሩ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

144 የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ ወቅት ሰነዶች የሚጣሩት በልምድ መሆኑንና እንደ ሀገር ወጥ የሆነ መታወቂያ አለመኖሩን ገልጸዋል፡፡

145 ተቋሙ የፓስፖርት መረጃ ጥራት እና ደህንነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የአሰራር ስርአት ዘርግቶ ተግባራዊ ባለማድረጉ ፎርጂድ የሚሰሩ ማስረጃዎች በማጣራት ወቅት እንዲያልፉ በማድረግ ፓስፖርት ለማይገባው ሰው (ለውጭ ዜጎች) እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡

የኢሚግሬሽን አገልግሎት ለማግኘት ተገልጋዮች የሚሞሏቸው ቅጾች ዲጂታላይዝድ መደረጉን በተመለከተ፤

146 የኢሚግሬሽን አገልግሎት ለማግኘት ተገልጋዮች የሚሞሏቸው ቅጾች ዲጂታላይዝድ ሊደረጉ ይገባል፡፡

147 ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች፣ ከተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና የመስክ ምልከታ ተቋሙ በኦንላይን ከሚሞሉት መረጃዎች ውጭ የኢሚግሬሽን አገልግሎት ለማግኘት ተገልጋዮች የሚሞሏቸው ቅጾችን ዲጂታላይዝድ ያላደረገ መሆኑ፤ ለማሳያ፡-

- በዋና መ/ቤት ተገልጋዮች በአካል መጥተው የሚያቀርቡት ማስረጃ እና አስቸኳይ ፓስፖርት የሚያወጡ ተገልጋዮች መረጃ ዲጂታላይዝድ ያልተደረገ መሆኑን፤
- የአሶሳ፣ ጋምቤላ እና ሆሳዕና ቅ/ጽ/ቤቶች የኦንላይን አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑና የተገልጋይ ማስረጃዎች ዲጂታላይዝ ያልተደረጉ መሆኑን፤

ለማወቅ ተችሏል፡፡

148 እንዲሁም በናሙና ተመርጠው በታዩት ቅ/ጽ/ቤቶች የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና የመስክ ምልከታ ድሬዳዋ፣ ሀዋሳ፣ ደሴ፣ ጅማ እና ጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤቶች የተገልጋይ መረጃዎች ዲጂታላይዝድ ያልተደረጉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

149 ስለጉዳዩ የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ምላሽ አልሰጡም፡፡

150 የኢሚግሬሽን አገልግሎት ለማግኘት ተገልጋዮች የሚሞሏቸው ቅጾች ዲጂታላይዝድ ባለመደረጋቸው በአስቸኳይ የሚፈለጉ ፋይሎች በቀላሉ እንዳይገኙ እና መረጃዎችን

በሀርድ ኮፒ በመያዝ የቦታ መጣበብ ከመፍጠሩም በላይ የተገልጋይ መረጃዎች እንዲጠፉ ያደርጋል፡፡

የፓስፖርት አገልግሎት መረጃዎች እና ማስረጃዎች በአግባቡ መያዛቸውንና መወገዳቸውን በተመለከተ፤

151 የፓስፖርት አገልግሎት መረጃዎች እና ማስረጃዎች በአይነት፣ በጊዜና በደህንነት ደረጃቸው ተለይተው ሊደራጁ፣ በአግባቡ ሊያዙ እና ሊወገዱ ይገባል፡፡

152 ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች፣ ከተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና የመስክ ምልከታ፡-

- በተቋሙ የፓስፖርት አገልግሎት መረጃዎች እና ማስረጃዎች በአይነት፣ በጊዜና በደህንነት ደረጃቸው ለይቶ ለማደራጀት የኢሚግሬሽን መረጃ አደረጃጀት መመሪያ የተዘጋጀ ቢሆንም ያልጸደቀ መሆኑ፣
- በዋና መ/ቤትና በናሙና ተመርጠው በታዩ ቅ/ጽ/ቤቶች የፓስፖርት መረጃን በአግባቡ አደራጅቶ ለመያዝ የሚያስችል የተደራጀ ክፍል የሌለና የፋይል መደርደርያዎች ሞልተው የተገልጋይ መረጃዎች መሬት ላይ ተደርድረውና ተበትነው የተቀመጡ መሆኑ፤ ተዘዋውሮ መረጃዎችን ለማውጣት የማይመች፤ የመረጃዎች የመደበላለቅ ሁኔታ መኖሩንና በአስቸኳይ የሚፈለጉ ፋይሎችን ለማግኘት አስቸጋሪ መሆኑን፤

ፎቶ-6 በዋና መ/ቤት መሬት ተደርድረውና ተበትነው የተቀመጡ መረጃዎች

ፎቶ7 በሀዋሳ እና ጅማ ቅ/ጽ/ቤቶች መሬት ላይ ተደርድረው የተቀመጡ መረጃዎች

- በዋና መ/ቤት የፓስፖርት መረጃ ማደራጃ ክፍል ጣሪያው የሚያፈስ፣ ከአቀማመጥ ጉድለት የተበላሹና በአይጥ የተበሉ መረጃዎች መኖራቸው፣

ፎቶ 8 በዋና መ/ቤት ጣሪያው የሚያፈስ መረጃ ማደራጃ ክፍል

- ስምንት ሚሊየን አንድ መቶ አስራ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሀያ (8,111,720) ማስረጃዎችን በመለየት የማስወገድ ስራ የተሰራ መሆኑ በ2015 በጀት አመት አመታዊ እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ የተገለጸ ቢሆንም በምን አግባብ እንደተወገዱ

የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ እና የአወጋገድ ሂደቱ ህጋዊ ሥርአቱን ተከትሎ የተወገደ ስለመሆኑ የኦዲት ቡድኑ ማረጋገጥ አለመቻሉን፤

ለማወቅ ተችሏል፡፡

153 ስለጉዳዩ የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ በፓስፖርት ማደራጃ ክፍል የሚያፈስ ጣሪያ ስለመኖሩ በሥራ ክፍሉ የቀረበ ጥያቄ አለመኖሩንና ይህ ችግር ስለመፈጠሩ መረጃው እንዳልነበራቸው የገለጹ ሲሆን የመረጃዎችን አቀማመጥ እና የተወገዱ 8,111,720 ማስረጃዎችን በተመለከተ በተደጋጋሚ የተጠየቁ ቢሆንም ምላሽ አልሰጡም፡፡

154 የተቋሙ ኃላፊዎች በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት አስተያየት የፓስፖርት አገልግሎት መረጃን አዲሱ አስተዳደር ከመጣ ጀምሮ ሰነድ አለማስወገዳቸውን እና የተወገደዉ እነሱ ከመምጣታቸው በፊት ስለሆነ መረጃዉ እንደሌላቸው ገልጸዋል፡፡

155 የፓስፖርት አገልግሎት መረጃዎች በአግባቡ ባለመደራጀታቸውና ባለመወገዳቸው ሰነዶች ደህንነታቸው በተጠበቀ መልኩ እንዳይቀመጡ በማድረግ ለብልሽት እንዲጋለጡና መረጃዎች እንዲደበላለቁ በማድረግ በቀላሉ እንዳይገኙ ከማድረጉም በላይ የተወገዱ መረጃዎችን በተመለከተ ማስረጃዎች ባለመቅረባቸው መረጃዎቹ በመንግስት የግዢና የንብረት አወጋገድ መመሪያ መሰረት ስለመወገዳቸው ተአማኒነት እና ግልጸኝነት እንዳይኖረው ያደርጋል፡፡

ለህትመት ማሽኖችና ለፓስፖርት አገልግሎት ስርዓቱ (System) ጥገና መከናወኑን በተመለከተ፤

156 ተቋሙ ለህትመት የሚያገለግሉ የኤሌክትሮኒክስ እቃዎችና የህትመት ማሽኖች ወቅቱን ጠብቀው መጠገናቸውን የሚከታተልበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ እንዲሁም

157 ለፓስፖርት አገልግሎት ስርዓቱ (System) የቅድመ ብልሽት ቁጥጥር /Inspection/ እና የጥገና ዕቅድ በማዘጋጀት በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

158 ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች እና ከተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ፡-

- ተቋሙ ለህትመት የሚያገለግሉ የኤሌክትሮኒክስ እቃዎችና የህትመት ማሽኖችን ለመጠገን ዕቅድ ያልተያዘ፣ ወቅቱን ጠብቀው መጠገናቸውን የማይከታተልና ከውጭ

ድርጅቶች ጋር በተገባ ውል መሰረት ጥገና ስለመከናወኑ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ ለማሳያ፡-

- ተቋሙ ሱፐርኮም (SUPERCOM LTD) ከተባለ ድርጅት ጋር የጉዞ ሰነዶች ህትመት ንዑስ ስርዓቱን (Travel Document Printing/ TDP) ለማሻሻል እ.ኤ.አ ሚያዝያ 2020 ውል የተዘጋጀ ቢሆንም ስምምነቱ የተፈረመው በኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት በኩል ብቻ መሆኑ፤

- የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ጥገናው አለመሰራቱን ነገር ግን ስምምነቱ በሁለቱም ወገን የተፈረመ መሆኑን የገለጹ መሆኑ፤
- ተቋሙ ለፓስፖርት አገልግሎት ስርዓቱ (System) የቅድመ ብልሽት ቁጥጥር /Inspection/ እና የጥገና ዕቅድ በማዘጋጀት በዕቅዱ መሰረት ቁጥጥር እና ጥገና የማያደርግ መሆኑ፤
- ተቋሙ IN-IDT SAS ከተባለ የፈረንሳይ ድርጅት ጋር የተቀናጀ የኢሚግሬሽን ቁጥጥር መረጃ ንዑስ ስርዓቱን (Integrated Immigration control Information system/ IICIS) ለማሻሻል፣ አጠቃላይ የስርዓት፣ የመሳሪያዎች ድጋፍ እና የጥገና አገልግሎት ለመስጠት እ.ኤ.አ በ2020 ውል የተዘጋጀ ቢሆንም ስምምነቱ የተፈረመው በኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት በኩል ብቻ መሆኑን፤

ለማወቅ ተችሏል፡፡

159 ስለጉዳዩ የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ

- የህትመት ማሽኖችን በተመለከተ ስራው ስለመጠናቀቁ FINAL ATP CERTIFICATE: Integration and Testing TDP system after upgrade. በቴክኒካል ቲም በሁለቱም ተቋማት የተፈረመ ማስረጃ በአባሪ ተያይዟል
- ሲስተሙን በተመለከተ ስራው ስለመሰራቱ CERTIFICATE OF ACCEPTANCE, የተፈረመ መሆኑ የሚያሳይ አባሪ ላይ የተቀመጠ ሲሆን፣ በተለያዩ ጊዜያት የሰርቨር እቃዎችን፣ የላይሰንስ ዶንግል እና የአሻራ መውሰጃ መሳሪያዎችን በኤምባሲ እና በDHL እንደላኩልን ግንዛቤ ውስጥ እንዲገባ እና ማስረጃዎቹ፣ (ኤርዌይ ቢልና የእቃ ዓይነት ዝርዝር በአባሪ ተያይዟል)።

በማለት ገልጸዋል፡፡

160 ለህትመት ማሽኖችና ለፓስፖርት አገልግሎት ስርዓቱ (System) የቅድመ ብልሽት ቁጥጥር /Inspection/ እና የጥገና ዕቅድ በማዘጋጀት ወቅቱን ጠብቀው እንዲጠገኑ ባለማድረጉ የሚጋጥሙ ችግሮች በወቅቱ እንዳይፈቱ በማድረግ አገልግሎት አሰጣጡ ቀልጣፋ እንዳይሆን እና ተገልጋዮች እንዲጉላሉ ያደርጋል።

የፓስፖርት አገልግሎትን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፤

161 ተቋሙ የፓስፖርት አገልግሎትን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር የሚሰሩ ጉዳዮችን በመለየት ተግባራዊነቱን በጋራ የሚከታተልበት ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

162 ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች፣ ከተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ ተቋሙ የፓስፖርት አገልግሎትን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር የሚሰሩ ጉዳዮችን በመለየት ተግባራዊነቱን በጋራ የሚከታተልበት ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፤

163 በተጨማሪም በናሙና ተመርጠው በታዩት ቅ/ጽ/ቤቶች የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ የሆሳዕና ቅ/ጽ/ቤት ከባለድርሻ አካላት ጋር በአካል ተገናኝተው እየሰሩ አለመሆኑን የገለጹ ሲሆን ሌሎቹ (ሀዋሳ፣ ጅማ፣ ደሴ እና ድሬዳዋ) ቅ/ጽ/ቤቶች ከፍትህ አካላት እና ከቀበሌዎች ጋር በጋራ እንደሚሰሩ የገለጹ ቢሆንም ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

164 የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ ወቅት በሰጡት ምላሽ በፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ባለድርሻ ያልሆነ አካል አለመኖሩን ነገር ግን በሰነድ ደረጃ ተፈራርመው በቅንጅት የሚሰሩት ስራ አለመኖሩን ገልጸዋል፡፡

165 ተቋሙ የፓስፖርት አገልግሎትን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር የሚሰሩ ጉዳዮችን በመለየት ተግባራዊነቱን በጋራ የሚከታተልበት ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ባለማድረጉ ፓስፖርትን በተመለከተ ከባለድርሻ ጋር መሰራት ያለባቸው ስራዎች እንዳይታወቁ በማድረግ አገልግሎት አሰጣጡ ቀልጣፋ እንዳይሆን ያደርጋል።

ክፍል ሦስት

መደምደሚያ

ከላይ በኦዲት ግኝቶቹ ላይ እንደተመለከተው በኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት እና በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በተሰበሰቡ ማስረጃዎች መሰረት በተገኙ የአሰራር ክፍተቶች ላይ የሚከተሉት የመደምደሚያ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡

- ተቋሙ የኢሚግሬሽን አሰራር ስርዓትን የሚመለከት ፖሊሲ አመንጭቶ ለሚመለከተው አካል በማቅረብ አጸድቆ ተግባራዊ አላደረገም፡፡
- ተቋሙ ለፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ የሚያገለግሉና የአገልግሎት አሰጣጥን በግልጽ የሚያሳይ መመሪያ፣ ስታንዳርድና የዜጎች ቻርተር ሰነድ አዘጋጅቶ በማጸደቅ ተግባራዊ በማድረግ አፈጻጸሙን እየተከታተለ አይደለም።
- የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ተቋማዊ መዋቅር በማጥናትና ለሚመለከተው አካል በማጸደቅ የተፈቀደው የስራ መደብ በዋና መ/ቤትም ሆነ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በሰው ኃይል እንዲሟላ አላደረገም።
- ተቋሙ የስራ መዘርዝር (Job Description) አዘጋጅቶ በማጽደቅ ሰራተኞች ስራ ከመጀመራቸው በፊት አልሰጠም፡፡
- ተቋሙ በዓለም አቀፉ የሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ስታንዳርድ (ICAO DOC 9303) መሰረት ጥናት በማድረግ የቡክሌት ፓስፖርትን ወደ ኢ-ፓስፖርት መቀየር የሚያስችል አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ አላደረገም፡፡
- ተቋሙ ከድንበርና ከጎረቤት ሃገራት መሆናቸው አጠራጣሪ የሆኑ ተገልጋዮች ሲያጋጥሙ ዜግነታቸውን በልምድ የሚጣራና ወጥ የሆነ አሰራር እና መመሪያ አዘጋጅቶ ተግባራዊ አላደረገም፡፡
- ተቋሙ የአዲስ መደበኛ ፓስፖርት፣ ለአስቸኳይ ፓስፖርት እና የፓስፖርት እድሳት ተገልጋዮች አገልግሎቱን በምን ያህል ጊዜ እንደደሚያገኙ የጊዜ ሰሌዳ ያላዘጋጀ፣ ፓስፖርት በቀነ ቀጠሮ የማይሰጥና የኦንላይን መመዝገቢያ ድረ ገጽ ላይ ያሉ መረጃዎችን አላሻሻለም፡፡
- ተቋሙ የፓስፖርት ምዝገባ ቀን ቀጠሮ ያሳለፉ ግለሰቦች የሚስተናገዱበት አሰራር ሌሎች ህጎችን በማይጥስ መልኩ አዘጋጅቶ እና በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ተግባራዊ አላደረገም፡፡

- ተቋሙ ፓስፖርት ከሚወስዱ ተገልጋዮች ያለደረሰኝ 50 ብር ያለደረሰኝ የሚቀበል መሆኑ እና ከመልክት አስተላላፊ ተቋማት ጋር የፓስፖርት ስርጭትን ለማካሄድ የሚያስችል ህጋዊ መሰረት ያለው የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግራዊ አላደረገም፡፡
- ተቋሙ የፓስፖርት የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት፣ ተደራሽነትና ሽፋን ደረጃን ለመገምገም፣ ለመቆጣጠርና ለመደገፍ የሚያስችል ጥናት በማካሄድ አገልግቱን ተደራሽ አላደረገም፡፡
- ተቋሙ የፓስፖርት አገልግሎትን ለመስጠት በዋው መ/ቤትም ሆነ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የቢሮው አቀማመጥ የስራ ፍሰትን ባማከለ መልኩ ያላደራጀና መጠለያ ያለው ወረፋ መጠበቂያ እንዲሁም ንጹህና ከተገልጋዩ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ መጸዳጃ ቤት አላዘጋጀም፡፡
- ተቋሙ የሰራተኞች የስነ ምግባር መመሪያ አዘጋጅቶ በዋናው መ/ቤት እና በቅ/ጽ/ቤቶች መመሪያው ተግባራዊ ስለመደረጉ ክትትል ለማድረግ በሚያስችል መልኩ እየሰራ አይደለም፡፡
- በፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የሚታዩ የብልሹ አሰራር ችግሮችን ለመከላከል የሚያስችል ያልዘረጋ እና ተጠያቂነት ያለበት አሰራር በመዘርጋት ክትልና ቁጥጥር አላደረገም፡፡
- ተቋሙ የፓስፖርት ግብዓቶች የግዥ ዕቅድ በወጥነት የማያቅድና ግዥውም በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ ስለመደረጉ የሚከታተልበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አላደረገም፡፡
- ተቋሙ ለፓስፖርት ግብቶች ግዥ የውል ስምምነት ማስረጃዎችን አደራጅቶ የማይይዝ፣ ግዥው በውሉ መሰረት ስለመከናወኑ የሚቆጣጠርበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አላደረገም፡፡
- ተቋሙ ለፓስፖርት ግብዓቶች ግዥ በተዘጋጀው የግዥ መስፈርት መሰረት ስለመከናወኑ የሚያረጋግጥበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አላደረገም፡፡
- ተቋሙ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን የፓስፖርት አገልግሎትን ለመስጠት በሚያስችል መልኩ (በግብዓትና በቴክኒክ) አላደራጀም፡፡
- በተቋሙ የስራ ክፍሎች በተቋሙ ዕቅድ መሰረት የስራ ክፍላቸውን ዕቅድ አዘጋጅተው አፈጻጸማቸውን በወጥነት የሚከታተሉበት እንዲሁም ማኔጅመንቱም በሚያደርጋቸው ስብሰባዎች ቃለ-ጉባኤ በመያዝ በዘርፍ አፈጻጸማቸውን የሚገመግሙበትና ግብረመልስ የሚሰጡበት አሰራር አልዘረጋም፡፡

- ተቋሙ በፓስፖርት አገልግሎት ዙሪያ በክፍተት ላይ የተመሰረተ ስልጠናዎችን የማይሰጥ፣ ስልጠናው ያስገኘውን ውጤት የሚገመገምበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አላደረገም፡፡
- ተቋሙ በፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮችን እና ሚዲያዎችን በመጠቀም ለህብረተሰቡና ባለድርሻ አካላት ተደራሽ የሆነ እና ቀጣይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አላደረገም፡፡
- ተቋሙ የፓስፖርት አገልግሎትን ለመስጠት ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን የህብረተሰብ አካላት ተጠቃሚ የሚያደርግበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አላደረገም፡፡
- ተቋሙ ዘመናዊ የመረጃ ማዕከል (data center) እና የአደጋ ጊዜ መጠባበቂያ ማዕከላት (Disaster recovery sites) ሊአደራጅቶ የፓስፖርት መረጃዎች ለአደጋ እንዳይጋለጡ ተገቢውን ደህንነትና ጥበቃ የሚያደርግበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አላደረገም፡፡
- ተቋሙ የፓስፖርት መረጃ ጥራት እና ደህንነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የአሰራር ስርአት ዘርግቶ ተግባራዊ አላደረገም፡፡
- የኢሚግሬሽን አገልግሎት ለማግኘት ተገልጋዮች የሚሞሏቸው ቅጾች ዲጂታላይዝድ አልተደረጉም፡፡
- ተቋሙ ለህትመት ማሽኖችና ለፓስፖርት አገልግሎት ስርዓቱ (System) የቅድመ ብልሽት ቁጥጥር /Inspection/ እና የጥገና ዕቅድ በማዘጋጀት ወቅቱን ጠብቀው እንዲጠገኑ አላደረገም፡፡
- ተቋሙ የፓስፖርት አገልግሎትን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር የሚሰሩ ጉዳዮችን ለይቶ በማስቀመጥ ተግባራዊነቱን በጋራ አልተከታተለም፡፡

ክፍል አራት
የማሻሻያ ሃሣቦች

በመሆኑም የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት በፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ቀልጣፋ እና ውጤታማ ስራ እየተሠራ እንዳልሆነ ያሳያል፡፡ ይህንንም መሠረት በማድረግ በዝርዝር የቀረቡትን የኦዲት ክፍተቶች ለማሻሻል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ተብሎ የታመነባቸው የማሻሻያ ሃሣቦች ቀርበዋል፡፡

- ተቋሙ የኢሚግሬሽን አሰራር ስርዓትን የሚመለከት ፖሊሲ አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል በማጸደቅ የተሰጠውን ተልዕኮ ከሀገራዊ ስትራቴጂክ ጉዳዮች ጋር አስተሳስሮ መስራት ይኖርበታል፡፡
- ተቋሙ ለፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ የሚያገለግሉ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት እና መመሪያና ስታንዳርድ አዘጋጅቶ በማጸደቅ ተግባራዊ ሊያደርግና ተጠያቂነትን በማስፈን ለተገልጋዩ ቀልጣፋ አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል።
- ተቋሙ የአሰራር ስርዓት ማሻሻያ በማዘጋጀት የፓስፖርት አገልግሎትን ለማሳለጥ የሚያስችል የዜጎች ቻርተር ሰነድ አዘጋጅቶ በማጽደቅ ተግባራዊ በማድረግ ተጠያቂነትን በግልጽ በማመላከት ተገልጋዮች የሚያገኙትን የአገልግሎት አይነት ፣ የሚወስደውን ጊዜና ወጪ በማሳወቅ ለተገልጋዩ ቀልጣፋ እና ውጤታማ አገልግሎት በመስጠት አፈጻጸሙን ሊከታተል ይገባል።
- የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ተቋማዊ መዋቅር በማጥናትና ለሚመለከተው አካል በማጸደቅ የተፈቀደው የስራ መደብ በዋና መ/ቤትም ሆነ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በሰው ኃይል እንዲሟላ ማድረግ ይኖርበታል።
- ተቋሙ ለሁሉም የስራ መደቦች የስራ መዘርዝር (Job Description) አዘጋጅቶ በማጸደቅ እና ለሰራተኞችም ስራ ከመጀመራቸው በፊት እንዲደርሳቸው ማድረግ ይኖርበታል።
- ተቋሙ በዓለም አቀፉ የሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ስታንዳርድ (ICAO DOC 9303) መሰረት ጥናት በማድረግ የቡክሌት ፓስፖርትን ወደ ኢ-ፓስፖርት መቀየር የሚያስችል አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ በማድረግ ደህንነቱ የተጠናከረ የጉዞ ሰነድ መስጠት ይኖርበታል።

- ተቋሙ ከድንበርና ከጎረቤት ሃገራት መሆናቸው አጠራጣሪ የሆኑ ተገልጋዮች ሲያጋጥሙ ዜግነታቸው የሚጣራበት ወጥ የሆነ የአሰራር መመሪያ አዘጋጅቶ በማጸደቅ በመመሪያው መሰረት ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት ይኖርበታል።
- ተቋሙ የአዲስ መደበኛ ፓስፖርት፣ የፓስፖርት እድሳት፣ የጠፋ ፓስፖርት እና የፓስፖርት እርማት አገልግሎት ፈላጊዎች አገልግሎቱን በምን ያህል ጊዜ እንደሚያገኙ የሚገልጽ የአገልግሎት ስታንዳርድ ሊያዘጋጅና አገልግሎቱን በወቅቱ የሚሰጥበትና ተገልጋዩን እኩል ተጠቃሚ የሚያደርግበት እንዲሁም ፓስፖርት ለመውሰድ የሚወስደውን የቀጠሮ ጊዜ የሚያሳጥርበት ቀልጣፋና ውጤታማ አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል።
- ተቋሙ የአስቸኳይ ፓስፖርት መመሪያው አሻሽሎ ግልጽና ሁሉንም ተገልጋይ እኩል ተጠቃሚ ሊያደርግ በሚያስችል መልኩ ማዘጋጀት ይኖርበታል።
- የተቋሙ የኦንላይን መመዝገቢያ ድረ ገጽ ላይ ያሉ መረጃዎች ተገልጋዩ (ፓስፖርት አገልግሎት ለማግኘት ማሟለት ያለበት ቅድመ ሁኔታ) በተቋሙ መጥቶ በሚጠየቀው መረጃ ልክ ሊሻሻልና አብዛኛው ህብረተሰብ ሊረዳው በሚችል ቋንቋ ሊዘጋጅ ይገባል።
- ተቋሙ ፓስፖርት ለመውሰድ ከሚመጡ ተገልጋዮች የሚሰበስበውን ገንዘብ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያሳትመው ወይም እንዲታተም በሚፈቅደው ደረሰኝ ሊያደርግ እንዲሁም ለተቋሙ በገንዘብ ሚኒስቴር በተፈቀደ አካውንት ውስጥ ሊያስገባ ይገባል።
- ተቋሙ ከመልክት አስተላላፊ ተቋማት ጋር የፓስፖርት ስርጭትን ለማካሄድ የሚያስችል ህጋዊ መሰረት ያለው ቀልጣፋ የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል።
- ተቋሙ የፓስፖርት የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት፣ የተደራሽነትና ሽፋን ደረጃን ለመገምገም፣ ለመቆጣጠርና ለመደገፍ የሚያስችል ጥናት በማካሄድ በጥናቱ የታዩ ችግሮች ላይ በሚሰጠው ምክረሀሳብ መሰረት ማሻሻያዎች ስለመደረጋቸው ክትትል ሊያደርግና፤ በስትራቴጂክ ዕቅዱ መሰረት አገልግሎቱን በማስፋት ተደራሽ በማድረግ ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት ይጠበቅበታል።
- በተቋሙ የፓስፖርት አገልግሎትን ለመስጠት የቢሮውን አቀማመጥ የስራ ፍሰትን ባማከለ መልኩ አደራጅቶ ቢሮዎቹ የሚሰጡትን አገልግሎት በግልጽ የሚያሳይ ጠቋሚ

ምልክት ሊያዘጋጅና ተገልጋዩ ጋር ተመጣጣኝ መጠለያ ያለው ወረፋ መጠበቂያ እንዲሁም ንጹህ የሆነ መጸዳጃ ቤት ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

- ተቋሙ የሰራተኞች የስነ ምግባር መመሪያ አዘጋጅቶ በሚመለከተው አካል በማጸደቅ መመሪያው ተግባራዊ ስለመደረጉና ሰራተኞች ከተገልጋዩ ጋር ባላቸው የስራ ግንኙነት ተገልጋዩን በአክብሮትና በትህትና የሚያስተናግዱ ስለመሆኑ ውጤታማ የክትትልና የቁጥጥር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- በተቋሙ በዋና መ/ቤትና በቅ/ጽ/ቤቶች የተደራጀ ቅሬታ የሚቀርብበት ስርዓት በመዘርጋት ቅሬታው የሚጣራበት እና የሚሄድበት ሂደት የሚወስደውን ጊዜ፣ ቅሬታ የቀረበባቸው ሰዎች የሚወሰድባቸው እርምጃ በግልጽ የሚያሳይ ቀልጣፋ እና ውጤታማ አሰራር ሊዘረጋና የቀረበውን ቅሬታ እና ቅሬታው መፈታቱን በግልጽ በሚያሳይ መልኩ ተመዝግቦ የሚያዝበት፤ ቅሬታዎችም በወቅቱ እንዲፈቱ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
- ተቋሙ በፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የሚታዩ የብልሹ አሰራር ችግሮችን ለመከላከል የሚያስችል ውጤታማ ስርዓት ሊዘረጋና ብልሹ አሰራር ሲፈጽሙ የተገኙ የተቋሙ ሰራተኞችን ተከታትሎ እርምጃ በመውሰድ ተጠያቂ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- ተቋሙ የፓስፖርት ግብዓቶች የግዥ ዕቅድ በየአመቱ በማዘጋጀት ግዥውን በዕቅዱ መሰረት ሊያከናውንና ተግባራዊነቱን ለመገምገም የአፈጻጸም ሪፖርት አዘጋጅቶ ቀልጣፋ እና ውጤታማ ክትትል ሊያርግ ይገባል፡፡
- ተቋሙ ለፓስፖርት ግብቶች ግዥ የውል ስምምነት በግዥ መመሪያ መሰረት አደራጅቶ ሊያስቀምጥና ግዥው በውሉ መሰረት ስለመከናወኑ ውጤታማ ክትትል ማድረግ ይኖርበታል።
- ተቋሙ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን የፓስፖርት አገልግሎትን ለመስጠት በሚያስችል መልኩ (በግብዓትና በቴክኒክ) በማደራጀት ውጤታማ ድጋፍ እና ክትትል ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
- የተቋሙ የስራ ክፍሎች በተቋሙ ዕቅድ መሰረት የስራ ክፍላቸውን ዕቅድ አዘጋጅተው አፈጻጸማቸውን በወጥነት የሚከታተሉበት እንዲሁም ማኔጅመንቱም በሚያደርጋቸው ስብሰባዎች ቃለ-ጉባኤ በመያዝ በዘርፍ አፈጻጸማቸውን የሚገመግሙበትና ግብረመልስ የሚሰጡበት ውጤታማ እና ቀልጣፋ የሆነ የክትትልና የቁጥጥር ስርዓት ዘርቶ ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

- ተቋሙ የፓስፖርት መረጃ ህትመት ጥራትና ቁጥጥር ስራን በመስራት ፓስፖርት በአለም አቀፍ ስታንዳርድ መሰረት መታተሙን በመከታተልና በመቆጣጠር በጥራት ጉድለት ምክንያት የሚወድቁ የፓስፖርት እና የላሚኔት ቁጥር መቀነስ ይኖርበታል፡፡
- ተቋሙ በፓስፖርት አገልግሎት ዙሪያ በክፍተት ላይ የተመሰረተ ወጥነትና ቀጣይነት ያለው ስልጠናን ለመስጠት የሚያስችል ውጤታማ ስርዓት ዘርግቶ የመጣውን ውጤት ለመገምገም በሚያስችል መልኩ መስራት ይኖርበታል፡፡
- ተቋሙ በፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮችን እና ሚዲያዎችን በመጠቀም ለህብረተሰቡና ባለድርሻ አካላት ውጤታማ፣ ተደራሽ እና ቀጣይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡
- በተቋሙ የፓስፖርት አገልግሎትን ለመስጠት ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን የህብረተሰብ አካላት ቅድሚያ እንደሚያገኙ ወጥ የሆነ እና ሊገመገም የሚችል (ልዩ መስኮት መክፈት...) ስርዓት በመዘርጋት ትኩረት ተሰጥቶ ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- ተቋሙ ዘመናዊ የመረጃ ማዕከላትን (data center) እና የአደጋ ጊዜ መጠባበቂያ ማዕከላት (Disaster recovery sites) አደራጅቶ የፓስፖርት መረጃዎች ለአደጋ እንዳይጋለጡ ተገቢውን ደህንነትና ጥበቃ የሚያደርግበት ውጤታማ የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
- ተቋሙ በዋና መ/ቤትና በቅ/ጽ/ቤቶች የኢሚግሬሽን አገልግሎት ለማግኘት ተገልጋዮች በአካል መጥተው የሚያቀርቡት ማስረጃ እና አስቸኳይ ፓስፖርት የሚያወጡ ተገልጋዮች መረጃ ዲጂታላይዝድ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- ተቋሙ የኢሚግሬሽን መረጃ አደረጃጀት መመሪያን በሚመለከተው አካል አጸድቆ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፤
- ተቋሙ በዋና መ/ቤትና በቅ/ጽ/ቤቶች መረጃን በአግባቡ አደራጅቶ ለመያዝ የሚያስችል ክፍል በማዘጋጀት የፓስፖርት አገልግሎት መረጃዎችን እና ማስረጃዎችን ከአቀማመጥ ጉድለት እንዳይበላሹና በቀላሉ እንዲገኙ በአይነት፣ በጊዜና በደህንነት ደረጃቸው ለይቶ በአግባቡ ሊያዝ በሚያስችል መልኩ ቀልጣፋ እና ውጤታማ ስራ መስራት አለበት፡፡
- ተቋሙ ለህትመት የሚያገለግሉ የኤሌክትሮኒክስ እቃዎችና የህትመት ማሽኖች ወቅቱን ጠብቀው መጠገናቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡

- ተቋሙ ለፓስፖርት አገልግሎት ስርዓቱ (System) የቅድመ ብልሽትና የጥገና እቅድ አዘጋጅቶ በዕቅዱ መሰረት ቁጥጥር እና ጥገና ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- ተቋሙ የፓስፖርት አገልግሎትን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር የሚሰሩ ጉዳዮችን ለይቶ በማስቀመጥ ተግባራዊነቱን በጋራ የሚከታተልበት ስርዓት በመዘርጋት በቅንጅት መስራት ይጠበቅበታል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት * Office of the Federal Auditor General *

አባሪ አንድ:- የመመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria)

ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት፡- የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት

የኦዲቱ አካባቢ፡- የፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነትን በተመለከተ

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issue)	የኦዲቱ የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria)
1.የመደበኛና አስቸኳይ ፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤	1. ተቋሙ የኢሚግሬሽን አሰራር ስርዓትን የሚመለከት ፖሊሲ ሊያመነጭና ለሚመለከተው አካል በማቅረብ አጸድቆ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል። ምንጭ፡- የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 449/2011 አንቀጽ 5 ን.አ 14
	2. ተቋሙ ለፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ የሚያገለግሉ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት እና መመሪያና ስታንዳርድ አዘጋጅቶ በማጸደቅ ተግባራዊ ሊያደርግና አፈፃፀሙን ሊከታተል ይገባል። ምንጭ፡- የኢሚግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ የአምስት ዓመት (2014-2018 ዓ.ም) ስትራቴጂካዊ እቅድ ገጽ11፣12 እና የኢምግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ተቋማዊ አደረጃጀት ሰነድ ገጽ 6
	3. ተቋሙ የፓስፖርት አገልግሎትን ለማሳለጥ የሚያስችል የዜጎች ቻርተር ሰነድ አዘጋጅቶ በማጽደቅ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምንጭ፡- የኢሚግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ የአምስት ዓመት (2014-2018 ዓ.ም) ስትራቴጂካዊ እቅድ ገጽ 11
	4. የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ተቋማዊ መዋቅር በማጥናትና ለሚመለከተው አካል በማጸደቅ የተፈቀደው የስራ መደብ በሰው ኃይል ሊሟላ ይገባል። ምንጭ፡-የ2015 በጀት ዓመት ዓመታዊ እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ገጽ 15

	5. ተቋሙ ሰራተኞች ስራ ከመጀመራቸው በፊት የስራ መዘርዝር (Job Description) አዘጋጅቶ በማጽደቅ ሊሰጥ ይገባል። ምንጭ፡- የኦንላይን ሲስተም አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል የተዘጋጀ ጥናት ሐምሌ 2013ዓ.ም ገጽ 10
	6. ተቋሙ በዓለም አቀፉ የሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ስታንዳርድ (ICAO DOC 9303) መሰረት ጥናት በማድረግ የቡክሌት ፓስፖርትን ወደ ኢ-ፓስፖርት መቀየር የሚያስችል አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምንጭ፡- የኢሚግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ የአምስት ዓመት (2014-2018 ዓ.ም) ስትራቴጂካዊ እቅድ ገጽ 48 እና የፓስፖርት አገልግሎት መሪ ስራ አስፈጻሚ የስራ መዘርዝር ገጽ 2
	7. ተቋሙ ከድንበርና ከጎረቤት ሃገራት መሆናቸው አጠራጣሪ የሆኑ ተገልጋዮች ሲያጋጥሙ ዜግነታቸው የሚጣራበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምንጭ፡- የኢምግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ተቋማዊ አደረጃጀት ሰነድ ገጽ 32
	8. ተቋሙ የአዲስ መደበኛ ፓስፖርት፣ ለአስቸኳይ ፓስፖርት እና የፓስፖርት እድሳት አገልግሎት ፈላጊዎች በተቀመጠላቸው መመሪያ፣ ስታንዳርድ እና የጊዜ ሰሌዳ መሰረት አገልግሎቱን ማግኘታቸውን የሚከታተልበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምንጭ፡- የአዲስ ፓስፖርት ምዝገባ አገልግሎት ዴስክ የስራ መዘርዝር ገጽ 3 እና የኢምግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ተቋማዊ አደረጃጀት ሰነድ ገጽ 30፣31
	9. ተቋሙ የፓስፖርት ምዝገባ ቀን ቀጠሮ ያሳለፉ ግለሰቦች የሚስተናገዱበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል።

	ምንጭ፡- የኦንላይን ፓስፖርት ምዝገባ ቀን ቀጠሮ ያሳለፉ ግለሰቦች ቅጣት ክፍያ መመሪያ ጥቅምት 2014 ዓ.ም
	10.ተቋሙ ከመልክት አስተላላፊ ተቋማት ጋር የፓስፖርት ስርጭትን ለማካሄድ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል። ምንጭ፡-የስርጭት ዴስክ ኃላፊ የስራ መዘርዝር ገጽ 3 እና 5
	11.ተቋሙ የፓስፖርት የአገልግሎት ጥራት፣ ተደራሽነትና ሽፋን ደረጃን ለመገምገም፣ ለመቆጣጠርና ለመደገፍ የሚያስችል ጥናት በማካሄድ በአሰራር ሂደት የታዩ ችግሮች ላይ የመፍትሄ ሀሳብ የሚሰጥበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምንጭ፡- የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 449/2011 አንቀጽ 5 ን.አ 10
	12.በተቋሙም ሆነ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የፓስፖርት አገልግሎትን ለመስጠት የቢሮው አቀማመጥ የስራ ፍሰትን ባማከለ መልኩ ሊደራጅና መጠለያ ያለው ወረፋ መጠበቂያ እንዲሁም መጸዳጃ ሊኖር ይገባል፡፡ ምንጭ፡- የኢሚግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ የአምስት ዓመት (2014-2018 ዓ.ም) ስትራቴጂካዊ እቅድ ገጽ 11 እና የአሰቸኳይ ፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥን ወደ መደበኛ ስርዓት ለማስገባት የተዘጋጀ የጥናት ሰነድ ነሀሴ- 2014 ዓ.ም ገጽ 5
	13.በተቋሙ የሰራተኞች የስነ ምግባር መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል። ምንጭ፡- የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት የ2014 በጀት ዓመት ዓመታዊ እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ገጽ 20
	14.በተቋሙ የተገልጋይ ቅሬታ መፍቻ ስርዓት ሊኖርና የሚቀርቡ ቅሬታዎችም በወቅቱ የሚፈቱበት የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል። ምንጭ፡- የኢሚግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ የአምስት ዓመት (2014-2018 ዓ.ም) ስትራቴጂካዊ እቅድ ገጽ12

	15.ተቋሙ በፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የሚታዩ የብልሹ አሰራር ችግሮችን ለመከላከል የሚያስችል ተጠያቂነት ያለበት አሰራር በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- የኢሚግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ የአምስት ዓመት (2014-2018 ዓ.ም) ስትራቴጂካዊ እቅድ ገጽ22 እና የኢምግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ተቋማዊ አደረጃጀት ሰነድ ገጽ 29**
2.የፓስፖርት ግብዓቶች ግዥ አፈጻጸም ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤	16.ተቋሙ የፓስፖርት ግብዓቶች የግዥ ዕቅድ ሊኖረውና ግዥውም በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ ስለመደረጉ የሚከታተልበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- የኢምግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ተቋማዊ አደረጃጀት ሰነድ ገጽ 83**
	17.ተቋሙ ለፓስፖርት ግብዓቶች መስፈርት ሊያዘጋጅና ግዥውም በተዘጋጀው መስፈርት መሰረት ስለመከናወኑ የሚያረጋግጥበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- የኢምግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ተቋማዊ አደረጃጀት ሰነድ ገጽ 60**
	18. ተቋሙ ለፓስፖርት ግብቶች ግዥ የውል ስምምነት ሊፈራረምና ግዥው በውሉ መሰረት ስለመከናወኑ የሚቆጣጠርበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል። **ምንጭ፡- የፌደራል መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የግዥ አፈጻጸም ማንዋል ሐምሌ2002 ዓ.ም ገጽ 148**
3.የፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ የክትትል እና የስልጠና ስርዓት መኖሩንና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፤	19.ተቋሙ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን የፓስፖርት አገልግሎትን ለመስጠት በሚያስችል መልኩ (በግብዓትና በቴክኒክ) ሊያደራጅና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- የኢምግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ተቋማዊ አደረጃጀት ሰነድ ገጽ 33**
	20.ተቋሙ ስትራቴጂክ ዕቅድ በማዘጋጀት በስትራቴጂክ ዕቅዱ መሰረት ዓመታዊ ዕቅድ ሊያዘጋጅና ዳይሬክቶሬቶችም (የስራ ክፍሎችም) በተቋሙ ዕቅድ

	መሰረት የስራ ክፍላቸውን ዕቅድ አዘጋጅተው አፈጻጸማቸውን በወጥነት የሚከታተሉበት፣ የሚገመግሙበትና ግብረመልስ የሚሰጡበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል። **ምንጭ፡- የኢምግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ተቋማዊ አደረጃጀት ሰነድ ገጽ** 33 **እና የኢሚግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ የአምስት ዓመት** (2014-2018 **ዓ.ም**) **ስትራቴጂካዊ እቅድ ገጽ** 11
	21.ተቋሙ የፓስፖርት መረጃ ህትመት ጥራትና ቁጥጥር ስራን በመስራት ፓስፖርት በአለም አቀፍና በተቋሙ ስታንዳርድ መሰረት መታተሙን የሚከታተልበትና የሚቆጣጠርበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- የኢምግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ተቋማዊ አደረጃጀት ሰነድ ገጽ** 60
	22.ተቋሙ በፓስፖርት አገልግሎት ዙሪያ በክፍተት ላይ የተመሰረተ ስልጠናዎችን የሚሰጥበትና ስልጠናው ያስገኘው ውጤት የሚገመግምበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር** 449/2011
	23.ተቋሙ በፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮችን እና ሚዲያዎችን በመጠቀም ለህብረተሰቡና ባለድርሻ አካላት ቀጣይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- የኢሚግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ የአምስት ዓመት** (2014-2018 **ዓ.ም**) **ስትራቴጂካዊ እቅድ ገጽ** 26፣36፣22
	24.ተቋሙ የፓስፖርት አገልግሎትን ለመስጠት ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን የህብረተሰብ አካላት ተጠቃሚ የሚያደርግበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል።

	ምንጭ፡- በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ1263/2014ዓ.19 ን.ዓ 11
4. በቴክኖሎጂ የተደገፈ ውጤታማ የመረጃ አያያዝ፣ ጥገና እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር መኖሩንና ተግባራዊነቱን መገምገም፤	25.ተቋሙ ዘመናዊ የመረጃ ማዕከላትን (data center)፣ ምትክ ቅጂ (Backup) እና የአደጋ ጊዜ መጠባበቂያ ማዕከላት (Disaster recovery sites) ሊያደራጅና የፓስፖርት መረጃዎች ለአደጋ እንዳይጋለጡ ተገቢውን ደህንነትና ጥበቃ የሚያደርግበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምንጭ፡- የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 449/2011 እና የኢምግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ተቋማዊ አደረጃጀት ሰነድ ገጽ8
	26.ተቋሙ የፓስፖርት መረጃ ጥራት እና ደህንነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የአሰራር ስርአት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምንጭ፡- የኢምግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ተቋማዊ አደረጃጀት ሰነድ ገጽ37
	27.የኢሚግሬሽን አገልግሎት ለማግኘት ተገልጋዮች የሞሏቸው ቅጾች ዲጂታላይዝድ ሊደረጉ ይገባል፡፡ ምንጭ፡- የኢሚግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ የአምስት ዓመት (2014-2018 ዓ.ም) ስትራቴጂካዊ እቅድ ገጽ13
	28.የፓስፖርት አገልግሎት መረጃዎች እና ማስረጃዎች በአይነት፣ በጊዜና በደህንነት ደረጃቸዉ ተለይተው ሊደራጁና በአግባቡ ሊያዙ ይገባል፡፡ ምንጭ፡- የኢምግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ተቋማዊ አደረጃጀት ሰነድ ገጽ30
	29.ተቋሙ ለህትመት የሚያገለግሉ የኤሌክትሮኒክስ እቃዎችና የህትመት ማሽኖች ወቅቱን ጠብቀው መጠገናቸውን የሚከታተልበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምንጭ፡- የህትመትና ስርጭት መሪ ስራ አስፈጻሚ የስራ መዘርዝር ገጽ 4

	30. ለፓስፖርት አገልግሎት ስርዓቱ (System) የቅድመ ብልሽት ቁጥጥር /Inspection/ እና የጥገና ዕቅድ በማዘጋጀት በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምንጭ፡- የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ የ2015 እቅድ ገጽ16
	31. ተቋሙ የፓስፖርት አገልግሎትን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር የሚሰሩ ጉዳዮችን በመለየት ተግባራዊነቱን በጋራ የሚከታተልበት ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ ምንጭ፡- የኢሚግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ የአምስት ዓመት (2014-2018 ዓ.ም) ስትራቴጂካዊ እቅድ ገጽ5

አባሪ ሁለት:- የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት አደረጃጀት



አባሪ ሶስት:- በናሙና ተመርጠው የታዩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ዝርዝር

1. ሀዋሳ
2. ሆሳዕና
3. ጅማ
4. ደሴ
5. ድሬዳዋ
6. ጅጅጋ

አባሪ አራት:- ተቋሙ ያሉት የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ብዛት እና ስራ ላይ ያለው የሰው ኃይል

ተ.ቁ	የስራ ሂደቱ መጠሪያ	የተፈቀደ የሰዉ ኃይል	ስራ ላይ ያለ የሰዉ ኃይል	በፐርሰንት
1.	ድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት	24	10	41%
2.	ጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት	14	8	57%
3.	ሰመራ ቅ/ጽ/ቤት	16	4	25%
4.	መቀለ ቅ/ጽ/ቤት	23	-	-
5.	አሶሳ ቅ/ጽ/ቤት	17	4	23.5%
6.	ጋምቤላ ቅ/ጽ/ቤት	18	4	22%
7.	ባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት	22	17	77%
8.	ደሴ ቅ/ጽ/ቤት	23	12	52%
9.	ሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት	23	16	69.5%
10.	አዳማ ቅ/ጽ/ቤት	28	17	60.7%
11.	ጅማ ቅ/ጽ/ቤ/ት	23	17	74%
12.	ሆሳዕና ቅ/ጽ/ቤ/ት	23	12	52%

አባሪ አምስት:- ተቋሙ በገንዘብ ሚኒስቴር የተፈቀደለት አካውንት

1.	1000000984888	HEAD OFFICE D ACCOUNT
2.	1000006957084	AIR PORT B CASH ACCOUNT
3.	1000090923424	AIR PORT B POSS ACCOUNT
4.	1000514624619	ICS B ACCOUNT (DOLLAR)
5.	0101681300002	VIDITURE ACCOUNT
6.	1000459918764	INVEA B ACCOUNT(ONLINE)
7.	1000387040758	ICS B2 ACCOUNT

አባሪ ስድስት:- በዋና መ/ቤትና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የፓስፖርት ስርጭትን የሚያሳይ ሰንጠረዥ

ተቋሙ በዋና መ/ቤትና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ፓስፖርት ማደል የጀመረው መስከረም 20/2016 ዓ.ም ሲሆን እስከ ጥር 18/2016 ዓ.ም የታደለውን ብዛት ከታች ባለው ሰንጠረዥ ተቀምጧል።

ተ.ቁ	በዋና መ/ቤትና አዲስ አበባ ባሉ የተቋሙ ቅርንጫፎች	ለቅርንጫፍ የተላከ (ብዛት)	የታደለ (ብዛት)	ቀሪ (ብዛት)	መግለጫ
1.	መደበኛ ስርጭት	84,312	51,860	32,452	
2.	በኃላፊ የተመራ(በ120)	5,394	5,034	360	
3.	አስቸኳይ አገልግሎት(በ120)	17,745	17,480	265	50ብር የማይሰበሰብበት
	ድምር				

የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ስርጭት ዳታ

ተ.ቁ	የቅ/ጽ/ቤት ስም ዝርዝር	ጠቅላላ ለቅርንጫፍ የተላከ(ብዛት)	የታደለ(ብዛት)	ቀሪ(ብዛት)
1.	አዳማ	5,208	2,332	2,876
2.	አሶሳ	947	622	325
3.	ጋምቤላ	588	431	157
4.	ሃዋሳ	7,923	2,934	4,989
5.	ድሬዳዋ	3,123	1,606	1,517
6.	ጅግጂጋ	3,108	2,408	700

7.	ሆሳዕና	10,560	7,369	3,119
8.	ደሴ	5,929	3,237	2,692
9.	ሰመራ	1,574	648	926
10.	ባህርዳር	8,434	3,257	5,177
11.	ጅማ	6,853	3,958	2,895
	ድምር	54,247	28,802	25,445

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት * Office of the Federal Auditor General *

አባሪ ሰባት:- በህትመት ጥራት ጉድለት የወደቁ የፓስፖርት ቡክሌትና ላምኔት ብዛት

ዓ.ም	ፓስፖርት ቡክሌት	ላምኔት	ድምር
2013	2240	665	2905
2014	1321	17926	19247
2015	590	1041	1631
2016	724	3500	4224
ድምር	4875	23132	28007

አባሪ ስምንት፡- በዋናው መ/ቤት እና በቅርንጫፎች የሚሰሩ ሰራተኞች በዲሲፕሊን ጉድለት ምክንያት ለዲሲፕሊን ኮሚቴ ቀርበው ጉዳያቸው ተንጠልጥለው ያሉ

ተ.ቁ	የተከሳሽ ሰራተኛ ሙሉ ስም	የስራ ክፍል	ቅርንጫፍ
1	ብርትኳን ተከስተ ፈለቀ	ህግና እግድ ጉዳዮች	ዋና መ/ቤት
2	አቶ ደሳለኝ ፀጋዬ	ሰነዶች ምዝገባ	ሀዋሳ ቅርንጫፍ
3	አቶ ደሳለኝ በዳሳ ጃጊ	ሰነዶች ምዝገባ	ዋና መ/ቤት
4	አቶ አስማማው ስማቸው	ሰነዶች ምዝገባ	አሶሳ ቅርንጫፍ
5	አቶ ንዋይ ደምሰ	ሰነዶች ምዘዝገባ	አዳማ ቅርንጫፍ
6	ወ/ሮ ብዙነሽ ደጀኔ	ሰነዶች ምዝገባ	አዳማ ቅርንጫፍ
7	አቶ መሀመድ መኩሪያ	ህትመትና ስርጭት	ዋና መ/ቤት
8	አቶ ተመስገን ዋሊ	ፋይናንስና በጀት	ዋና መ/ቤት
9	አቶ ታምራት ደስታ	ሰነዶች ምዝገባ	ሆሳዕና ቅርንጫፍ
10	አቶ አለማየሁ አንዛ	ሰነዶች ምዝገባ	ሆሳዕና ቅርንጫፍ
11	አቶ መለሰ ሉንጎ	ሰነዶች ምዝገባ	ሆሳዕና ቅርንጫፍ
12	አቶ አንለይ ደገፉ	ሰነዶች ምዝገባ	ሆሳዕና ቅርንጫፍ

Office of the Federal Auditor General

አባሪ ዘጠኝ፡- ከህዳር 2013 እስከ ሰኔ 2013 በህገወጥ መንገድ ፓስፖርት እንዲታተም ያደረጉ 23 ሰራተኞች እና ከዛ ውስጥ 11ዱ ክሳቸው ምን ላይ እንደደረሰ የማይታወቅ ሰራተኞች ዝርዝር

ተ.ቁ	የተከሳሹ ሰራተኛ ሙሉ ስም	የስራ ክፍል	ቅርንጫፍ	የተሰጡ ውሳኔዎች
1	ወ/ሮ እናትሽ ባይለየኝ አየለ	ሰነዶች ምዝገባና አሰጣጥ	ሀዋሳ	ክሳቸው ምን ላይ እንደደረሰ የማይታወቅ
2	አቶ ኢብራሂም ኡመር ኢብራሂም	ሰነዶች ምዝገባና አሰጣጥ	ድሬዳዋ	በሙስና ክስ ተከሰው በጠ/ዐ/ህግ አማካኝነት 7 ወር የእስር ቅጣት የተቀጡ
3	አቶ ኪሴ ፎርማሲ አብዲሳ	ሰነዶች ምዝገባና አሰጣጥ	አዳማ	በሙስና ክስ ተከሰው በጠ/ዐ/ህግ አማካኝነት 7 ወር የእስር ቅጣት የተቀጡ
4	አቶ ተማም አቡ መሀመድ	ሰነዶች ምዝገባና አሰጣጥ/ባዮዳታ	ዋና መ/ቤት	በሙስና ክስ ተከሰው በጠ/ዐ/ህግ አማካኝነት 7 ወር የእስር ቅጣት የተቀጡ
5	አቶ በሀይሉ ካልሳይ ከሊል	ሰነዶች ምዝገባና አሰጣጥ/ባዮዳታ	ዋና መ/ቤት	በሙስና ክስ ተከሰው በጠ/ዐ/ህግ አማካኝነት 7 ወር የእስር ቅጣት የተቀጡ
6	አቶ ፀጋዬ ገ/መስቀል ገ/ኪዳን	ሰነዶች ምዝገባና አሰጣጥ/ባዮዳታ	ዋና መ/ቤት	ክሳቸው ምን ላይ እንደደረሰ የማይታወቅ
7	አቶ ሀብታሙ ዳዊት ሀ/ወልድ	ሰነዶች ምዝገባና አሰጣጥ /ካሸር	ሀዋሳ	ክሳቸው ምን ላይ እንደደረሰ የማይታወቅ
8	አቶ ክንዱ ጌጤ ሙጩ	ሰነዶች ምዝገባና አሰጣጥ	ባህርዳር	ክሳቸው ምን ላይ እንደደረሰ የማይታወቅ
9	አቶ ሽመልስ ዋሲሁን ቦጋለ	ሰነዶች ምዝገባና አሰጣጥ /አውቶራይዜሽን	ዋና መ/ቤት	በሙስና ክስ ተከሶ በነጻ የተለቀቀ
10	አቶ ዮሴፍ ቃንጣ ባኔታ	ሰነዶች ምዝገባና አሰጣጥ /አውቶራይዜሽን	ዋና መ/ቤት	ክሳቸው ምን ላይ እንደደረሰ የማይታወቅ
11	አቶ እንዳልካቸው አባተ ተሰማ	ሰነዶች ምዝገባና አሰጣጥ /አውቶራይዜሽን	ዋና መ/ቤት	በሙስና ክስ ተከሰው በጠ/ዐ/ህግ አማካኝነት 6 ወር የእስር ቅጣት የተቀጡ
12	ወ/ሮ አዲስ ገብሬ	ሰነዶች	ሀዋሳ	በሙስና ክስ ተከሰው

	አደፍርስ	ምዝገባና አሰጣጥ		በጠ/ዐ/ህግ አማካኝነት 7 ወር የእስር ቅጣት የተቀጡ
13	አቶ ቦካ ዋሴ ለማ	ሰነዶች ምዝገባና አሰጣጥ /ባዮዳታ	ዋና መ/ቤት	ክሳቸው ምን ላይ እንደደረሰ የማይታወቅ
14	ወ/ሮ አምሳል ደመቀ ቀለሙ	ሰነዶች ምዝገባና አሰጣጥ	ሀዋሳ	ክሳቸው ምን ላይ እንደደረሰ የማይታወቅ
15	አቶ መዝገቡ ሙሉነህ አብርሀም	ሰነዶች ምዝገባና አሰጣጥ	ሀዋሳ	ክሳቸው ምን ላይ እንደደረሰ የማይታወቅ
16	አቶ ገበየሁ እሸቱ ዲነግዴ	ሰነዶች ምዝገባና አሰጣጥ /ካሸር	ዋና መ/ቤት	በሙስና ክስ ተከሰው በጠ/ዐ/ህግ አማካኝነት 7 ወር የእስር ቅጣት የተቀጡ
17	አቶ አበራ ኤርሚያስ ሂይሶ	ሰነዶች ምዝገባና አሰጣጥ /ካሸር	ዋና መ/ቤት	ክሳቸው ምን ላይ እንደደረሰ የማይታወቅ
18	ወ/ሮ አየለች አሉላ ፍሰሀ	ሰነዶች ምዝገባና አሰጣጥ	ሀዋሳ	ክሳቸው ምን ላይ እንደደረሰ የማይታወቅ
19	ወ/ሪት አያንቱ ለገሰ ዱሬሳ	ሰነዶች ምዝገባና አሰጣጥ	አዳማ	በሙስና ክስ ተከሰው በጠ/ዐ/ህግ አማካኝነት 7 ወር የእስር ቅጣት የተቀጡ
20	ወ/ሮ ውባለም ማናዬ አንዷለም	ሰነዶች ምዝገባና አሰጣጥ /ካሸር	ዋና መ/ቤት	በሙስና ክስ ተከሰው በጠ/ዐ/ህግ አማካኝነት 6 ወር የእስር ቅጣት የተቀጡ
21	ወ/ሮ ፀሀይ ማሞ ደጁ	ሰነዶች ምዝገባና አሰጣጥ /ካሸር	ዋና መ/ቤት	ክሳቸው ምን ላይ እንደደረሰ የማይታወቅ
22	ወ/ሪት በቀሉ ዳምጤ አበጋዝ	ሰነዶች ምዝገባና አሰጣጥ /ካሸር	ዋና መ/ቤት	በሙስና ክስ ተከሰው በጠ/ዐ/ህግ አማካኝነት 6 ወር የእስር ቅጣት የተቀጡ
23	አቶ ኡመር ሀጅ በሪሶ	ሰነዶች ምዝገባና አሰጣጥ /ካሸር	ዋና መ/ቤት	በሙስና ክስ ተከሰው በጠ/ዐ/ህግ አማካኝነት 7 ወር የእስር ቅጣት የተቀጡ

አባሪ አስር፡- ከ 2013 ዓ.ም አስከ ጥር 2016 ዓ.ም ድረስ ገቢና ወጪ የተደረጉ ፓስፖርትና ላሚኔት

እ.አ.አ	ገቢ የተደረገ መደበኛ ፓስፖርት ብዛት	ወጪ የተደረገ መደበኛ ፓስፖርት ብዛት	ገቢ የተደረገ ላሚኔት	ወጪ የተደረገ ላሚኔት
2020	ገቢ አልተደረገም	94,920	ገቢ አልተደረገም	10,400
2021	635,000	585,131	440,000	183,000
2022	ገቢ አልተደረገም	665,400	180,000	326,000
2023	471,800	467,100	480,000	252,000
2024	190,000	ወጪ አልተደረገም	220,000	21,000
ድምር	1,296,800	1,812,551	1,320,000	792,400

Office of the Federal Auditor General